https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 22
ADDIS ABABA, 5nd April, 2021

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ፲፫
የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ .....ገጽ ፲፫፻፺፱፲፫

**Content**

Proclamation No. 1238/2021
Media Proclamation …….....Page 13113

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ፲፫
## የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እንዲሁም በኢትዮጵያ ላይ ግዴታ የሚጥሉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና ለዜጎች የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ቴክኖሎጂ እድገት ጋር የሚጣጣም ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

ሀሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን መብቶች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ለማረጋገጥ ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብ እና በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን መገናኛ ብዙሃን የሚጫወቱትን የማይተካ ሚና በመረዳት ይህን ሁኔታ ሊያስተናግድ የሚችል ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO. 1238/2021
## MEDIA PROCLAMATION

**WHEREAS,** there is a need to enact a law that accommodates the social, economic, political and technological developments in Ethiopia and fully enforce the right to freedom of expression and citizens' freedom of the media which is guaranteed under the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, as well as international human rights instruments which are binding on Ethiopia;

**WHEREAS,** it is important to enact law to entertain the situation of the significance of freedom of expression and of the media in ensuring respect for fundamental rights and freedoms guaranteed by the Constitution, and aware that the media plays an irreplaceable role for the success of efforts towards building a democratic system in Ethiopia;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me


ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን አሰራር እንዲስፋፋ ማድረግ ለፈጣንና ቀጣይነት ላለው ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ የሆነውን በመረጃ የበለፀገ ህብረተሰብ ለመፍጠር የሚያስችልና ለሀገራቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማመን፤

መገናኛ ብዙሃን የሕዝብን ሠላምና ደህንነት፣ እንዲሁም ተነፃፃሪ መብቶችና ጥቅሞችን ባከበረ መልኩ በኃላፊነት መንቀሳቀሳቸውን ማረጋገጥና በሕግ መሠረት እንዲሠሩ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍና ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፪፻፴፰/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የመገናኛ ብዙሃን" ማለት በየጊዜው የሚወጣ ህትመትን የብሮድካስት አገልግሎትን እና የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የዜና ወይም የፕሮግራም ወይም የዜና እና የፕሮግራም አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ የተቋቋሙ አካላት ሲሆኑ መጻሕፍትን፣ ማኅበራዊ መገኛኛ ብዙሃንን፣ ጦማሮችን እና በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አካል ያልሆኑ ፎቶ፣ ስዕልና ካርቱንን ሳይጨምር የዜና አገልግሎት ድርጅቶችን ያካትታል፤

**WHEREAS,** ensuring the expansion of media services that are accessible and of high quality enables to create an informed society, which is key to accelerate sustainable and holistic political, social and economic development;

**WHEREAS,** by understanding the need to have a legal framework and system that ensure the media operate responsibly by respecting the public peace, security and competing rights and interests;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “Media Proclamation No. 1238/2021.”

### 2. Definition

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ “Media” means, excluding books, social media, blogs, and photos, images and cartoons that are not part of a periodical, news agencies and all organs established to provide news or programs or news and programs to the public via periodicals, broadcasting service, and online media;

https://chilot.me


፪/ "በየጊዜው የሚወጣ ህትመት" ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም፣ ለጠቅላላው ህብረተሰብ ወይም ለአንድ የተወሰነ የሕዝብ ክፍል እንዲደርስ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መፅሔቶችን የሚያካትት የህትመት ሥራ ነው፤

2/ “Periodical” means printed material which is scheduled to appear in regular intervals of at least twice a year, has a fixed title, is aimed at the entire public or a section thereof and includes newspapers and magazines;

፫/ “የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ዳታና የጽሁፍ መልዕክትን፣ የግል ድርጅት ወይም የመንግሥት አካል ውስጣዊ ግንኙነቶችን ሳይጨምር ከምድር ወደ አየር አስተላላፊ፣ በሬዲዮ ሞገድ፣ በኬብል፣ በሳተላይት፣ ወይም እነዚህን በማቀናጀት ሥራ ላይ በሚውሉ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሰራጫዎች አማካይነት አጠቃላይ ሕዝብን ወይም የተወሰነ የህብረተሰብን ክፍል ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት በድምፅ ወይም በምስል ወይም በድምፅና በምስል በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ ወይም የሚሰራጭ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

3/ “Broadcasting service” means the transmission of images or sound or both images and sound, to inform, educate or entertain the general public or sections of the public who have equipment appropriate for receiving these services; whether the delivery is through terrestrial transmitters, radio frequency spectrum, cable, satellite, or a combination of these, whether by subscription to such a service or not, through radio and/or television broadcast receivers; but does not include a service which provides no more than data or text, with or without associated still images; or communications internal to a private organization or a government body;

፬/ "የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን" ማለት በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ሥር ዋነኛ ሥራው ዜናና ፕሮግራምን መሰብሰብ፣ ማዘጋጀት፣ ማጠናቀርና ማሰራጨት በሆነ ድርጅት በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ምስል፣ ድምፅ፣ ቪድዮ እና የድረ-ገፅ ጽሁፍን በመጠቀም ወይም እነዚህን በማቀናጀት መረጃ የማስተላለፍ አገልግሎት ነው፤

4/ “Online media” means an internet-based information dissemination service by an organization whose principal business involves the collection, production, processing and dissemination of news or programs or news and programs, through online images, audio, video and websites or through a combination of the aforementioned means, in accordance with the editorial responsibility of a media service provider;

https://chilot.me


፰/ "ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት" ማለት በዜና ወይም በፕሮግራም መረጣ ወይም አቀራረብ ላይ ውጤታማ ቁጥጥርን ተግባራዊ ማድረግ ነው፤

5/ “Editorial responsibility” means the exercise of effective control over both the selection of the news or programs and over their organization;

፱/ “ዜና” ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት በየጊዜው በሚወጣ ህትመት ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚቀርብ የዘገባ ሥርጭት ነው፤

6/ “News” means transmission of report on current affairs having local, regional, national or international content presented through periodicals, or broadcasting service, or online media;

፲/ “ፕሮግራም” ማለት በየጊዜው ሰዓቱ ወይም ሰፋ ያለ ጊዜ ጠብቆ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በድምፅ፣ በምስል ወይም በድምፅና በምስል ተቀነባብሮ ሕዝብን ለማሳወቅ ወይም ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት እና በበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚቀርብ ዝግጅት ነው፤

7/ “Program” means a continuous feed of audio, visual or audiovisual content, produced and transmitted locally through any broadcasting service and online media whether over 24 hours or extensive period of time, intended to inform or educate or entertain the public, or inclusive of all;

፲፩/ “የብሮድካስት ፈቃድ” ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት በባለሥልጣኑ ለብሮድካስት ፈቃድ አመልካች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

8/ “Broadcasting license” means a license issued by the Authority granted to an applicant for the purpose of providing a broadcasting service;

፲፪/ “የብሮድካስት ባለፈቃድ” ማለት በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት የፀና የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

9/ “Broadcasting licensee” means a person that has been granted a broadcasting service license in accordance with this Proclamation or Regulations or Directives issued hereunder;

፲፫/ “የፈቃድ አካባቢ” ማለት በብሮድካስት ፈቃድ ላይ የብሮድካስት አገልግሎቱን ለመስጠት ተለይቶ የተቀመጠ አካባቢ ነው፤

10/ “License area” means the geographical target area of a broadcasting service as specified in the relevant broadcasting license;

https://chilot.me


፲፩/ "የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ በሕግ የተቋቋመ ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤት የሆነ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በመንግሥት በጀት የሚተዳደር፣ ከመንግሥት ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጡ ይዘቶች በማዘጋጀት ለሕዝብ የማቅረብ ግዴታ ያለበት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

11/ "Public service broadcasting" means a radio or television transmission established at National or Regional State level, accountable to the House of Peoples' Representatives or to Regional Councils; wholly or substantially financed by government budget with a mandate to provide contents that guarantee public interest while remaining neutral and independent of government;

፲፪/ "ልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ መሰረት በተቋቋመ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት አማካኝነት የሚመሰረት ሆኖ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጡ ይዘቶች በማዘጋጀት ለሕዝብ የማቅረብ ግዴታ ያለበት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

12/ "Special public service broadcasting" means a radio or television broadcast service established by a civil society organization formed on the basis of the Civil Society Organization Proclamation with a mandate to provide content that guarantee public interest;

፲፫/ "የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት የሕግ ሰውነት በተሰጠው የንግድ ድርጅት ወይም ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ የግል ድርጅት ባለድርሻ በሆነበት ሌላ ድርጅት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ ወይም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

13/ "Commercial broadcasting service" means a broadcasting service provided by a business organization conferred with a legal personality or an organization that is privately owned and operated for profit or as part of a profit entity and available to the public free of charge or through payment;

፲፬/ "የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ባለቤትነቱና አስተዳደሩ አገልግሎቱ ታላሚ ባደረገው ማኅበረሰብ ተወካዮችና ፍላጎት የሚመራ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ጣቢያ ለተለየ ማኅበረሰብ የሚያቀርበው የብሮድካስት አገልግሎት ሲሆን የማኅበረሰቡን አባላት እና ከማኅበረሰቡ ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይም የማኅበረሰቡን ጥቅም ለማሳደግ የሚሰሩ ግለሰቦች በፕሮግራም መረጣና አቅርቦት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታና አገልግሎቱን በአጠቃላይ ለሕዝቡ በነፃ የሚያቀርብ ነው፤

14/ "Community broadcasting service" means a non-profit broadcasting service provided for a specific community free of charge via a radio or television station whose ownership and management are representative of the community for which the service is provided; and it encourages members of the community it serves, persons associated with it or those that promote the interests of such communities to participate in the selection and provision of programs.

https://chilot.me


፲፭/ “ማኅበረሰብ” ማለት በአንድ አካባቢ በመኖራቸው ወይም የተለየ ማንነት በመጋራታቸው የተነሳ፣ የተለየ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ወይም በተለየ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ዙሪያ የተሰባሰበ የሕዝብ ክፍል ነው፤

15/ “Community” means people bound by a distinctive identity, by virtue of living in one place or locality, or by common interests and objectives; or a sector of the public bound by a specific, ascertainable common interest;

፲፮/ “ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በዓለም አቀፉ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት ለኢትዮጵያ የተመደበውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰጥ የአናሎግ ወይም የዲጂታል የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

16/ "Terrestrial broadcasting service" means analogue or digital radio or television broadcasting service in which information can be transmitted by radio waves assigned to Ethiopia for broadcasting use by the International Telecommunications Union (ITU), as per International Agreements;

፲፯/ “ነፃ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ለብሮድካስት ባለፈቃዱ ምንም ክፍያ ሳያስፈልግ ለተጠቃሚው በተለመደው የብሮድካስት መቀበያ መሳርያ አማካይነት የሚደርስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

17/ “Free broadcasting service” means broadcasting service that can be received by the end user through conventional broadcast receiving equipment without payment to the broadcasting service licensee;

፲፰/ “የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ሳተላይት ላይ በተቀመጡ ማሰራጫዎች አማካይነት የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

18/ "Satellite broadcasting service" means a broadcasting service which is broadcasted by transmitters situated on a satellite;

፲፱/ “የኬብል የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በኬብል አማካይነት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለደንበኞች የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

19/ “Cable broadcasting service” means a television broadcasting service provided to subscribers via cable;

፳/ “የክፍያ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት ለአጠቃላይ ሕዝቡ ተደራሽ የሆነና በክፍያ ብቻ በቋሚነት ወይም በተለያዩ ጊዜያት አገልግሎቱን ለሚፈልጉ ደንበኞች ፕሮግራሞችን የማድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

20/ “Subscription broadcasting service” means a broadcasting service made available permanently or on-demand to the general public only upon payment of fee by subscribers;

https://chilot.me


፳፩/ “በተፈለገ ጊዜ ተደራሽ የሚሆን ቴሌቪዥን ፕሮግራም” ማለት ኤሌክትሮኒክ ኮሚዩኒኬሽን ኔትወርክ በመጠቀም አገልግሎቱን ለመጠቀም ጥያቄ ላቀረቡ ተጠቃሚዎች በመረጡት ሰዓት ከፕሮግራም ዝርዝሮቹ መካከል ተጠቃሚዎች የመረጡትን ፕሮግራም በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው አማካይነት የማሰራጨት የቴሌቪዥን ፕሮግራም አገልግሎት ነው፤

21/ “On-demand television program” means a media service, particularly television programs, provided to the public via electronic communications networks, upon the request of the user, at a time chosen by the user, and from a catalogue of programs that the provider has prepared for selection;

፳፪/ “አናሎግ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት አናሎግ ሞጁሌሽን ቴክኒክ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

22/ “Analog broadcasting service” means a broadcasting service that is transmitted using analog modulation technique;

፳፫/ “ዓለም አቀፍ የብሮድካስት አገልግሎት” ማለት በዋነኛነት ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ አድማጭና ተመልካቾች ዜናና ፕሮግራም የሚያቀርብና አገልግሎቱን ለመስጠት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሬዲዮ ኮሙዩኒኬሽን ማሰራጫን ብቻ ወይም ከሌሎች ማሰራጫ መንገዶች ጋር በማቀናጀት የሚጠቀም የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

23/ “International broadcasting service” means a broadcasting service that provides news and programs which significantly target audiences outside Ethiopia, where the means of delivering the services involves the use of a radio communications transmitter situated in Ethiopia, either exclusively or in combination with other transmission systems;

፳፬/ “ሀገር አቀፍ ሥርጭት” ማለት በመላ ሀገሪቱ የሥርጭት ሽፋን ባለው የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚሰጥ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት ነው፤

24/ “National transmission” means broadcasting service provided by a broadcasting service licensee the transmission of which has a nation-wide coverage;

፳፭/ “ክልላዊ ሥርጭት” ማለት በብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚሰራጭ በአንድ ክልል ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት ነው፤

25/ “Regional transmission” means broadcasting service provided by a broadcasting service licensee the transmission of which is limited to only one Regional State;

፳፮/ “አካባቢያዊ ሥርጭት” ማለት ከክልል በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት ነው፤

26/ “Local transmission” means broadcasting service provided by a broadcasting service licensee the transmission of which is limited to administrative structures below Regional States;

https://chilot.me


፳፯/ “ሀገር በቀል ይዘት” ማለት ስፖርታዊ ክንውኖችንና ጥንቅሮችን እንዲሁም ማስታወቂያ የማያካትት በሀገር ውስጥ በሚገኝ የብሮድካስት አገልግሎት በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ በሆነ ዜጋ ወይም አብዛኛዎቹ ዳይሬክተሮቹ፣ ባለድርሻዎቹ ወይም አባላቱ በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች የሆኑበት የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ወይም እነዚህ በጋራ ወይም እነዚህ የተጠቀሱት ግለሰቦች ቢያንስ ፶ በመቶ የገንዘብ ጥቅም ይዘው ከሌላ አካል ጋር በጥምረት በማዘጋጀት የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራም፣ ሙዚቃ፣ ድራማ ወይም ዘጋቢ ፊልም ነው፤

27/ “Domestic content” means a broadcasting service program, music, drama, and documentary, excluding transmission of sporting events and compilations thereof, and advertisements, which is produced; by a broadcasting service licensee; by a natural person who is a citizen of, and permanently resident in, Ethiopia; by a juristic person, the majority of the directors, shareholders or members of whom are citizens of, and permanently resident in, Ethiopia; or in a co-production in which persons referred to above have at least a 50 percent financial interest; by persons referred to above, in circumstances where the prescribed number of key personnel who are involved in the production of the program, are citizens of, and permanently resident in, Ethiopia;

፳፰/ “የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ” ማለት አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት እራሱንና ዓላማውን ለማስተዋወቅ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በየጊዜው በሚወጣ ህትመት ወይም በበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን የሚያስነግረው ማስታወቂያ ነው፤

28/ “Election campaign advertisement” means radio, television, periodical or online media promotions made upon payment or promise of payment by a political organization or private candidate during election period to publicize themselves and their objectives;

፳፱/ "ዋና አዘጋጅ" ማለት በየጊዜው የሚወጣ ህትመትና የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

29/ “Editor-in-chief” means a natural person who exercises editorial responsibility over a periodical or an online media;

https://chilot.me


፴/ "ፕሮግራም ኃላፊ" ማለት በብሮድካስት አገልግሎት ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

30/ “Program director” means a natural person who exercises editorial responsibility over a broadcasting service;

፴፩/ "አሳታሚ" ማለት በየጊዜው የሚወጣ ህትመትን ወይም የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃንን የሚያሳትምና ለሥርጭት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

31/ “Publisher” means any person who publishes or distributes a periodical or an online media;

፴፪/ "አታሚ" ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችን ለማተም በአሳታሚው የተመረጠ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ማንኛውም ሰው ነው፤

32/ “Printer” means any person who has been designated by or enters into a contract with a publisher for the purpose of printing a periodical;

፴፫/ “ቁጥጥር” ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶችና የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን በሕግ መሠረት መሥራታቸውንና ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን የመከታተል፣ የማረጋገጥና የማገዝ ሥራ ነው፤

33/ “Regulation” means the work of following-up, ensuring and assisting broadcasting service licensees and online media so that they can operate and discharge their responsibilities in line with the law by setting and applying administrative rules relating to the operation of the media;

፴፬/ "የመገናኛ ብዙሃን የእርስ በእርስ ቁጥጥር" ማለት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርተው የሚገዙበትን፣ የሙያ ሥነ ምግባርና የመልካም አሠራር ደንብ የሚያወጡበት፣ የዘርፉን የሙያ ብቃት የሚያሳድጉበትና የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ቅሬታዎች የሚያስተናግዱበትን አሰራር በመዘርጋት ራሳቸውን ለሕዝቡ ተጠያቂ አድርገው እርስ በእርስ የሚተራረሙበት ሂደት ነው፤

34/ “Media self-regulation” means a voluntary peer review and learning process used by media institutions by setting up and abiding by editorial guidelines, professional ethics and Codes of Conduct to enhance professional expertise and devise a mechanism to entertain complaints and ensure public accountability;

https://chilot.me


፴፭/ "የመረጃ ብዝሃነት" ማለት የተለያየ ይዘት ያላቸውን ሀሳቦች በተለያዩ አቀራረቦች፣ አመለካከቶችና እይታዎች ማቅረብ እንዲሁም ለሕዝብ የሚደርሱ የመገናኛ ብዙሃን ዜናና ፕሮግራሞች፣ ትንተናና አስተያየቶች ይዘት ጾታን፣ ብሔርን፣ የአካል ጉዳትን፣ ሃይማኖትን፣ ዕድሜን፣ የምጣኔ ሀብት ተሳታፊነትን፣ የፖለቲካ አመለካከትና አስተያየቶችን በተቻለና ምክንያታዊ በሆነ መጠን ሚዛናዊና ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንዲያካትትና እንዲያንጸባርቅ ማድረግ ነው፤

35/ “Information diversity” means, to the extent possible and reasonable, provision of content that covers a range of manners, views, and perspectives, and balance proportional inclusion and reflection, of gender, ethnicity, disability, religion, age, economic participation and political views and opinions in news, programs, analysis and commentaries of the media presented to the public;

፴፮/ "የሕዝብ ጥቅም" ማለት ከግል ወይም ከጥቂት ቡድኖች የጥቅም ፍላጎት በተቃራኒ የማኅበረሰቡን የደህንነት፣ የምጣኔ ሃብት፣ የባህል፣ የፖለቲካ እና መሰል ተፈጥሮ ያላቸውን ጥቅሞች ጨምሮ የሰፊው ሕዝብ ተጠቃሚነት ነው፤

36/ “Public interest” means the need of the wider public – whether of a security, economic, cultural, political or other nature – as opposed to a private or a limited group's interest;

፴፯/ "የባለድርሻ አካላት ምክክር" ማለት ባለሥልጣኑ ፍላጎት ያላቸው ባለድርሻ አካላት በባለሥልጣኑ እየታየ ባለ ጉዳይ ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ ጥሪ የሚያደርግበት ሂደት ነው፤

37/ “Stakeholder consultation” means a process by which the Authority reaches out to hear the views of interested stakeholders in a matter under consideration;

፴፰/ "ሕዝባዊ አካል" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል ሕገ መንግሥት ወይም በሌላ ሕግ መሰረት የተቋቋመ እና ሌላ ማንኛውም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥታት መዋቅር ውስጥ የሚገኝ አካል ወይም ዋነኛ የፋይናንስ ምንጩን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከእነዚሁ አካላት የሚያገኝ ወይም ተጠሪነቱ ለፌደራል ወይም ለክልል መንግሥት የሆነ ማንኛውም አካል ነው፤

38/ “Public body” means any ‘body’ established under the Federal Constitution or State Constitution or any other law and any other body which forms part of Federal or Regional Government or owned, controlled or directly or indirectly substantially financed by funds provided by the Federal or Regional Governments or accountable to the Federal or Regional States;

https://chilot.me


፴፱/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

39/ “Region” means a Regional State established under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for the purpose of this Proclamation shall include Addis Ababa and Dire Dawa;

፵/ "ዘመድ" ማለት ወደላይ፣ ወይም ወደታች ወይም ወደጎን የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ነው፤

40/ “Relative” means persons related by consanguinity or by affinity in the ascending or the descending or the collateral lines;

፵፩/ "ባለሥልጣን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፤

41/ “Authority” means Ethiopian Media Authority established under Article 4 of this Proclamation;

፵፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

42/ “Person” means a natural or juridical person;

፵፫/ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

43/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable to the following:

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቋቋሙ መገናኛ ብዙሃን፣ እንደገና በሚመዘገቡ በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶች እና ፈቃድ በሚያሻሽሉ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች፤

1/ media established in accordance with this Proclamation, periodicals that reregister and broadcasting services that amend license;

፪/ ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚታተም በየጊዜው የሚወጣ ህትመት፤ እና፣

2/ any foreign periodical which focuses on national issues and entered into Ethiopia with the intention of disseminating in the country; and,

፫/ ሀገር ውስጥ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ወይም ወኪል ቢኖረውም ባይኖረውም ማንኛውም በውጭ ሀገር ተቋቁሞ እና በውጭ ሀገር የብሮድካስት ፈቃድ አግኝቶ ማንኛውንም የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ በመጠቀም ፕሮግራሞቹን የሚያሰራጭ ሆኖ፡-

3/ whether or not it has a branch office or an agent in the country, any broadcast service provider established and licensed abroad, that transmits programs from abroad through any means of broadcast transmission:

https://chilot.me


ሀ) ከ፶ በመቶ በላይ ይዘቶቹ በኢትዮጵያ ላይ ያተኮሩ፣

ለ) አገልግሎቱን ለኢትዮጵያዊያን አድማጭና ተመልካቾች በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች የሚያቀርብ፣ እና፣

ሐ) ገቢውን በሀገር ውስጥ ከሚገኝ ማስታወቂያና ድጋፍ የሚያገኝ የብሮድካስት አገልግሎት ላይ።

## ክፍል ሁለት
## ስለ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

**፬. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራው) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል።

፫/ የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

**፭. ዓላማዎች**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና በኢትዮጵያ ላይ ግዴታ በሚጥሉ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

a) with more than 50 percent of its content focuses on Ethiopia;

b) providing services to Ethiopian audiences in local languages; and,

c) whose revenue derived from advertising and sponsorship within the country.

## PART TWO
## MEDIA AUTHORITY

**4. Establishment**

1/ The Ethiopian Media Authority (hereinafter referred to as the "Authority") is hereby established as an autonomous Federal Government Agency having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3/ The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may establish branch offices elsewhere in the country as may be necessary.

**5. Objectives**

The Authority shall have the following objectives:

1/ creating enabling environment to fully enforce the rights of freedom of expression and of the media which is guaranteed under the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, as well as International Human Rights Instruments which are binding on Ethiopia;

https://chilot.me


ፀ/ መገናኛ ብዙሃን ተግባራቶቻቸውን በሕግ መሰረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የመገናኛ ብዙሃን የእርስ በእርስ ቁጥጥርና ግምገማ እንዲጠናከር ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

ፁ/ በብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ መስጠት፣ የአገልግሎቱ ተጠቃሚነት፣ ባለቤትነት፣ ዝግጅትና ሥርጭት ላይ ብዝሃነት እንዲጠበቅና እንዲስፋፋ መሥራት፤ እና፣

ፂ/ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በመደበኛነት የሚወያዩበትን መድረክ ማመቻቸት፣ በመገናኛ ብዙሃንና በመንግሥት አካላት መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖርና እንዲጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፡፡

**፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ ሁኔታን ይወስናል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፪/ በብሮድካስት አገልግሎት ለመሰማራት የሚያስችል የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ በማዘጋጀት በቦርድ ያስወስናል፡፡ በመመሪያው መሰረትም የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፫/ ሥርጭቱ ከአንድ ክልል በላይ የሆነ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ሥራን ወይም የዜና አገልግሎት ሥራን ወይም የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃንን በመመዝገብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመስጠት ሕጋዊ እውቅና ይሰጣል፤

2/ regulate broadcasting media to ensure they are operating in accordance with the law; provide proper support to strengthen media self-regulation;

3/ issue broadcasting license; ensure diversity and plurality in the utilization, ownership, production or distribution of broadcasting services; and,

4/ facilitate a regular discussion forum for stakeholder consultation; establish and strengthen a good working relationship between the media and the government.

**6. <u>Power and Duties of the Authority</u>**

The Authority shall have the following power and duties:

1/ determine the licensing condition of broadcasting services; and issue, renew, suspend and revoke broadcasting license;

2/ prepare a Directive that sets the criteria to determine the competency and technical standards of broadcasting services and get it approved by the Board; issue certificates of competency and technical competency based on the Directive;

3/ give legal recognition to a periodical or news service activity or an online media the dissemination of which covers more than one regional state by registering and issuing certificate of registration;

https://chilot.me


፬/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት፣ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃንና የዜና አገልግሎት ምዝገባ፣ የብሮድካስት ፈቃድ፣ የፈቃድ ማሳደሻ እና የብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ አገልግሎቶች ክፍያዎችን መንግሥት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት ይሰበስባል፤

4/ collect periodical, online media and news service registration; broadcasting license; license renewal and the provision of the competency and technical standards of broadcasting services fees in accordance with the rate approved by the government;

፭/ የመገናኛ ብዙሃን ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በሕገ መንግሥቱ፣ በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንብና መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ቁጥጥር ያደርጋል፤

5/ regulate broadcasting media to ensure that they are operating in accordance with the Constitution, this Proclamation, other pertinent laws and Regulations and Directives issued hereunder;

፮/ በማስታወቂያ ሕግ መሠረት ማስታወቂያን ይቆጣጠራል፤

6/ regulate advertisement as per the Advertisement Law;

፯/ የብሮድካስት አገልግሎትን እና የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ በዜጎችና ተቋማት የሚቀርቡትን ቅሬታዎች እንዲሁም በባለፈቃዶች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

7/ investigate and give decisions on grievances lodged by individuals and organizations against broadcasting services and online media as well as on disagreements that arise among the licensees;

፰/ ስለመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ዕድገትና መሻሻል ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎችን አጠናቅሮ ይይዛል፤

8/ conduct researches that contribute to the advancement and improvement of the media services; compile and archive data related to the media sector;

፱/ የፖሊሲና የሕግ ሀሳቦችን ያመነጫል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተማክሮ ለመንግሥት ውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

9/ formulate laws and policy issues in consultation with relevant stakeholders and submit for government approval; and enforces these when approved;

፲/ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በመደበኛነት የሚወያዩበትን መድረክ ማመቻቸትን ጨምሮ በመገናኛ ብዙሃንና በመንግሥት አካላት መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት እንዲኖርና እንዲጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

10/ establish and strengthen good working relationship between the media and the government bodies, including facilitating regular discussion forum for stakeholder consultation;

https://chilot.me


፲፩/ የመገናኛ ብዙሃንን አቅም ለማሳደግ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤ በዚሁ ሥራ ላይ ከሚሰማሩ ሲቪል ማኅበራት፣ የትምህርት፣ የጥናትና ምርምርና የሥልጠና ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤ የመገናኛ ብዙሃንን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን የሥልጠና ማዕከል ያቋቁማል፤

11/ perform consent based capacity building activities including technical and financial support to enhance the capacity of the media; and work in collaboration with civil society, education, research and think-tank institutions working in these areas; organize training center which enables building the capacity of the media;

፲፪/ በብሮድካስት አገልግሎት እና የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን የሚሠራጩ ፕሮግራሞች የሚመሩበትን ዝርዝር የሥነ-ምግባር መመሪያ ያወጣል፤ የእርስ በእርስ ቁጥጥር ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አደረጃጀቶች አስተያየት እንዲሰጡበት አተገባበሩ ላይም እንዲሳተፉ ያደርጋል፤

12/ issue detailed Code of Conduct that directs programs to be disseminated through broadcasting service and online media; ensure that the self-regulation structure of the media are given an opportunity to provide comments on the Code of Conduct and participate in its implementation;

፲፫/ የመገናኛ ብዙሃን የእርስ በእርስ ቁጥጥርና ግምገማ አደረጃጀትና አሰራር እንዲጠናከር ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

13/ provide proper support to strengthen the organizational structure and operation of media self-regulation mechanisms;

፲፬/ ለመገናኛ ብዙሃን ዘገባ ሥራ ከውጭ ሀገር ለሚመጡም ሆነ ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሆኑ የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙሃን እና የዜና ወኪሎች በነጻነት ተንቀሳቅሰው እንዲሰሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሰነዶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

14/ provide necessary support, upon request, to reporters or news agents, coming from foreign countries to Ethiopia or resident foreign media correspondents to ensure that their freedom of movement is respected; conduct registration after ensuring that all the necessary documents are presented;

፲፭/ ከኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ለብሮድካስት ባለፈቃዶች የሬዲዮ ሞገድ እንዲመደብ ያደርጋል፤

15/ allocate radio wave spectrum for broadcasting service in collaboration with the Communication Authority;

፲፮/ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጡ የሲቪል ማኅበራትን አደረጃጀት እና የፋይናንስ አያያዝ አግባብነትን ይቆጣጠራል፤

16/ in cooperation with the Agency for civil society organizations, regulate the organization, finance and operation of civil society organizations that provide a special public broadcasting services;

https://chilot.me


፲፯/ የብሮድካስት ጣቢያ የሚቋቋምበትን ሥፍራና የሽፋን ክልል ከሌሎች የሬዲዮ ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር አለመጋጨቱን አረጋግጦ ይወስናል፤

17/ determine the site and coverage of a broadcasting station upon verifying that it does not overlap with any radio communication service;

፲፰/ ለብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ እና መቀበያ የሚውሉትን መሣሪያዎች ዓይነት፣ ጥራት እና የቴክኒክ ብቃት ደረጃን እንዲሁም የማሰራጫ መሣሪያውን ጉልበት ይወስናል፤ ያሳውቃል፤

18/ determine, notify and regulate the type, quality, capacity and technical competence of transmitter and receiver equipment to be used for broadcasting services;

፲፱/ ለተለያዩ የብሮድካስት አገልግሎቶች የቴክኒክ ደረጃ ይወስናል፤ ደረጃቸውን ጠብቀው አገልግሎት መስጠታቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

19/ determine technical standard for different categories of broadcasting services; supervise and provide support to ensure that services rendered meet expected standards;

፳/ የሕዝብ ጥቅምን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ብዝሃነት ያላቸው የብሮድካስት አገልግሎት አይነቶች እድገት እንዲኖር ያስፋፋል፤ ያሳልጣል፤

20/ promote and facilitate the development of a diverse range of broadcasting services in Ethiopia in line with the public interest;

፳፩/ የመገናኛ ብዙሃን ፕሮግራሞች ሀገር በቀል ይዘት እንዲስፋፋ ያሳልጣል፤ያበረታታል፤

21/ facilitate and encourage the development of domestic content in media programs;

፳፪ የብሮድካስት አገልግሎት ደረጃዎችን ያወጣል፤ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

22/ develop standards for broadcasting services and ensure that these standards are met;

፳፫/ በብሮድካስት ኢንደስትሪ አቅም በመገንባት የሰው ሀብት እድገት እንዲኖር ያበረታታል፤

23/ encourage the development of human resources through capacity building initiatives within the broadcasting industry;

፳፬/ የብሮድካስት ዘርፉን እድገት ያስፋፋል፤

24/ promote the development of the broadcasting sector;

፳፭/ በብሮድካስት አገልግሎት አዲስ፣ ወቅታዊ እና ተገቢ መረጃና የኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እንዲውል ይሰራል፤

25/ promote the use of new, up-to-date and appropriate information and communication technologies in broadcasting;

፳፮/ ሥልጣንና ኃላፊነቱን ለመወጣት እንዳስፈላጊነቱ ከኮሚዩኒኬሽን ባለሥልጣን እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

26/ work in collaboration with the Communications Authority and with concerned bodies to discharge its functions as necessary;

https://chilot.me


፳፯/ አግባብነት ያላቸው ሕጎችና የመንግሥት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤

፳፰/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፡፡

**፯. <u>የባለሥልጣኑ ገለልተኝነትና ነፃነት</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነቱን ሲወጣ ከማንኛውም ዓይነት አግባብነት ከሌላቸውና ከተቋሙ ዓላማዎች ጋር ከማይሄዱ ፍላጎቶችና ተፅዕኖዎች ገለልተኛና ነፃ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ባለሥልጣኑ በተለይም ከመንግሥት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሚቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከንግድና ከሌሎችም ማኅበረሰባዊ ቡድኖችና ተቋማት ገለልተኛና ነፃ መሆን ይኖርበታል።

**፰. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>**

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ ሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾም ዋና ዳይሬክተርና እንደ አስፈላጊነቱ በቦርዱ የሚሾሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤ ይኖሩታል፡፡

**፱. <u>ስለቦርድ አባላት</u>**

፩/ ቦርዱ ፆታዊ ተዋፅኦን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተመርጠው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰየሙ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል፡፡

27/ participate in international meetings on matters related to media, without prejudice to the other relevant laws and government decisions; and

28/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name.

**7. <u>Impartiality and Independence of the Authority</u>**

1/ The Authority shall be independent and free from any interference and influence contrary to its objectives while exercising its powers and functions.

2/ Notwithstanding the general provision of Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall be independent and free mainly from influence from the government, political parties, the media sector it regulates, religious institutions, commercial and other social groups and institutions.

**8. <u>Organization of the Authority</u>**

The Authority shall have:

1/ a Management Board (hereinafter referred to as the “Board”);

2/ a Director General appointed by the House of Peoples’ Representatives and, as appropriate Deputy Directors Generals; and,

3/ the necessary staff.

**9. <u>Members of the Board</u>**

1/ The Board shall have nine members which are selected by considering gender composition and shall be appointed by the House of Peoples’ Representatives, upon recommendation by the Prime Minister.

https://chilot.me


፪/ የቦርድ አባላት እጩዎችን የመመልመሉና የማፅደቁ ሂደት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን ያለበት ሲሆን፤ በሂደቱም፡-

ሀ) ሕዝቡ እጩ ግለሰቦችን ለመጠቆምና በእጩዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ እድል እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤

ለ) የዚህን አዋጅ ዓላማዎችና መርሆች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የእጩዎች አመራረጥ ሂደትና የተመረጡ እጩዎች ዝርዝር በመገናኛ ብዙሃን ወይም በሌሎች ኤሌክትሮኒክ ማሰራጫዎች ታትሞ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፤ እና፤

ሐ) የእጩዎች ምልመላ የኢትዮጵያን ብዝሃነት ያማከለ ፍትሐዊ ውክልና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

2/ Members of the Board must be appointed in an open and transparent manner and, shall in the process:

a) give the public the opportunity to nominate and share their opinions of candidates;

b) publish the selection process of candidates and a shortlist of candidates via media and other electronic means of dissemination, taking into account the objectives and principles of this Proclamation; and,

c) ensure fair representation of Ethiopian diversity in the selection of candidates.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተተኪ የቦርድ እጩ አባልን በሚያቀርቡበት ሂደትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

3/ The rules in the Sub-Article (2) of this Article shall apply to the replacement nomination process of a candidate board member by the Prime Minister.

፬/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት የቦርዱ አባላት መካከል አንዱን በሰብሳቢነት ሌላኛውን ደግሞ በምክትል ሰብሳቢነት እጩ አድርገው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማሉ፡፡

4/ The Prime Minister shall nominate one of the members of the Board referred to in Sub-Article (1) as Chairperson and another member as a Deputy Chairperson and have them approved by the House of Peoples' Representatives.

፭/ ከቦርዱ አባላት መካከል፡-

ሀ) ሁለቱ ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ሁለቱ ከመገናኛ ብዙሃን እና ሁለቱ ለመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ጠቀሜታና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች፤

5/ Among the Board members,

a) two of them shall be drawn from civil society organizations, two of them from media and two of them from other institutions that have relevance to the media sector;

https://chilot.me


ለ) ሦስቱ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የተውጣጡ ይሆናሉ።

፮/ የቦርዱ አባላት ሥራቸውን ሲያከናውኑ ከፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጣልቃ ገብነት ወይም ተፅዕኖ ገለልተኛና ነፃ መሆን አለባቸው።

፯/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያለ ድምፅ የሚሳተፍ የቦርዱ ጸሐፊ ይሆናል።

## ፲. ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች

ለቦርድ አባላት የሚከፈለው ክፍያ አግባብነት ባላቸው ሕጎችና መመሪያዎች መሠረት ይወሰናል።

## ፲፩. የቦርድ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት

ማንኛውም ለቦርድ አባልነት የሚመረጥ ሰው፡-

፩/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለውና በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ኗሪ የሆነ፣

፪/ ሥራውን በተገቢው መንገድ እንዲፈፅም የሚያስችል ከዘርፉ ጋር የተገናኘ የትምህርት ዝግጅትና ብቃት ወይም ልምድ ያለው፣

፫/ መልካም ሥነ-ምግባር እና ስብዕና ያለው፣

፬/ ተግባራቱን በኃላፊነት ለመወጣት ብቃትና ፍላጎት ያለው፣

፭/ ከምርጫው ቀደም ብሎ ባሉት ፮ ወራት ውስጥ በዚህ አዋጅ ክትትልና እርምጃ በሚወሰድበት የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ጋር በተገናኘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት የሌለው፣

፮/ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም ተቀጣሪ ያልሆነ፣ እና፣

b) the other three shall be drawn from relevant government organs.

6/ Members of the Board must function independently and free from either political and economic interferences or pressures.

7/ The Director-General shall be an *ex officio* member of the Board but shall have no right to vote at any meeting of the Board.

## 10. Remuneration of Members

The remuneration fees or allowances for expenses to Board members shall be determined in accordance with the relevant laws and Directives.

## 11. Criteria for Appointing Board Members

A person will qualify to be appointed to the Board if such person-

1/ is a citizen and permanent resident of Ethiopia;

2/ possess suitable qualifications and expertise or experience in the media sector;

3/ possesses good conduct and personality;

4/ is capable and willing to discharge duties with responsibility;

5/ had no personal direct or indirect conflicting commercial interest in the sector regulated under this Proclamation in the last 6 months immediately preceding the appointment;

6/ is not a member or employee of a political party; and,

https://chilot.me


፯/ ከመንግሥታዊ የኃላፊነት ቦታ ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀሙ ያልተከሰሰና ያልተፈረደበት፣ ወይም በፍርድ ቤት የሲቪል መብቱ የተገፈፈ በመሆኑ የተነሳ ከሥራ ኃላፊነቱ ተገዶ ያልለቀቀ ወይም ያልተባረረ፣ መሆን ይኖርበታል፡፡

7/ has not been compelled to resign or been removed from government offices as a result of conviction or judicial suspension of civil rights, on account of abuse of office.

**፲፪. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ቦርዱ፡-

**12. <u>Powers and Functions of the Board</u>**

The Board shall have the following powers and functions:

፩/ የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፤

1/ oversee the implementation of this Proclamation and the activities of the Authority;

፪/ የባለሥልጣኑን የሥራ እቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይገመግማል፤

2/ review the work plan, budget and activity reports of the Authority at least twice a year;

፫/ የባለሥልጣኑን የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ያወጣል፤ የደሞዝ፣ የአበል እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፤

3/ prepare administrative and employment Directives that officials and employees of the Authority abide by; and decide on salary, allowances and other benefits;

፬/ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ፣ ግልፅ በሆነ ሂደት የባለሥልጣኑን ዋና ዳይሬክተር በመመልመል ለመንግሥት አቅርቦ ያሰይማል፤

4/ recruit and nominate to the government a candidate for a Director General of the Authority, to be appointed in accordance with the criteria under this Proclamation in an open and transparent process;

፭/ የባለሥልጣኑን ውሳኔዎች በይግባኝ ይመለከታል፡፡ አመልካቾች እና ባለፈቃዶች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች፣ ባለፈቃዶችን አስመልክቶ ከሕዝብ የቀረቡ ቅሬታዎችን እና የዚህን አዋጅ አፈጻጸም በሚመለከት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

5/ review the decisions of the Authority on appeal, examine and decide on complaints brought by applicants and licensees, examine and decide on public grievances concerning licensees and review complaints regarding decisions made in the course of implementing this Proclamation;

https://chilot.me


፮/ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በተያያዘ በዜጎችና በብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የሚቀርብለትን ማናቸውንም ቅሬታና አቤቱታ እንዲሁም ከባለሥልጣኑ የሚቀርብለትን የክትትል ውጤት በመመርመር ለቦርድ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ገለልተኛ የሆነ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በባለሥልጣኑ ሥር ያደራጃል፤ የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ መነሻ በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፤

6/ organize independent complaints hearing committee within the Authority which investigates any complaints of citizens and broadcasting service licensees related with media as well as monitoring results provided by the Authority and submit recommendations to the Board; make decisions based on the recommendations

፯/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በግልፅ በተሰጡት መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣንና ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን ያወጣል፤እና

7/ review and approve Directives prepared on the matters clearly stipulated to facilitate the implementation of this Proclamation; and

፰/ የዚህን አዋጅ አፈጻጸም በሚመለከት በሚቀርቡ በማናቸውም የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ እንደአግባብነቱ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

8/ deliberate on any policy matter pertaining to the implementation of this Proclamation, and submit for government decision, as may be appropriate.

## ፲፫. የቦርድ ውክልና

## 13. Delegation by the Board

፩/ ቦርዱ በጠቅላላው ወይም በተለየ ጉዳይ ላይ ለማንኛውም የቦርድ ኮሚቴ ወይም የቦርድ አባል፣ የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ተወካይ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲያከናውን ውክልና ለመስጠት ሊወስን ይችላል፡፡

1/ The Board may, by resolution either generally or in any particular case, delegate to any committee of the Board or to any member, officer, employee or agent of the Authority the exercise of any of the powers or the performance of any of the functions or duties of the Board under this Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ውክልና፣ መመሪያ ማውጣትን፣ ይግባኝ መመልከትን፣ ፈቃድ መስጠትና መሰረዝ፣ እና ቦርዱ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፪ በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር አያካትትም፡፡

2/ The delegation referred to under Sub-Article (1) of this Article is not applicable to the adoption of Directives, appeal, the awarding, and revocation of licenses, and the powers of the Board under Article 12 Sub Article (2) and (3) of this Proclamation.

https://chilot.me


**፲፬. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን**

፩/ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተቀመጠው ሁኔታና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተጠቀሰው ሥነ-ሥርዓት መሠረት የቦርዱ አምስት አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት ለተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

፫/ የሥራ ዘመኑ ሊጠናቀቅ ቢያንስ ፮ ወራት የቀሩት ማንኛውም የቦርድ አባል በሞት፣ በፈቃድ በመልቀቅ፣ ከኃላፊነቱ በመነሳቱና በቋሚነት ቀሪ በመሆኑ የአባላት ቁጥር የተጓደለ እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በ፫ ወር ጊዜ ውስጥ እጩ ተተኪ አባላትን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፡፡ የተተኪ አባላት የሥራ ዘመን የተተኩ የቦርድ አባላት ቀሪ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

**14. Term of Office of Board Members**

1/ The term of office of Board members shall be four years.

2/ Five members of the Board may be re-appointed for one additional term upon the recommendation of the Prime Minister, subject to the conditions set out in Article 9 Sub Article (2) and the procedure set out in Sub-Article (3) of this Article. A Board member shall not be elected for more than two terms.

3/ When any board member who had at least 6 months left in his term dies, resigns, is dismissed, or is permanently absent, the Prime Minister shall present replacement nominees to the House of Peoples' Representatives within 3 months. However, the member who fills the vacancy must hold office for the unexpired portion of the period for which the vacating member was appointed.

**፲፭. የቦርድ አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች**

፩/ ማንኛውም የቦርድ አባል የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) ለቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በጽሁፍ በማስታወቅ በፈቃዱ ሲለቅ፣

ለ) ህይወቱ ሲያልፍ፣

ሐ) ከኃላፊነቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ሲነሳ፡-

**15. Termination of Appointment**

1/ The office of the any member of the Board shall be terminated if the holder:

a) resigns from office by submitting a written notice to the Chairperson of the Board or Director General of the Authority;

b) dies;

c) is removed from office for:

https://chilot.me


(ሀ) ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ጉድለት ሲያሳይና በቂ ምርመራ ተደርጎ በአቅም ማነስ ምክንያት በቦርድ ሰብሳቢነት ወይም በቦርድ አባልነት ተግባሩ ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት እንዳልቻለ ከተረጋገጠ፤

(ለ) በአካላዊ ወይም አእምሯዊ ህመም ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ካልቻለ፤

(ሐ) ያለበቂ ምክንያት እና ሳያሳውቅ በተከታታይ አምስት ጊዜ ስብሰባ ከቀረ ወይም በዓመት ውስጥ ከተደረጉት ስብሰባዎች ከግማሽ በላይ በሚሆኑት ካልተገኘ፤እና፣

(መ) የዚህን አዋጅ የጥቅም ግጭት ድንጋጌዎች እያወቀ ጥሰት ከፈጸመ፡፡

(1) gross misconduct or inability to perform duties efficiently as a Chairperson or member of the Board, after due inquiry;

(2) physical or mental incapacity;

(3) being absent from five consecutive meetings or half of the meetings of the Authority in a year without prior notice and good cause; and,

(4) not declaring a clear breach of the rules of conflict of interest.

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ፊደል ተራ(ሐ) በተገለፀው ምክንያት አንድ አባል ከአባልነት እንዲነሳ በሰብሳቢው፣ በምክትሉ ወይም በጸሐፊው አማካኝነት ጥያቄ ሲቀርብ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አባሉ አስተያየት እንዲሰጥ እድል መስጠት ይኖርበታል፡፡

2/ The member against whom a complaint is lodged via the Chairperson, Deputy Chairperson or the secretary shall have the opportunity to be heard and forward his comments before the Board decides to terminate his appointment in accordance with Sub-Article (1) paragraph (c) of this Article.

፫/ አንድ የቦርድ አባል ከአባልነቱ ለማንሳት በቂ ምክንያቶች መሟላታቸውን ቦርዱ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ከወሰነ፣ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ አማካኝነት የውሳኔ ሀሳብ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ ከኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

3/ When the Board decides with two-third vote that all conditions to terminate membership are present, that membership shall be terminated by the decision of the House of Peoples' Representatives upon the recommendation of the Board communicated via the Board Chairperson or secretary.

https://chilot.me


**፲፮. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም ሰብሳቢው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ወይም ሦስት የቦርድ አባላት ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ ወይም የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርድ መወሰን ያለባቸው አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት በሰብሳቢው ወይም በምክትሉ አማካኝነት በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፪/ የቦርዱ ሰብሳቢ ከሰባት ቀናት አስቀድሞ የስብሰባውን ጊዜና ቦታ እንዲሁም አባላት እንዲጨምሩበት የታቀደውን የስብሰባውን አጀንዳ በመግለጽ የቦርድ ስብሳባ እንደሚካሄድ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡ በልዩ ሁኔታና በአሳማኝ ምክንያት አስቀድሞ የማስታወቂያ ጊዜው ሊያጥር ይችላል፡፡

፫/ የቦርድ ስብሰባ በቦርዱ ሰብሳቢ የሚመራ ሲሆን ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢ እንዲሁም ምክትሉ በማይኖርበት ጊዜ በሌሎች አባላት በሚመረጥ አባል ይመራል፡፡

፬/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፭/ የቦርዱ ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ያልፋሉ፤ ድምፅ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፮/ የእያንዳንዱ የቦርድ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ በፀሐፊ ሊያዝና ሊቀመጥ ይገባል፤ በስብሰባው ሰብሳቢና በፀሐፊ ተፈርሞ በቀጣይ ስብሰባ ይጸድቃል፡፡

**16. Meeting Procedure of the Board**

1/ The Board shall meet once every month. However, it may convene at any time when called by the Chairperson or by the request of three Board members, or when the Director General faces urgent issues requiring Board decisions via the Chairperson or the Deputy.

2/ The Board Chairperson shall give a seven days advance notice of board meetings, indicating the time and place of the meeting and the proposed agenda, which members may then add to. In exceptional cases, with justification, shorter notice may be provided.

3/ The Board Chairperson will chair Board meetings, or, in his absence, the Deputy Chair and, in his absence, the member selected by the other members to Chairperson.

4/ There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.

5/ Decisions of the Board shall be passed by a simple majority vote; in case of tie, the Chairperson shall have a casting vote.

6/ Minutes of each board meeting shall be taken and kept by the Secretary, and shall be approved at the next meeting of the Board and signed by the persons acting as Chairperson and secretary at that meeting.

https://chilot.me


፯/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯. <u>የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባራት</u>**

፩/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በቦርዱ ተመልምሎ በመንግሥት አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰየም ዋና ዳይሬክተር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ሊሆን ይገባል፡፡

፫/ ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተርነት የሚመረጥ ሰው ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ የሆነ መሆን ይኖርበታል፡፡

፬/ የባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ቦርዱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል፤ የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑ ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆች ተከትሎ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚጸድቅ ደንብ መሠረት መቀጠራቸውንና መተዳደራቸውን ያረጋግጣል፤

7/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of Procedures for its meetings.

**17. <u>Powers and Duties of the Director General</u>**

1/ The Director General shall be assigned by the House of Peoples' Representatives with the nomination of the government after selected by the Board.

2/ A Director General selected as per Sub-Article (1) of this Article shall meet all the criteria listed under Article 11 of this Proclamation.

3/ A person nominated to be selected as a Director General of the Authority shall be free from any political party membership.

4/ Subject to the final decision-making authority of the Board, the Director General shall be the chief executive officer of the Authority, and shall direct and administer the activities of the Authority.

5/ Without limiting the generality of Sub-Article (3) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Authority specified under Article 6 of this Proclamation;

b) ensure that the Authority's staff are hired and administered in accordance with a Regulation to be ratified by the House of Peoples' Representatives having basic principles of the Federal Civil Service Law, that will be exclusively passed by the government;

https://chilot.me


ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ መርሐ ግብርና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ያፀድቃል፤

መ) ለባለሥልጣኑ የሚመደበውን በጀት ያስተዳድራል፣ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ እና

ሰ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፮/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

፯/ የዋና ዳይሬክተሩ የሥራ ዘመን አራት አመት ሲሆን ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ሊሾም አይችልም።

## ፲፰. ስለ ባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር

፩/ የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች በዋና ዳይሬክተሩ አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሾም ምክትል ዋና ዳይሬክተር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ ሊሆን ይገባል።

፫/ ለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተርነት የሚመረጥ ሰው ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ መሆን ይኖርበታል።

c) prepare the work plan and budget of the Authority and submit to the Board for approval;

d) administer the budget allocated to the Authority and effect expenditure;

e) represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Board the activity and financial reports of the Authority; and

g) perform other duties as may be assigned to him by the Board.

6/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Authority to the extent necessary for the efficient execution of the activities of the Authority.

7/ The Director General shall be appointed for a term of four years and he cannot stay in office for more than two terms.

## 18. Deputy Directors General of the Authority

1/ Deputy Directors General of the Authority shall, upon recommendation by the Director General, be appointed by the Board.

2/ A person who is appointed as a Deputy Director General as per Sub-Article (1) of this Article shall also meet all the criteria listed under Article 11 of this Proclamation.

3/ A person who is appointed as a Deputy Director General of the Authority shall be free from any political party membership.

https://chilot.me


፬/ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

ሀ) የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ) ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት የተመደቡበትን የሥራ ዘርፍ ይመራሉ፤ ያስተባብራሉ፤ እና፣

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ፡፡

፭/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሰራል፡፡

4/ The Deputy Directors General shall:

a) assist the Director General in planning, organizing, leading and coordinating the works of the Authority

b) direct and co-ordinate sectors assigned under their supervision in accordance with the directives of the Director General; and

c) perform other activities assigned to them by the Director General.

5/ In the absence of the Director General, the Deputy Director General especially delegated shall act on behalf of the Director General.

**፲፱. <u>ስለጥቅም ግጭት</u>**

፩/ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ የቦርድ አባል፣ ወይም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቆጣጠረው ኩባንያ ላይ ቀጥተኛ የባለቤትነት ጥቅም ሊኖረው አይችልም፡፡

፪/ ከባለሥልጣኑ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ የቦርድ አባል፣ ወይም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ በራሱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፉ ሂደቶች ላይ መሳተፍ አይችልም፡-

ሀ) የራሱን የግል የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

ለ) የባለቤቱን ወይም የልጆቹን ጨምሮ የዘመድ የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

**19. <u>Conflict of Interest</u>**

1/ The Director General, the Deputy Director General, any member of the Board, or any staff employed by the Authority shall not hold direct ownership interest in any company that is subject to the jurisdiction of the Authority pursuant to this Proclamation.

2/ The Director General, the Deputy Director General, any member of the Board, or any staff employed by the Authority shall not involve in the decision-making process on any matter of the Authority that will affect:

a) his personal financial interests;

b) the financial interests of relatives including his spouse or children;

https://chilot.me


ሐ) የራሱን የንግድ አጋር የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

መ) በኦፊሰርነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በአጋርነት፣ በሠራተኝነት ወይም በባለአደራነት የሚያገለግለውን የማንኛውም ተቋም የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤ ወይም፣

ሠ) በሥራ ለተቀጠረበት ወይም ለሥራ ቅጥር በድርድር ላይ የሚገኝበትን ከማንኛውም አካል የፋይናንስ ጥቅም ጋር በሚገናኝ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲኖሩ የቦርድ አባላት፣ ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለቦርዱ፣ ሠራተኞች ደግሞ ለዋና ዳይሬክተሩ ለጥቅም ግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል ያሉትን ምክንያት የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፬/ የቦርድ አባላቱ የጥቅም ግጭት ስለመኖር አለመኖሩ መክረው አባሉ በስብሰባ እንዳይሳተፍ ሊወስኑ ይችላሉ፣ የሠራተኞችን የጥቅም ግጭት በተመለከተም ዋና ዳይሬክተሩ ይወስናል፡፡

፭/ ይህን የጥቅም ግጭት ድንጋጌ የጣሰ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ የባለሥልጣኑ የቦርድ አባል እና የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡ አባሉ የተሳተፈበት ስብሳባም የጥቅም ግጭት በተነሳበት ጉዳይ ላይ ብቻ ፈራሽና የማይጸና ይሆናል፡፡

c) the financial interests of his business partner;

d) the financial interests of any organization in which he serves as an officer, director, general partner, employee or trustee; or

e) the financial interests of any entity with whom he has an arrangement for employment or with whom he is negotiating for employment.

3/ When the conditions referred under Sub-Article (2) of this Article exist, the Director General, the Deputy Director General, members of the Board, or any employee of the Authority are obliged to fully disclose the nature of their interest to the Board or the Director General.

4/ After discussing whether conflict of interest may arise or not, the remaining Board members may decide whether the individual should be precluded from participating in meetings because of the conflict of interest. The Director General shall decide on matters regarding employees' conflicts of interests.

5/ If the Director General, the Deputy Director General, any member of the Board, or any employee of the Authority's staff fails to disclose any conflict of interest as required by this provision, he shall be relieved of his responsibility. If he is present at the venue where a meeting of the Board is held or in any manner whatsoever participates in the proceedings of the Board, the relevant decisions the Board will be null and void.

https://chilot.me


፮/ የጥቅም ግጭትን የሚተረጉምና ከጥቅም ግጭት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

6/ The Board shall enact a Directive which defines conflict of interest and related conditions.

## ፳. በጀት

## 20. Budget

፩/ የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

1/ The budget of the Authority shall be drawn from the following sources:

ሀ) በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤እና፣

a) budget allocated by the government; and

ለ) የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍን ለማሳደግና ለማጎልበት ፕሮጀክት በመቅረፅና በቦርዱ በማስፀደቅ ከሚገኙ እርዳታና ድጋፍ ምንጮች፡፡

b) from Board approved donations and grants for projects designed to develop and strengthen the media sector.

፪/ የባለሥልጣኑ የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራው አግባብነት ባለው የፌደራል የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

2/ The financial administration of the Authority shall be governed by the relevant Federal Financial Administration law.

## ፳፩. ስለሂሳብ መዛግብት

## 21. Books of Accounts

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

2/ The accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by the Auditor General.

https://chilot.me


## ክፍል ሦስት

## የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት፣ ምዝገባ እና ፈቃድ

### ፳፪. መሠረታዊ መርሆች

፩/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው በግል ወይም የሕግ ሰውነት ባለው አካል ግልፅ በሆነ መስፈርትና ያለ አድልኦ በየጊዜው ለሚወጣ ህትመት፣ ለበይነመረብ መገናኛ ብዙሃንና ለዜና አገልግሎት በመመዝገብ የምዝገባ ምስክር ወረቀትና ሕጋዊ እውቅና የማግኘት መብት አለው፡፡ ይህ የምዝገባ ሥርዓት ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ላይ የይዘት ገደብ ሊያደርግ አይገባም፡፡

፪/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል የብሮድካስት አገልግሎት በማመልከትና መስፈርቶችን በማሟላት ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡፡

፫/ የብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ፍትሐዊ፣ ግልፅና የመረጃ ብዝሃነትን የሚያስፋፋ መሆን አለበት፤ የፈቃድ መስፈርቶች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ላይ አግባብነት የሌለው ገደብ ሊፈጥሩ አይገባም፡፡

፬/ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ድንጋጌዎች መተርጎም ያለባቸው ዘርፉን በዋነኛነት መቆጣጠርን ለመከላከልና የሀሳብ ብዝሃነት እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ ነው፡፡

### ፳፫. የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት

፩/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል በየጊዜው የሚወጣ ህትመትና የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን በባለቤትነት ለማቋቋም ይችላል፡፡

## PART THREE

## MEDIA OWNERSHIP, REGISTRATION AND LICENSING

### 22. Basic Principles

1/ Every Ethiopian citizen, either privately or through a legal person, has the right to be legally recognized and get certificate of registration to establish a periodical, an online media and news service based on clear criteria and without discrimination. Such a registration system for periodicals and online media shall not impose substantive restrictions on the right to freedom of expression.

2/ Anybody that is conferred with a legal personality in accordance with Ethiopian law has the right to apply for and get a broadcasting license upon meeting the criteria.

3/ Broadcasting licensing processes shall be fair, transparent, and seek to promote diversity in broadcasting; licensing requirements shall not constitute undue infringements on the right to freedom of expression.

4/ Media ownership regulations shall only be interpreted to prevent monopoly and ensure plurality and diversity of views.

### 23. Media Ownership

1/ Ethiopian citizens either privately or through a juridical person may own periodicals and online media.

https://chilot.me


፪/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል የብሮድካስት አገልግሎት ሥራ እና የዜና አገልግሎት ድርጅት ባለቤት በመሆን ለመሥራት ይችላል፡፡

፫/ የውጪ ዜጋ ወይም ድርጅት እንዲሁም የውጭ ዜጎች ከ ፳፭ በመቶ ያልበለጠ የአክሲዮን ድርሻ የያዙበትና ኢትዮጵያውያን ቀሪውን ድርሻ የያዙበት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት በአንድ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት፣ የበይነመረብና የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅት ላይ ከ ፳፭ በመቶ ያልበለጠ የባለቤትነት ድርሻ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

፬/ በብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ድርጅት ባለቤትነት የሚሳተፉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አባላት ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይገባል።

2/ Anybody that is conferred with a legal personality in accordance with Ethiopian law may own a broadcasting service and news agency.

3/ Foreign citizens and organizations, and an Ethiopian organization where foreign citizens own less than 25 percent of the shares and remaining shares owned by citizens may own less than 25 percent of the shares of periodicals, online media and broadcasting service.

4/ Civil Society Organizations that have ownership stake in broadcasting service shall have only Ethiopian members.

**፳፬. <u>ተሻጋሪና ተደራራቢ ባለቤትነት</u>**

**24. <u>Cross-Ownership and Concentration</u>**

፩/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት አንድ የቴሌቪዥን፣ አንድ የሬዲዮ፣ አንድ ጋዜጣ፣ አንድ መጽሔትና አንድ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም ይችላል፡፡

1/ Anybody that is conferred with a legal personality in accordance with Ethiopian law may establish one television, one radio, one newspaper, one magazine and one online media.

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ ወይም የድርጅቱ ባለድርሻዎች በሌሎች መገናኛ ብዙሃን ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር የሌለው የአክስዮን ድርሻ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the organization or its shareholders may not directly or indirectly control more than the effective control threshold from the capital or shares of other media.

፫/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ሥራን ወይም የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን የሚሰራ ድርጅት ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው የህትመት

3/ Without prejudice to Sub-Articles (1) and (2), a person who directly or indirectly exercises effective control over a periodical or online media may buy shares from other periodical or online media without any limit, make acquisition and take total control over

https://chilot.me


ሥራን ወይም የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ከሚሰሩ ሌሎች ድርጅቶች ላይ ያለገደብ የአክሲዮን ድርሻ መግዛት፣ ደርጅቱን መጠቅለልና ውህደት መፍጠር ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተው ውጤታማ ቁጥጥር የሚወሰንበትና የመለኪያ ቅኝቱ የሚከናወንበት ሥነ-ሥርዓት ደንብ እስኪወጣ ድረስ ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር፣ ማንኛውም ኩባንያ ወይም ድርጅት አክስዮኖች ወይም ካፒታል ወይም እሴቶችን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በድርጅቱ ወይም በድርጅቶቹ ከ ፳፭ በመቶ በላይ የያዘ ማንኛውም ሰው ውጤታማ ቁጥጥር እንዳለው ይገመታል፡፡

፭/ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን በየሦስት ዓመቱ የመገናኛ ብዙሃንን ይዞታ እና የመገናኛ ብዙሃን የገንዘብና የገበያ እንዲሁም የባለቤትነት ይዞታን ከገበያና ከሀሳብ ጠቅላይነት አንጻር በመገምገም በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተደነገገው ገደብና የአክስዮን ድርሻ ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፮/ የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት ባለፍቃድ የሆነ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (፩) ከተቀመጠው ውጪ ተጨማሪ መገናኛ ብዙሃንን በባለቤትነት መያዝ አይችልም፡፡

**፳፭. <u>ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ አስቀድሞ በጽሁፍ ካላጸደቀው በስተቀር ፈቃድን ማከራየት፣ በሽያጭም ሆነ አግባብነት ባላቸው መንገዶች በሌላ ሰው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ማድረግና ማስተላለፍ አይቻልም ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማስተላለፍ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

another periodical or online media, or merge with another periodical or online media.

4/ The procedure for assessing effective control referred to in Sub-Articles (1) and (3) may be laid down by law but, in the absence of proof to the contrary, a person shall be regarded as exercising such control if he holds 25 percent or more of the shares or assets of the entity either directly or through any company or companies.

5/ The Authority may change the rules on ownership restrictions and the percentage of effective control referred to in Sub-Articles (1) to (4) every three years after evaluating the state of the media, the capital and financial situation of the media sector, ownership status and its impact on market concentration and monopoly of ideas.

6/ A civil society organization that has special public broadcasting service license cannot own another media save for what is provided for under Sub-Article (1) of this Article.

**25. <u>Non-Transferability of License</u>**

1/ A licensee may not be let, its control may not be assigned by sale or other appropriate means, or in any way transferred, to any other person without the prior written permission of the Authority.

2/ For the purposes of Sub-Article (1), transfer includes:

https://chilot.me


ሀ) የፈቃድ ቁጥጥር ለውጥ፤

ለ) በፈቃዱ የተሠጡትን መብቶች በፈቃደኝነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤ እና

ሐ) የፈቃድ ሁኔታው ላይ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ለመለወጥ የሚደረግ ማንኛውም ድርጊት።

a) change in control of the operator;

b) voluntary transfer of a right under the licensee to another person; and

c) any action to changes specified to constitute a transfer in the conditions of license.

፫/ ፈቃድ ለማስተላለፍ የባለሥልጣኑን ይሁንታ የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን በባለሥልጣኑ በተዘጋጀ ቅፅ አማካይነት ማቅረብ አለበት።

3/ An application for permission to transfer license shall be made to the Authority in the prescribed manner.

፬/ ባለሥልጣኑ ጥያቄውን በፅሁፍ የሚያጸድቀው፡-

ሀ) ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው የፈቃድ ዘመኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ያለው ከሆነ፤

ለ) የፈቃዱ መተላለፍ የባለቤትነት መከማቸትን የማይጨምር ከሆነ፤ እና

4/ The prior written permission of the Authority may only be granted if:

a) the acquiring party has adequate financial and technical resources to broadcast during the entire term of the license;

b) the transfer will not increase the concentration of ownership among those with licenses to broadcast more than a limited extent; and

ሐ) የፈቃዱ መተላለፍ የብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ባለፈቃዶች ብዝሃነትን የማይቀንስ ከሆነ፤ብቻ ነው።

c) the transfer will not cause a reduction of diversity in the range of media services requiring license.

፭/ ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው ፈቃድ በሚያስተላልፈው ሰው ላይ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን መብቶችና ግዴታዎች የፈቃዱ መተላለፍ ሲጸና አብረው ይተላለፋሉ።

5/ A party that acquires a license takes over the transferor's rights and obligations under this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder upon the consent of the Authority.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማስተላለፍ ውጤታማ ቁጥጥር የሌለው የአክሲዮን ለውጥን አያካትትም።

6/ The transfer referred under Sub-Article (1) of this Article is not applicable to a transfer of shares without effective control.

https://chilot.me


**፳፮. በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ሥራ ምዝገባ**

፩/ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ሥራ ለመሥራት የሚከተሉትን መረጃዎች በማሟላት ለባለሥልጣኑ ሕጋዊ እውቅና እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡-

ሀ) የመስራች ሥምና አድራሻ፤

ለ) የባለቤትነት ሁኔታ፤

ሐ) የዜግነት ሁኔታ፤

መ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ሠ) የዋና አዘጋጅ ሥምና አድራሻ፤ እና፣

ረ) የንግድ ፈቃድ ወይም ዋና ምዝገባ፡፡

፪/ ሥርጭቱ በአንድ ክልል ውስጥ የሆነ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት በሚመለከተው የክልል አካል በመመዝገብ ሕጋዊ እውቅና እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡ ምዝገባ የሚያከናውኑ የክልል አካላት ነፃና ገለልተኛ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ መሟላት ያለበትን መስፈርት መሟላቱን አረጋግጦ የምዝገባ ጥያቄ በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ምዝገባውን በማከናወን የእውቅና ምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በ፴ ቀናት ውስጥ የእውቅና የምስክር ወረቀት ካልሰጠ አመልካቹ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

፭/ ለምዝገባ ያመለከተው ግለሰብ ወይም ድርጅት መስፈርቱን አሟልቶ ማመልከቻ ካስገባ ፴ ቀን ካለፈው የእውቅና የምስክር ወረቀት እስከሚሰጠው መጠበቅ ሳያስፈልገው ወደ ህትመትና ሥርጭት መግባት ይችላል፡፡

**26. Registration of Periodical**

1/ Any Ethiopian citizen who desires to publish a periodical shall obtain a certificate of registration and legal recognition from the Authority by submitting the following information:

a) name (s) and address (es) of the founder (s);

b) ownership condition;

c) nationality condition;

d) tax payer identification number;

e) name and address of the Editor-in-Chief; and

f) trade license or main registration.

2/ A periodical the distribution of which is restricted to one regional state shall obtain a certificate of registration and legal recognition from the relevant regional body. The registering bodies in each region shall be free and independent.

3/ The Authority ,by making sure that the criteria are met, shall issue certificate of registration and legal recognition within 30 days of request to a person seeking to establish a periodical.

4/ Legal recognition is presumed if certificate of registration is not issued after 30 days of the application.

5/ A periodical shall wait for response and can start publication and distribution after 30 days if a certificate of registration has not been issued to the applicant but the Authority has obtained the application meeting all the required conditions.

https://chilot.me


፮/ በ፴ ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ የአመልካቹን ማመልከቻ ተመልክቶ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው አመልካቹ ሊያሟላ የሚገባውን መረጃ ካለቀረበ ወይም በየጊዜው ለሚወጣው ህትመት የሰጠው ሥም አስቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፯/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ሥራን ማሳተም፡-

ሀ) አስቀድሞ በሕጋዊ መንገድ ለተመዘገበ ማንኛውም ድርጅት እንቅስቃሴዎች አስፈላጊነቱ ተፈጥሯዊ ከሆነ፤ ወይም፣

ለ) መንግሥታዊ አካል ዓላማውን ለማራመድ ወይም በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ካስፈለገው፤ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

6/ Registration may only be refused within 30 days only if the applicant does not provide the necessary information to the Authority or if the name the applicant want to use for the periodical is already taken.

7/ Where publishing a periodical is either:

a) inherent in the activities of an already legally registered organization; or

b) requirement to a government body to fulfil duties given to it by law; it shall, for the purpose of Sub-Article (1),be deemed to have obtained the requisite legal recognition.

**፳፯. <u>የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን ምዝገባ</u>**

**27. <u>Registration of Online Media</u>**

፩/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው በግል ወይም በድርጅት የበይነመረብ የመገናኛ ብዙሃን ለማቋቋም የሚከተሉትን በማሟላት ባለሥልጣኑ እንዲመዘግበው ማመልከት ይችላል፡-

ሀ) የተቋሙ ሥምና አድራሻ፡- የባለቤቱ ወይም የድርጅቱ ስም፣ የቢሮ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤

ለ) የባለቤትነት ሁኔታ፤

ሐ) የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃኑ ሥምና አድራሻ፡-

(፩) ዶሜይን ሥም፤

(፪) የዶሜይን ሥም ባለቤትነት ማረጋገጫ፤

1/ Ethiopian citizens either privately or through juridical person may request for an online media registration after fulfilling the following conditions:

a) Name and address of entity: Name of owner/company, office telephone number, and email address (s);

b) Ownership conditions;

c) Name and address of online media owner/company

(1) Domain name;

(2) Proof of ownership of domain name;

https://chilot.me


(፫) የቢሮ ስልክ ቁጥር፤

(፬) የኢሜል አድራሻ፤

(፭) የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪው ድርጅት የኢሜል አድራሻ፤ እና

(፮) የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪው ድርጅት የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ፤

ሙ) የዜግነት ሁኔታ፤

ሠ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

ረ) የዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ፤ እና፣

ሰ) የንግድ ፈቃድ ወይም ዋና ምዝገባ።

፪/ ባለሥልጣኑ የምዝገባ ጥያቄው በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ምዝገባ በማከናወን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። አመልካቹ መሟላት ያለበትን መስፈርት አሟልቶ ቀርቦ በ፴ ቀናት ውስጥ የእውቅና የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል።

፫/ ለምዝገባ ያመለከተ የበይነ-መረብ የመገናኛ ብዙሃን ድርጅት መስፈርቱን አሟልቶ ማመልከቻ ካስገባ ፴ ቀናት ካለፈው የእውቅና የምስክር ወረቀት እስከሚሰጠው መጠበቅ ሳያስፈልገው ወደ ሥራ መግባት ይችላል፤

፬/ ባለሥልጣኑ በ፴ ቀናት ውስጥ ማመልከቻ ተመልክቶ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው አመልካቹ ሊያሟላ የሚገባውን መረጃ ካለቀረበ ወይም ለበይነ-መረብ የመገናኛ ብዙሃኑ የሰጠው ሥም አስቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ ነው።

(3) Office phone number;

(4) Email address;

(5) Email address of the internet service provider; and

(6) Social media address of the internet service provider.

d) Nationality condition;

e) Tax payer identification number;

f) Name and address of the Editor-in-Chief; and

g) Trade license or main registration.

2/ The Authority has to complete the registration and issue certificate of registration within 30 days of request by the person seeking online media registration. Legal recognition is presumed if certificate of registration is not issued after 30 days of the application.

3/ Online media can start operations after 30 days if a certificate of registration has not been issued while the Authority has obtained the application meeting all the required conditions.

4/ Registration may only be refused within 30 days only if the applicant does not provide the necessary information to the Authority or if the name the applicant want to use for the online media is already taken.

https://chilot.me


**፳፰. <u>የመገናኛ ብዙሃን መረጃና መዝገብ</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉ፣ በቀጥታና በቋሚነት ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡-

ሀ) የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ስምና ሙሉ አድራሻ፤

ለ) የፖስታና የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻን ጨምሮ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ዝርዝር መረጃ፤ እና

ሐ) የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ድርጅት ተወካዮች ሥምና አድራሻ፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በመዝገቡ ላይ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢ የሕግ ሰዎችን የሚመዘግበው፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፮ ወይም ፳፯ መሠረት የተመዘገቡ ከሆነና፣

ለ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፱ እና ፴፩ መሠረት ፈቃድ የተሰጣቸው ከሆነ ነው፡፡

፫/ የባለሥልጣኑ መዝገብ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆን ይኖርበታል፣ የሚይዘው መረጃ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፮ (፩)፣ ፳፯ (፩)፣ ፴፫ እና ፴፮ የተመለከቱትን ብቻ ነው፡፡

**፳፱. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶች</u>**

የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

፩/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ አናሎግ የሬዲዮ የብሮድካስት አገልግሎት፤

**28. <u>Media Information and Registry</u>**

1/ The Authority shall ensure that media entities make at least the following information easily, directly and permanently accessible to the recipients of a service:

a) The name or trade name and geographical address of the media service provider;

b) Details of the media service provider, including postal address, telephone number, email address and website; and

c) names and address of the representatives of the media service provider organization.

2/ The Authority shall establish a registry of those legal persons which:

a) are registered pursuant to Articles 26 or 27 ; and

b) hold the type of license referred to in Articles 29 and 31.

3/ The registry shall be maintained with the help of automatic data processing. It may contain only such information as is referred to in Sub-Article (1) of Article 26 and Sub-Article (1) of Article 27 , and Articles 33 and 36.

**29. <u>Means of Broadcasting Service Transmission</u>**

Means of broadcasting service transmission shall be the following:

1/ terrestrial analogue radio broadcasting service;

https://chilot.me


፪/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ አናሎግ የቴሌቪዥን የብሮድካስት አገልግሎት፤

፫/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ አናሎግ ነፃ የብሮድካስት አገልግሎት፤

፬/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ አናሎግ የክፍያ የብሮድካስት አገልግሎት፤

፭/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ ዲጂታል የሬዲዮ የብሮድካስት አገልግሎት፤

፮/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ ዲጂታል የቴሌቪዥን የብሮድካስት አገልግሎት፤

፯/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ ዲጂታል ነፃ የብሮድካስት አገልግሎት፤

፰/ ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ ዲጂታል የክፍያ የብሮድካስት አገልግሎት፤

፱/ ነፃ የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲/ የክፍያ የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፩/ በተፈለገ ጊዜ ተደራሽ የሚሆን የሳተላይት የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፪/ የክፍያ የኬብል የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፫/ በተፈለገ ጊዜ ተደራሽ የሚሆን የኬብል የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፬/ ነፃ የኢንተርኔት የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፭/ የክፍያ የኢንተርኔት የብሮድካስት አገልግሎት፤

፲፮/ በተፈለገ ጊዜ ተደራሽ የሚሆን የኢንተርኔት የብሮድካስት አገልግሎት፤ እና

፲፯/ ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶች።

2/ terrestrial analogue television broadcasting service;

3/ terrestrial analogue free broadcasting service;

4/ terrestrial analogue subscription broadcasting service;

5/ terrestrial digital radio broadcasting service;

6/ terrestrial digital television broadcasting service;

7/ terrestrial digital free broadcasting service;

8/ terrestrial digital subscription broadcasting service;

9/ satellite free broadcasting service;

10/ satellite subscription broadcasting service;

11/ satellite on demand broadcasting service;

12/ cable subscription broadcasting service;

13/ cable on demand broadcasting service;

14/ internet free broadcasting service;

15/ internet subscription broadcasting service;

16/ internet on demand broadcasting service; and

17/ any other class of license prescribed by the Authority.

https://chilot.me


**፴. <u>ያለፈቃድ የብሮድካስት አገልግሎት መስጠት ስለመከልከሉ</u>**

ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችን ተጠቅሞ በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

**፴፩. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ዓይነቶች</u>**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ለ) ልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤

ሐ) የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፤ እና

መ) የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቦርድ በማፀደቅ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ በሌሎች ባለፈቃዶች ያልተሸፈነ ወይም ትኩረት ያልተሠጠበት የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ለሚያመለክት አመልካች ልዩ የንግድ ወይም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፴፪. <u>የባለሥልጣኑ ተጨማሪ የፈቃድ መስፈርት የማውጣት ወይም ያሉት ላይ ማብራሪያ የመስጠት ሥልጣን</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢ ምክክር ካደረገና አስቀድሞ ካሳወቀ በኋላ በብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች መካከል ግልፅ ልዩነት ለመፍጠር በአንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተጨማሪ የፈቃድ መስፈርት ሊያወጣ ወይም በዚህ አዋጅ ተለይተው የተደነገጉት ላይ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**30. <u>Prohibition of Provision of Service without License</u>**

No person may undertake broadcasting service by using means of broadcasting service transmission without obtaining a broadcasting license from the Authority or by using a suspended or revoked license.

**31. <u>Categories of Broadcasting Service Licenses</u>**

1/ The categories of broadcasting service license shall be the following:

a) public service broadcasting license,

b) special public service broadcasting license,

c) commercial broadcasting service license, and

d) community broadcasting service license.

2/ When it finds it necessary, the Authority may grant special public, commercial or community broadcasting service license upon the approval of the Board to an applicant who applies to transmit a broadcasting service whose program focuses on special issues not covered or given enough attention by existing broadcasting services.

**32. <u>Authority's Power of Determination of Additional Criteria or Clarification of Existing Criteria</u>**

1/ The Authority may, after properly consulting and notifying the relevant stakeholders, determine additional criteria pursuant to Sub-Article (2) of Article 37 or clarify the criteria specified in this Proclamation for the purpose of distinguishing between categories of broadcasting services.

https://chilot.me


፪/ ባለሥልጣኑ ለቴሌቪዥንና ለሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት የተለያዩ መስፈርቶች ወይም ማብራሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ለብሮድካስት አገልግሎት የተለያዩ መስፈርቶች ወይም ማብራሪያዎች ሲያወጣ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይገባል፡-

ሀ) አገልግሎቱ የሚሸፍነው አካባቢ፤

ለ) የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችና ሊጠቀሙ የሚችሉ ሰዎች ቁጥር፤ እና

ሐ) በቴክኖሎጂና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ የተነሳ የአገልግሎቱን ተደራሽነት የሚወስኑ ምክንያቶች፣ አገልግሎቱ የሚቆይበት ዘመንና የአገልግሎቱ መርሀ ግብር የጊዜ ሰሌዳ፣ የአገልግሎት ተጠቃሚዎቹና የሚቀርበው ፕሮግራም ባህሪ፣ የፕሮግራሙ ማኅበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖዎች፣ እና መሰል ጉዳዮች፡፡

**፴፫. <u>የሬዲዮ ሞገድን በመጠቀም የሚሰራጭ የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾችን ስለመጋበዝ</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት፣ የፈቃድ ጥያቄ አቅራቢው በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ያሟላና በብቃትና የቴክኒክ ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ መሰረት መስፈርቱን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ያቀረበው የማሰራጫ መንገድ የሬዲዮ ሞገድን የሚጠቀም በመሆኑ የተገደበ ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱን በ፴ ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡ አመልካቹ በተጠቀሰው

2/ Different criteria or clarifications may be determined or made for radio services and television services.

3/ The Authority shall take the following directions into account when making determinations and clarifications in relation to broadcasting services:

a) the geographic coverage of those services;

b) the number of persons who receive or are able to receive those services; and,

c) whether the accessibility of those services is restricted because of technology, high cost of equipment required to receive the services, the duration and frequency of those services, the nature of the audience to which the services are targeted and the nature of the programs being provided by those services, the social and cultural impact of those programs and the like.

**33. <u>Invitation to Applicants to Commercial Broadcasting Service License Using Radio Spectrum</u>**

1/ If the license requested is not using the limited radio spectrum, the Authority shall grant the broadcasting service license within 30 days when the applicant fulfils all the requirements under this Proclamation and meets the technical and capacity criteria required for the license as specified in the Directive. The applicant may apply to the Director General to get a response within 15 days if the license is not

https://chilot.me


ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ካልተሰጠው ለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በማመልከት በ፲፭ ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ በተጠቀሰው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ አመልካቹ በ፴ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማመልከት ይችላል፡፡ ቦርዱ ውሳኔውን በ፴ ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

issued within the specified period. The applicant may petition to the Board within 30 days if the Director General fails to respond within the specified period.The Board shall give its decision within 30 days.

፪/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች በዚህ አዋጅ መሠረት በተለያየ ደረጃ እንዲሞሉ የሚጠበቅባቸውን ቅጾች ባለሥልጣኑ በድረ-ገጹ ተደራሽ እንዲሆንና እንዲሞላ በማድረግ ወረቀት የመጠቀም ሂደትን የሚያቃልል አማራጭ መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ይህን ማድረግ ያልቻሉ አመልካቾች በአካል አገልግሎቱን ያገኛሉ፡፡

2/ The Authority shall create options and ensure that the application processes for a broadcasting service license pursuant to this Proclamation are done online by making the forms that the applicants are required to fill available in its website to reduce the paper-processing burden. However, the applicants who are unable to use this option for different reasons shall access the service in person.

፫/ ውስን የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሲኖር ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾችን በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ፣ አግባብነት ባለውና ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን በሚገለጽ ማስታወቂያ የመጋበዝ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ በየበጀት አመቱ ዝግጁ የሆኑ የብሮድካስት የሬዲዮ ሞገዶችን መረጃ ከሚመለከተው ተቋም ይወስዳል፡፡

3/ When broadcasting service license that uses radio spectrum are available, the Authority shall invite applicants by a notice published on the Authority's website, in appropriate wide circulation newspapers or by other media. The Authority shall receive information on the available broadcasting service licenses that use radio spectrum from the relevant organ every budget year.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚወጣው ማስታወቂያ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

4/ The notice to be published pursuant to Sub-Article (3) of this Article shall contain the following information:

ሀ) ፈቃድ ለመስጠት የታሰበውን የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነት፤

a) the category of broadcasting service for which the license is intended to be issued;

ለ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል ወይም አካባቢ፤

b) the geographic area to be coverd by the license.

https://chilot.me


ሐ) ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፤

መ) የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች፤

ሠ) አንኳር የፎርማት ግዴታዎች፤

ረ) ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

ሰ) ፈቃድ የሚሰጥባቸው መስፈርቶች፤

ሸ) የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜና ቦታ፤ እና፣

ቀ) የማመልከቻና የፈቃድ ክፍያ መጠን።

c) the available radio frequency spectrum;

d) terms and conditions of license;

e) major format obligations;

f) the length of the license period;

g) the criteria upon which the license will be awarded;

h) the time and place of submission of the application, and

i) the amount of application and license fees.

፭/ ፍትሐዊና አወዳዳሪ ሂደት ለማረጋገጥ ለንግድ ብሮድካስት የሚመደብ አዲስ ውስን የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሲኖር ሁልጊዜም ቢሆን በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ፣ አግባብነት ባለውና ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያ ሊወጣበት ይገባል።

5/ When new broadcasting service license that use radio spectrum is available, it should always be openly advertised on the Authority's website, in appropriate wide circulation newspaper or by other media in order to ensure a fair and competitive process.

፮/ በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚወጣው ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፤

6/ A person who intends to obtain a license for broadcasting service shall fill and submit the license application form prepared by the Authority within the time specified in the notice published in accordance with this Article.

፯/ የብሮድካስት ፈቃድ አመልካቾች የሥራ እቅድ ሰነዶቻቸውን ለማቅረብ ለሬድዮ ፫ ወር፣ ለቴሌቪዥን አመልካቾች ደግሞ የ፱ ወር ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

7/ Potential applicants for a radio and a television license shall be given 3 months and 9 months time, respectively to prepare their work plan documentations.

https://chilot.me


**፴፬. ስለሕዝብ ወይም ስለማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ**

ባለሥልጣኑ ለሕዝብ ወይም ለማሕበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች ያለ ውድድር በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**34. Public or Community Broadcasting Service License**

The Authority may grant license to public or community broadcasting license applicants any time without competition.

**፴፭. የፈቃድ ማመልከቻ ሂደት**

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ የፈቃድ አመልካቾች ሊሞሉት የሚገባ የማመልከቻ ቅጽ ያዘጋጃል፤

፪/ በማስታወቂያ ለተደረገው ጥሪ ምላሽ ሊሰጡ ለሚችሉ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ ይሰጣል፤ እና

፫/ ማመልከቻዎችን ለመገምገም አስፈላጊ ነው የሚለውን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ አመልካቾችን ይጠይቃል፡፡

**35. Application Process for License**

1/ The Authority shall issue an application form which must be completed by all the applicants.

2/ Any potential applicant who responds to the advertisement shall be given identical and sufficient information by the Authority to ensure that all applicants are treated fairly

3/ The Authority may require the applicant to provide such additional information as it may consider necessary in considering the application.

**፴፮. የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው የገለጻቸው እንዲሁም በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በፈቃዱ ውስጥ የተመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች የፈቃዱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ የፈቃዱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች እንደ ፈቃድ ዓይነት ልዩነት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

፪/ ፈቃድን በተመለከተ ምንም ዓይነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ባለሥልጣኑ ፈቃዱ ላይ ተፈጻሚ ሊያደርግ ያዘጋጃቸውን የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች አመልካቹ እንዲያገኛቸውና አስተያየቱን የመግለፅ እድል እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

**36. Terms and Conditions for License**

1/ The detailed issues stated on the application of any licensee who applies to obtain a license as well as those prescribed in the license pursuant to this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder shall be deemed terms and conditions of license. The terms and conditions may vary according to the different types of licenses.

2/ Before a decision has been made regarding a license, the applicant is to be given an opportunity to access, and express an opinion on, the conditions that the Authority intends to apply to the license.

https://chilot.me


፫/ ዜጎች ባለሥልጣኑ በተቀበላቸው ማመልከቻዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጡና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ፈቃዱን ለመስጠት ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ ጠቃሚ መረጃዎች እንዲሰጡ እድል እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3/ Members of the public shall be given the opportunity to comment and make representations on applications received by the Authority and provide valuable additional information and issues to consider when awarding a license.

፬/ ማንኛውም የብሮድካስት ፈቃድ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካትታል፡-

4/ Any broadcasting license term and condition should cover the following fundamental issues:

ሀ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል ወይም አካባቢ፤

a) the geographic area to be covered by the license,

ለ) የቴክኒክ መስፈርቶች መዘርዝር፤

b) technical specifications,

ሐ) የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ሥርጭት የሚጀምርበት ጊዜና ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፤

c) the date by which the service should commence broadcasting, and for how long the license will be in force,

መ) የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፤

d) license renewal conditions,

ሠ) አዲስ ፈቃድ ለመስጠት፣ ተፈጻሚ ከሆነ ለሬዲዮ ሞገድና ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ለመሸፈን በየዓመቱ የሚከፈል ክፍያ መጠን፤

e) a fee payable on the award of a new license, the spectrum fee, when applicable, and fees paid annually to cover on-going regulatory costs,

ረ) የፕሮግራም ፎርማት ግዴታዎች፤

f) program format conditions,

ሰ) የፕሮግራም የይዘት ደረጃዎች፤

g) content standards in programming,

ሸ) የፈቃድ ሁኔታዎች ሲጣሱ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች፤

h) what sanctions the Authority can apply for noncompliance with the conditions,

ቀ) ባለሥልጣኑ በመደበኛነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው የመረጃ ዓይነቶች፤

i) certain pieces of information that the Authority requires either on a regular basis, or from time to time,

በ) ፈቃድ የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች፤ እና፣

j) the terms upon which the license may be amended, and

ተ) የሚከተሉትን ጨምሮ በክፍያም ሆነ ያለ ክፍያ የብሮድካስት አገልግሎት ለሚጠቀሙ ደንበኞች ፍላጎቶች የሚደረጉ ጥበቃዎች፡-

k) the protection of the interests of the subscribers and end-users of broadcasting service, including, but not limited to:

https://chilot.me


(፩) ቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚያዙበትና እልባት የሚያገኙበት መንገድ፤

(፪) ለቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚሰጡ ተገቢ መፍትሔዎችና እርምቶች፤

(፫) ስለ አገልግሎትና የተጠቃሚዎች መብት የሚሰጥ መረጃ ግልፅነት፤ እና፣

(፬) ባለሥልጣኑ የተጠቃሚዎችን መብት ለመጠበቅ ውጤታማ ነው ብሎ የወሰነው ሌላ ማንኛውም ጉዳይ።

(1) the handling and resolution of complaints and disputes;

(2) the provision of appropriate remedies and redress in respect of such complaints and disputes;

(3) the transparency of information about services and the rights of subscribers; and

(4) any other matter the Authority determines to be necessary in order to achieve the effective protection of subscribers.

**፴፯. <u>የፈቃድ መስጫ መስፈርቶች</u>**

፩/ አመልካች ለፈቃድ አመልካቾች የወጣው ማስታወቂያ መስፈርቶችን፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተደነገጉትን መስፈርቶች ሲያሟላ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የአመልካቾችን ብቃት ለመመዘን የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት የሚያወጣ ሲሆን፣ መስፈርቱ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ መሆን አለበት፡-

ሀ) ከብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ እድገቶች ጋር በተያያዘ ሊሰጥ ከታሰበው አገልግሎት የሚጠበቅ የቴክኒክ ጥራትና አመልካቹ በፕሮጀክት ሀሳብ-ሥራው የዘረዘራቸው መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

**37. <u>Criteria for Issuance of License</u>**

1/ A broadcasting service license may be issued when the applicant meets the conditions in the call for license applications, the criteria provided under this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder.

2/ The Authority shall issue detail criteria that enable it to evaluate the capability of applicants. The detail criteria to be set by the Authority shall include the following:

a) expected technical quality of the proposed service and the capability of equipment and technologies listed in the applicant's project proposal to render the service, having regard to developments in broadcasting technology;

https://chilot.me


ለ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣ ድርጅታዊ ብቃት፣ የሥራ ልምድና ሙያዊ እውቀት፤

b) suitability, organizational capacity, experience and expertise of the applicant in as far as carrying out such broadcast service is concerned;

ሐ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ፣ አስተማማኝነትና ሥራውን ለማስኬድ ያለው ዝግጁነት፤

c) the applicant's financial capacity and means, reliability and adequacy to run the service and business record, if any;

መ) በአመልካቹ ፕሮጀክት ሀሳብ-ሥራ የተዘረዘሩ የፕሮግራሞች መርሐ-ግብርና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፤ እና፣

d) the program schedule listed in the applicant's project proposal and social needs covered by the programs; and

ሠ) አመልካቹ ለአገልግሎቱ የመደበው የሥርጭት ጊዜ፡፡

e) the transmission time allocated for the service.

**፴፰. <u>በፈቃድ ላይ የሚሠጥ ሕዝባዊ አስተያየት</u>**

**38. <u>Public Hearing for License</u>**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ለመገምገም ባለሥልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ሊጠራ ይችላል፡፡

1/ An application for broadcasting service license may be subject to a public hearing convened by the Authority for the purpose of considering the application.

፪/ ባለሥልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ለመጥራት ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ ማውጣት አለበት፡፡ ማመልከቻ ለመገምገም ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ መጥራት ከፍ ያለ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ከሆነ ባለሥልጣኑ መድረኩን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

2/ The requirements for the public hearing shall be prescribed by the Authority. The Authority shall convene a public hearing to consider an application where there is significant public interest in holding a hearing on an application.

፫/ ህዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበት ቦታ የብሮድካስት አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ ወይም ጣቢያው በሚገኝበት ክልል የሚገኝ መሆን አለበት፡፡

3/ The public hearing shall be held at a location within the area to be covered by the broadcasting service or in the district in which the station is located.

https://chilot.me


**፴፱. ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ**

ባለሥልጣኑ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበን ሰው ማመልከቻው ዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልገው ውድቅ በማድረግ በጽሁፍ እንዲያውቀው የሚያደረገው አመልካቹ፡-

፩/ ወደፊት የሚሰጥ ብድር መኖሩን ወይም የፋይናንስ ወይም የካፒታል አቅሙንና ምንጩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ ካላቀረበ፤

፪/ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፤ ወይም፣

፫/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵ መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል ከሆነ ነው፡፡

**39. Unacceptable Application**

Any broadcasting service license application may be rejected and notified in writing without going into detail screening, if the applicant:

1/ fails to produce evidence to ascertain the availability of potential loan or its financial capacity and source of financing;

2/ fails to produce detail project proposal; or

3/ is a body that may not be entitled to a license as provided for under Article 40 of this Proclamation.

**፵. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ስለማይሰጣቸው ሰዎች</u>**

፩/ የሚከተሉት አካላት ምንም አይነት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

ሀ) ማንኛውም፡-

(፩) የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተፈጥሮ ያለው ድርጅት፤

(፪) የፖለቲካ ፓርቲው ወይም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ባለድርሻ የሆነበት ድርጅት፤ ወይም

(፫) የፖለቲካ ፓርቲ አመራር በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል የሆነበት ድርጅት።

**40. <u>Persons not to be Issued with Broadcasting Service License</u>**

1/ The following persons shall not be issued with any categories of broadcasting service licenses:

a) any

(1) political party, movement, organization, body or alliance which is of a party- political nature;

(2) organization of which a political organization is a shareholder with effective control or a member of a political organization's top leadership is a shareholder with effective control; or

(3) organization of which member of its management, at any level, is in the leadership of a political party.

https://chilot.me


ለ) በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም ከፖለቲካ መብቶቹ የታገደ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው ባለቤት ወይም ከባለቤቶቹ አንዱ ወይም የበላይ አመራር አካል አባል የሆነበት ድርጅት፡፡

፪/ የሚከተሉት ሰዎች ውስን በሆነ የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ አይሰጣቸውም፡-

ሀ) በውጭ ሀገር ዜጎች የተቋቋመ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ወይም የውጪ ሀገር ዜጋ ከካፒታሉ ከ፳፭ በመቶ በላይ የአክስዮን ባለድርሻ የሆነበት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል፤ ወይም

ለ) የሃይማኖት ተቋማት፡፡

፫/ የሚከተሉት ሰዎች ውስን የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ የማይጠቀሙ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ዓይነቶች ሊሰጣቸው ይችላል፡-

ሀ) በውጭ ሀገር ዜጎች የተቋቋመ ድርጅት ወይም የውጪ ሀገር ዜጎች በካፒታሉ ላይ ከ፳፭ በመቶ በታች የአክስዮን ባለድርሻ የሆኑበት የሕግ ሰውነት ያለው አካል፤ ወይም

ለ) የሃይማኖት ተቋማት፡፡

፬/ በልዩ ሕግ ካልተፈቀደ በስተቀር የመንግሥት ተቋማት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ሊሰጣቸው አይችልም፡፡

b) an organization of which its owner or any of its owners or a member of its management is deprived of exercising his civil or political rights or has fully or partially lost his legal capacity by a decision of court.

2/ The following persons shall not be issued with broadcasting service license using the limited radio spectrum:

a) a body that is conferred with a legal personality and established by foreign nationals or an organization conferred with a legal personality under Ethiopian law where more than 25 percent of its capital shares are owned by foreign nationals; or

b) religious institutions registered by the relevant organ.

3/ The following persons may be issued with broadcasting service licenses not using the limited radio spectrum:

a) a body that is conferred with a legal personality established by Ethiopian nationals and less than 25 percent of its capital shares are owned by foreign organizations or foreign nationals; or

b) religious institutions registered by the relevant organ.

4/ Unless otherwise permitted under exceptional considerations by law, governmental institutions can not be issued broadcasting service licenses.

https://chilot.me


**፵፩. <u>የውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ የማቅረብ ሂደት</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበን የፈቃድ ማመልከቻ ከገመገመ በኋላ የወሰነውን ውሳኔ፣ ለውሳኔው ያደረሱ ምክንያቶችንና ፈቃዱ ላይ ተግባራዊ የሚሆኑ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎችን፡-

ሀ) ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፣ እንዲሁም

ለ) በድረ-ገጹ፣ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

፪/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች የፈቃዱ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች በመቀበል በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ስምምነት በመፈረምና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ በመፈጸም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ በመስጠት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚከተሉትን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) በጽሁፍ በቀረበው ማመልከቻ የተገኘውን መረጃ በመገምገም፣ ሕዝባዊ አስተያየት የማይሰጥ ከሆነ በፅሁፍ የቀረበለትን ማንኛውም ማስረጃ፣

ለ) በሕዝባዊ አስተያየት መድረኩና ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት የቀረቡትን የቃልና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ጨምሮ የሕዝባዊ አስተያየቱን ውጤት፣ እና

ሐ) ከሕዝባዊ አስተያየት ውጭ የተገኘ ማንኛውም ዓይነት መረጃ፡፡

**41. <u>Decision Making and Complaints Handling Procedure</u>**

1/ After considering any application for a license made in terms of this Proclamation, the Authority shall:

a) notify the applicant of its decision, the reasons for that decision and any license terms and conditions applicable; and

b) publish such information in the its website, newspaper with wider circulation or other media outlets.

2/ Where the application is accepted, the applicant shall be issued with a certificate of license, upon signing terms and conditions of a license agreement, prepared by the Authority and payment of the required license fee.

3/ The Authority shall consider the following in its decisions on the grant of a license:

a) an assessment of information from the written application and any written presentations made to it where a public hearing is not held;

b) the proceedings of the public hearing including oral and written presentations made at the hearing or soon after the hearing; and

c) other information solicited or made available to it outside the public hearing

https://chilot.me


፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመር በአንቀጽ ፴፯ የተመለከቱ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ወይም ተቀባይነት የሌለው ከሆነ በአንቀጽ ፴፱ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል።

4/ The Authority shall, upon examining the application submitted to it pursuant to Sub-Article (6) of Article 33 of this Proclamation, consider the fulfillment of the criteria provided under Article 37 or decide in accordance with Article 39 if it is rejected.

፭/ ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውል የሬዲዮ ሞገድ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ከማረጋገጥ አንፃር ለብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተለየ ትኩረትሊያደርግ ይችላል፦

5/ To ensure the efficient utilization of frequencies to broadcasting, when allocating licenses to broadcasting service applicant, the Authority shall take particular care to the following:

ሀ) የተለያዩ ፍላጎቶችና ምርጫዎችን መሳብ የሚችሉ የተለያዩ የብሮድካስት አገልግሎቶች መኖር፤

a) the existence of different broadcasting services that appeal to a variety of interests and tastes;

ለ) የሀገር አቀፍ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የብሮድካስት አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ሚዛን እንዲኖራቸው የተወሰዱ ውሳኔዎች፤

b) measures on proportionately balancing national, regional and local broadcasting services;

ሐ) እርስ በእርስ ባላቸው ግንኙነት ነፃና ገለልተኛ የሆኑ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ቁጥር፤ እና

c) number of broadcasting service licensees that remain independent of each other; and

መ) የሬዲዮ ሞገድ ለሚጠቀሙ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዶች በአመልካቹ ሊሰጥ የታሰበው የብሮድካስት አገልግሎት እንዲጀምር አገልግሎቱ እንዲሸፍን ከታሰበው የፈቃድ አካባቢ ፍላጎት መኖሩ።

d) with regard to broadcasting services using radio spectrum, the demand for the proposed broadcasting service within the proposed licensed area.

፮/ ባለሥልጣኑ በሕዝብ ጥቅም ምክንያት የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳያገኝ ከወሰነ ውሳኔውን ለአመልካቹ በ፲፬ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

6/ Where the application is rejected by the Authority because of public interest, the decision thereof shall be communicated to the applicant in writing within 14 days.

https://chilot.me


፯/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለቦርዱ በ፴ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል።

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት የቀረበለትን ቅሬታ ተመልክቶ ቦርዱ ውሳኔ ይሰጣል። በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፱/ አመልካቹ የቦርዱ ውሳኔ ቅጂ እንዲሰጠው ቦርዱን ከጠየቀ ቦርዱ በ፲፬ የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ የውሳኔውን ቅጂ መስጠት አለበት፡፡

**፵፪. <u>የብሮድካስት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን</u>**

፩/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የሬዲዮ ሞገድን በመጠቀም የሚሰራጭ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለ፲ ዓመት ጸንቶ ይቆያል፡፡

፪/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የሬዲዮ ሞገድን በመጠቀም የሚሰራጭ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራጭ ሲሆን ለ፲ ዓመት፤

ለ) የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለ፰ ዓመት፤

ሐ) የሥርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ከሆነ ለ፮ ዓመት፤

መ) የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ ፲ ዓመት፤ እና፤

ሠ) የአጭር ጊዜ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ ለ፩ ዓመት፡፡

7/ Any applicant who has been denied a license in accordance with Sub-Article (6) of this Article may appeal to the Board within 30 days.

8/ The Board shall review and decide on the appeal submitted to it in accordance with Sub-Article (7) of this Article. Any applicant aggrieved by the decision of the Board may appeal directly to the Federal High Court.

9/ The Board shall give a copy of its decision to the applicant within 14 working days.

**42. <u>Validity Period of Broadcasting License</u>**

1/ A television broadcasting service license that uses radio wave granted for the first time shall be valid for 10 years.

2/ The validity period of a radio broadcasting service license that uses radio wave granted for the first time shall be as follows:

a) where the transmission is at the national level, for 10 years;

b) where the transmission is limited to a regional state, for 8 years;

c) where the transmission is limited to local level, for 6 years;

d) where the transmission is community broadcasting servic, for 10 years; and

e) for short-term community broadcasting service 1 year.

https://chilot.me


**፵፫. የብሮድካስት ፈቃድን ስለማሳደስ**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ የተወሰነው የፈቃድ ዘመን የጊዜ ገደብ ከማለቁ ከአንድ ዓመት ባልበለጠና ከስድስት ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማደሻ ቅጽ ሞልቶ የዕድሳት ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀው የፈቃድ ማደሻ ማመልከቻ ቅጽ ሊያካትታቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል የማመልከቻው ቅርጽና ይዘት እንዲሁም ማመልከቻውን ለማስገባት የሚያስፈልገው ጊዜ ሊገለጽ ይገባል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በፈቃድ ማደስ ማመልከቻው ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ፈቃዱ እንደጸና ይቆያል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፵፪ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

፭/ ባለሥልጣኑ አሳማኝ ምክንያት ካለው ምክንያቶቹን በመዘርዘር ፈቃዱን በማሻሻል በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፬) የተመለከተውን የታደሠ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበትን ዘመን ሊያሳጥር ይችላል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ ክልከላው የሕዝብ ጥቅምን ያስከብራል ካላለ በስተቀር የብሮድካስት ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻን ይቀበላል፡፡

**43. Renewal of Broadcasting License**

1/ The broadcasting service licensee shall renew the license not earlier than one year and not later than six months before the expiry of the validity period of the license determined pursuant to Article 42 of this Proclamation by filling and submitting the license renewal application form prepared by the Authority.

2/ The form prescribed by the Authority in accordance with of Sub-Article (1) of this Article must specify, among other things, the form and content of applications for renewal and the time period for applying for renewal.

3/ A license shall continue to subsist until the Authority has taken the decision as regards the application for the renewal of the license.

4/ The validity period for a license renewed pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be in accordance with Article 42 of this Proclamation.

5/ The Authority may renew the license of a broadcasting service for a period less than provided in Sub-Article (4) of this Article for stated reasons.

6/ The authority shall grant an application for renewal unless it is in the public interest to refuse the same.

https://chilot.me


፯/ ባለሥልጣኑ የባለፈቃዱን ፈቃድ የማደስ ጥያቄ ሲያስተናግድ ባለፈቃዱ በሥራ ላይ ባለው ፈቃድ የተዘረዘሩትን የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በወጡ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተጣለበትን ግዴታዎች የማክበር የኋላ ታሪክና የተወሰዱበትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

፰/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ላለማደስ የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ካመነ የውሳኔውን ምክንያቶች ለባለፈቃዱ በመግለጽ በ፲፬ ቀናት ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ በውሳኔው ላይ አስተያየት እንዲሰጥና ተቃውሞ ካለው የጽሁፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ይሰጣል፡፡ ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት የባለፈቃዱን ምላሽ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡

፱/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ላለማደስ ሀሳብ ካለው ከሦስት ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ ለባለፈቃዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲/ በባለሥልጣኑ ፈቃድ ያልታደሰለት አመልካች ለቦርድ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ በቦርዱ ውሳኔ ቅር ከተሰኘም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**፵፬. <u>የብሮድካስት ፈቃድን ስለማሻሻል</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ ከባለፈቃዱ ጋር በመመካከር የብሮድካስት ፈቃድን በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊያሻሽል ይችላል፡-

ሀ) የፈቃዱን የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች በአጠቃላይ ለተመሳሳይ ፈቃዶች ከተጣለው የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ጋር የተጣጣመ ለማድረግ

7/ Before the Authority renews a license, it shall take into account records if the applicant has consistently complied with the terms, conditions and obligations of its license under this Proclamation, applicable Regulations and Directive issued hereunder and any administrative measure taken,

8/ Where the Authority decides not to grant the renewal for license, it shall state the grounds for its contemplated refusal of the renewal and give the licensee the opportunity to present its views and submit a written statement of objections to the Authority within 14 days. The Authority shall take into account the views and the written statement of the licensee before taking its final decision.

9/ The Authority shall give the licensee advance notice of not less three months of its intention not to renew the license.

10/ Appeal may be made to the Board if the applicant is denied renewal of a license. The applicant can appeal to the Federal High Court if aggrieved by the decision of the Board.

**44. <u>Amendment of Broadcasting License</u>**

1/ The Authority may amend a license under the following conditions after consultation with the licensee:

a) to make the terms and conditions of the license consistent with the terms and conditions being imposed generally in respect of all licenses of the same type;

https://chilot.me


ለ) በባለፈቃዶች መካከል ፍትሐዊ የንግድ ውድድር ለማረጋገጥ ሲባል፤

ሐ) የሌሎች ባለፈቃዶችን ጥቅምና ፍላጎት እንዲሁም በአጠቃላይ የሕዝብ ጥቅምን የማይጎዳ እስከሆነ ድረስ ባለፈቃዱ ማሻሻያውን ከጠየቀ፤

መ) በቴክኖሎጂ ለውጥ አስገዳጅነት የተነሳ፤

ሠ) ማሻሻያው በገበያ ላይ ከተለወጡ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ እና፤

ረ) በአዋጁ ላይ ለውጥ ከተደረገና በባለሥልጣኑና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣኑ ላይ የተጣለው ዓለም አቀፍ ግዴታ አፈፃፀም ማሻሻያ የሚጠይቅ ከሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከባለፈቃዱ ጋር የሚያደርገው መመካከር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን ለማሻሻል ሲወስን ለብሮድካስት ባለፈቃዱ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማስታወቂያው የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡-

ሀ) የማሻሻያውን ዝርዝር፤

ለ) ለማሻሻል ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፤ እና፤

ሐ) ማሻሻያው ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ፡፡

፫/ የብሮድካስት ባለፈቃዱ በማሻሻያው ላይ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል፡፡

b) for the purpose of ensuring fair competition between licensees;

c) to the extent requested by the licensee provided it will not prejudice the interests of other licensees and the overall public interest;

d) to the extent necessitated by technological change;

e) if the amendment relates to changed circumstances in the market; and

f) change in legislation and the implementation of an international obligation by the Authority and the Communications Service Authority require the amendment.

2/ Notwithstanding the consultation with the licensee stated under Sub-Article (1 ) of this Article, the Authority shall give prior notice to the licensee stating, among others:

a) the particulars of the amendment;

b) detailed reasons for the amendment; and

c) the date on which the amendment is to take effect.

3/ The licensee shall be given sufficient opportunity to make representations on the amendment to the Authority.

https://chilot.me


፬/ ማሻሻያው የተፈለገው ከሬዲዮ ሞገድ አስተዳደር ጋር በተገናኘ ከሆነ በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጁ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

4/ Where the amendment is required for reasons relating to the management of the radio spectrum the amendment shall be effected in accordance with the Communications Service Proclamation.

፭/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ እንደአግባብነቱ፡-

5/ A broadcasting service licensee shall, as appropriate, obtain an expansion license from the Authority when it intends to:

ሀ) ተጨማሪ ሥርጭት ለማካሔድ የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ ወይም የማሠራጫ መሣሪያውን አቅም ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግ ከፈለገ፤

a) upgrade the capacity of the station to provide additional transmission or to upgrade the capacity of the transmitter to make technological changes;

ለ) የማሠራጫ መሣሪያውን ጉልበት ከተፈቀደው መጠን ለመለወጥ ወይም ቦታ ለመቀየር ከፈለገ፤

b) change the capacity of the transmitter from the permitted level or change the place;

ሐ) የአንቴናውን ዓይነትና የአንቴና ተሸካሚ ምሰሶውን ርዝመት ለመለወጥ ወይም ቦታ ለመቀየር ከፈለገ፤ ወይም፣

c) change the type and the length of the pillar holding the antenna or place of the antenna or;

መ) ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ ለማግኘት ከፈለገ፤

d) obtain additional radio wave.

ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፮/ ባለፈቃዱ ቀደም ብሎ ፈቃድ በወሰደበት የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራው የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ላይ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ለማድረግ ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፭) የተጠቀሰውን መስፈርት ለማሟላት ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

6/ When a broadcasting service licensee requests an expansion license for the radio wave license issued earlier for technological expansion and to comply the criteria under Sub-Article (5) of this Article, the Authority shall ascertain:

ሀ) የተመረጠው ማስፋፊያ ቦታ ለታቀደው አገልግሎት ተስማሚ መሆኑን፤

a) the efficiency of the proposed expansion area for intended service;

https://chilot.me


ለ) የብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መሣሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ዕቅድ ጋር መጣጣማቸውን፤

ሐ) የሌላ የመገናኛ አገልግሎት መገልገያ መሣሪያዎችን ሥራ የማያውክ መሆኑን፤

መ) ፈቃድ በተጠየቀበት አካባቢ የተመዘገበ የሬዲዮ ሞገድ መኖር አለመኖሩን፤

ሠ) የማስፋፊያ ፈቃድ የተጠየቀበት ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት አለመያዙን ወይም ለሌላ አገልግሎት አለመፈለጉን፤ እና፣

ረ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ ህብረተሰብ ፍላጎት፡፡

b) that the equipment proposed is compatible with the expansion plan of the service to expand broadcasting service;

c) that it does not interfere with the operations of other communication service rendering equipment;

d) the existence or non-existence of registered radio wave in the area where the license is requested;

e) the requested additional wave is not held by another broadcasting service or not required for other service; and

f) the demand of the community of the area for which the license is requested.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም ፈቃድ ለማስፋፋት የቀረበን ጥያቄ አጠቃላይ የሕዝብ ጥያቄን ግምት ውስጥ በማስገባት የመከልከል ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

7/ Notwithstanding Sub-Article (6) of this Article, the Authority shall have the discretion to refuse an expansion request relating to use of the spectrum, taking into account the overall public interest.

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የማስፋፊያ ፈቃድ የተሰጠው ባለፈቃድ መሣሪያው የሚተከልበትን ቦታ ከአስፈላጊ ዝርዝር መረጃ ጋር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

8/ A licensee who has been granted an expansion license in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall notify to the Authority the place where the equipment is to be fixed with the necessary detailed information.

https://chilot.me


**፵፭. <u>የማሳወቅ ግዴታ</u>**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ለውጦች ሲያደርግ ለውጦችን ባደረገ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመር፤

ለ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲቋረጥ፤

ሐ) የመርሀ ግብር ለውጥና የሥርጭት ሰዓት ለውጥ ሲያደርግ፤

መ) የጣቢያው ሥም፣ ምልክትና አድራሻ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፤ እና፣

ሠ) የጣቢያው ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ወይም የፕሮግራም ኃላፊ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፡፡

፪/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ከማድረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

ሀ) የጣቢያውንም ሆነ የጣቢያውን የአክስዮን ባለድርሻዎች የአክስዮን ድርሻ መጠን ለመጨመር፣ ለመቀነስ፣ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ፣ ሌላ የመገናኛ ብዙሃን የንግድ ማኅበርን ለመግዛት፣ ለመዋሀድ ወይም መሰል ለውጥ ለማድረግ ወይም

ለ) የውጪ ሀገር ብሮድካስት አገልግሎቶች የሚያሠራጩትን ፕሮግራም ተቀብሎ ለማሠራጨት፡፡

**45. <u>Duty to Notify</u>**

1/ A broadcasting service licensee shall notify as appropriate the following changes to the Authority in writing within 14 days:

a) commencement of transmission service;

b) termination of transmitting its service;

c) change of program schedule and transmission hour;

d) change of name of the station, logo and address; and

e) change of manager or member of board or the person who is responsible to the program.

2/ A broadcasting service licensee shall notify in writing to the Authority and obtain the Authority's prior approval before making the proposed changes on the following:

a) to increase or decrease the amount of a share of the station and the station's shareholders or to transfer to other person or to buy other mass media business organization or to merge as well as to make other similar change; and

b) to receive and transmit program transmitted by foreign broadcasters.

https://chilot.me


፫/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የኦዲት ሪፖርት፣ የጣቢያውን የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ እና ዓመታዊ የወጪና ገቢ ሪፖርት የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በ፫ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ A broadcasting service licensee shall submit and notify performance report that shows the general activity, audit report, document of financial sources and yearly financial report of the organization, to the Authority within 3 months at the end of the budget year.

፬/ የጣቢያውን የአየር ሰዓት ለሌላ ተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢ የሚያስተላልፍ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢዎች ተገቢ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥና የስም ዝርዝርና የሚያሠራጩትን የፕሮግራም ዓይነት የበጀት አመቱ በተጀመረ በ፫ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ Broadcasting service licensee who transfers the station's air time to other associate program producer shall ensure that the associate program producers have issued business license and shall submit and notify to the Authority list of names and types of program they disseminated, within 3 months at the beginning of the budget year.

፭) ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በ፴ ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

5/ The Board shall give its decision within 30 days.

**፵፮. <u>የፈቃድ፣ ዓመታዊ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ</u>**

**46. <u>License, Annual Fee and License Renewal Fee</u>**

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ክፍያ፣ ተፈጻሚ ከሆነ የሬዲዮ ሞገድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

1/ Any broadcasting service licensee shall pay license fee, the spectrum fee, when applicable, annual fee and license renewal fee, when the license is renewed.

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈል እንዲሁም ሌላ ለባለሥልጣኑ መከፈል ያለበትን የክፍያ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ እያጠና በመንግሥት ያስወስናል፡፡

2/ The Authority shall, as may be necessary, review from time to time and submit for decision to the Government the amount of fee to be paid pursuant to Sub-Article (1) of this Article and other fees to be paid to it.

https://chilot.me


፫/ ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያው የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ በ፷ ቀናት ውስጥ ይከፈላል። የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ፷ ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ፭ በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፈላል፤ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከአመታዊ ክፍያ ወይም የፈቃድ ማደሻ ክፍያ ፶ በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

## ክፍል አራት

## የመገናኛ ብዙሃን መብቶች እና ግዴታዎች

### ፵፯. መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ መገናኛ ብዙሃን ሕጋዊ ግዴታቸውን በማክበር ኃላፊነት በተሞላው ሁኔታ ሙያው በሚያስፈልገው ብቃትና በከፍተኛ ሥነ-ምግባር ተግባራቸውን እንዲያከናውኑና፣ ነፃና ዘርፈ ብዙ የሆነ፣ ሠፊና የተለያየ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበት ምህዳር በመፍጠር ለሀሳብ ልውውጥ መነልበት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

፪/ መገናኛ ብዙሃን ከመንግሥት፣ ከፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ወይም ሀት-መቶቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን ለማመንጨትና ለማሰራጨት ወሳኝ የሆኑ ቁሳዊ እና መሰረተ-ልማታዊ ሀብቶችን ከሚቆጣጠሩ አካላት ተጽእኖዎች ነፃ ይሆናሉ።

፫/ በብሮድካስት ሥርጭት ላይ የይዘት ግዴታዎች የሚጣሉት መገናኛ ብዙሃን የሕዝብን ሠላምና ደህንነት ባከበረ መልኩ በኃላፊነት መንቀሳቀሳቸውን ለማረጋገጥ፣ ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ እንዲሰሩ ለማድረግ፣ ህብረተሰቡን ከጉዳት ለመከላከል እና ሸማቾችን ከሚያሳስቱ ማስታወቂያዎችና ካልተገቡ የንግድ ውድድሮች ለመጠበቅ ብቻ ነው።

3/ The annual fee and the license renewal fee, when the license is renewed, shall be paid within 60 days after the end of the fiscal year. Where it is not paid within 60 days after the end of the fiscal year, a penalty of 5 percent shall be imposed for the delay of each month; provided, however, that the total amount of penalty shall not exceed 50 percent of the annual fee or the license renewal fee.

## PART FOUR

## RIGHTS AND OBLIGATIONS OF MEDIA

### 47. Basic Principles

1/ Media organizations are expected to discharge their legal duty in a responsible manner with high ethical standards and professionalism. They are expected to encourage free flow of ideas, entertain diversity of views and contribute to strengthen dialogue among the public.

2/ The media should be free from governmental, political or economic influence; and influence of those in control of the material and infrastructure resources essential for the production and dissemination of its publications and services.

3/ Regulation of the content of broadcast material should only be conducted to ensure that the media operates with responsibility by respecting public peace and security, to work with impartiality, to protect the public from harm and consumers from misleading advertisement and unfair trade competition.

https://chilot.me


፬/ የይዘት ግዴታዎች በማንኛውም ሁኔታ ሀሳብን በነጻነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነጻነት በቅድመ-ምርመራ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፣ ትክክለኛ መረጃ የማስተላለፍ እና ጥራት ያለው ፕሮግራም የመሥራት መብት ላይ ያልተገባ ተፅእኖ በማይፈጥር መልኩ ይተገበራሉ።

4/ The content regulation shall be implemented by ensuring freedom of expression and freedom of the press is not endangered by censorship and without endangering the right of the media to publish accurate information and quality news and programs.

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የመገናኛ ብዙሃን መብቶች

## SUB-SECTION ONE

## RIGHTS OF THE MEDIA

**፵፰. የመገናኛ ብዙሃን መብቶች**

**48. Rights of Media**

፩/ ማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ተግባሩን ለመወጣት፡-

1/ Any media, in order to discharge its function, has the right to:

ሀ) ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፤

(a) gather, receive and disseminate news or information;

ለ) በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብ፤

(b) express opinions and engage in critical reporting on issues;

ሐ) ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን፣ መሣሪያዎችን የመጠቀም፤

(c) use information technology and methods;

መ) የተለያዩ ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሂደት የመሳተፍ፤ እና፣

(d) gather, record public opinion using different methods; and

ሠ) በመገናኛ ብዙሃን ነጻነት ላይ የሚከሰት ጣልቃ ገብነት፣ ተፅዕኖ፣ ጥቃትንና የደህንነት ሥጋትን ጨምሮ ሕገ መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሠራር ከተፈፀመበት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ፤

(e) bring charges or complaints to the Federal High Court when there is an action that interferes with, contravenes, or influences its constitutionally guaranteed freedom of the press, or threatens its wellbeing.

መብት አለው።

፪/ መገናኛ ብዙሃን በመረጡት ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አላቸው።

2/ The media have the right to form legal associations as they deem fit.

https://chilot.me


፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱት መብቶች ለጋዜጠኞችም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3/ Rights stated above under Sub-Article (1) and (2) of this Articles are applicable *ipso facto mutates mutandis* to journalists who are part of the media.

**፵፱. <u>የምንጭ ጥበቃ</u>**

**49. <u>Source Protection</u>**

1/ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ለመገናኛ ብዙሃን ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

1/ Journalists may not be forced to reveal a source that provided information on a confidential basis.

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ሁኔታዎች የመረጃ ምንጭ እንዲገለጽ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡-

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the court may order the disclosure of a confidential source when:

ሀ) የተፈጸመ ከባድ ወንጀል ላይ ክስ ለመመስረት ወይም መከላከያ ለማቅረብ፣ ወይም በሀገር ጸጥታ ላይ ግልጽና ድርስ አደጋን ለመከላከል ወሳኝ የመረጃ ምንጭ ሲሆን፣ እና፣

a) it is a critical information necessary for prosecution or defence of a serious crime or for preventing clear and imminent danger to the national security; and

ለ) ክስ ለመመስረት ወይም መከላከያ ለማቅረብ አስፈላጊና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ከሆነ እና ድርስ የሆነውን አደጋ ለመከላከል ሌላ አማራጭ የሌለ ሲሆን፡፡

b) there is no alternative means of obtaining the information needed to prosecute or defend the case, or avert the imminent danger.

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
## <u>የመገናኛ ብዙሃን ግዴታዎች</u>

## <u>SUB-SECTION TWO</u>
## <u>OBLIGATIONS OF THE MEDIA</u>

**፶. <u>የእርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ</u>**

**50. <u>Obligation to Reply or to Correct</u>**

፩/ በመገናኛ ብዙሃን በቀረበ የፍሬ ነገር ዘገባ መልካም ሥሙና ክብሩ በሐሰት ወይም በአሉታዊ ጎኑ ተጎዳብኝ ያለ ማንኛውም ሰው ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ ጊዜ በግልፅ ያለ ክፍያ እርማት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

1/ Anyone whose name and reputation has been affected due to false and inaccurate information reported in the media, have the right to demand correction free of charge, in a proportional manner and at the same time in the media outlet in which the information appeared.

https://chilot.me


፪/ ማንኛውም ግለሰብ የራሱን መልካም ሥምና ክብር የመከላከል የሲቪል መብትን የጣሰ መረጃ በመገናኛ ብዙሃን ከቀረበ ግለሰቡ ለዚህ መረጃ የሰጠው ምላሽ ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ ጊዜ በግልፅ ያለ ክፍያ እንዲካተት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2/ Anyone whose name and reputation has been affected due to information reported by violating applicant's civil right, has a right to reply in proportional manner free of charge in the media outlet in which the information appeared.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተደነገጉት መብቶች ተግባራዊ የሚደረጉት በሚከተሉት ደንቦች አማካይነት ነው፡-

3/ The rights provided in Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall be implemented based on the following rules:

ሀ) በየጊዜው የሚወጣ ህትመት በሚሆንበት ጊዜ፣ ከህትመት በተጨማሪ በድረ-ገጹና በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ከሆነ እርማቱ ወይም ምላሹ በደረሰ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ፣ ዕለታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ፫ ቀናት ውስጥ፣ ሳምንታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ ዓይነት ህትመት ከሆነ በቀጣዩ እትም መውጣት አለበት፡፡

a) In the case of periodicals, the correction or reply shall be posted within 24 hours of receipt if it is disseminated via internet, inserted within 3 days for daily periodical, within 14 days in case of a weekly periodical and, in other publications, in the next issue.

ለ) የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮ ፕሮግራም በሚሆንበት ጊዜ እርማቱ ወይም ምላሹ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፭ ቀናት ውስጥ መተላለፍ አለበት፡፡

b) In the case of a broadcast program, the correction or reply shall be transmitted within 5 days of receipt.

ሐ) እርማቱ ወይም ምላሹ ተጨማሪ ምርመራ እንደሚያስፈልገው በመገናኛ ብዙሃኑ ኤዲቶሪያል ቡድን ከታመነበት ቅሬታው በቀረበ ከ፫ ሳምንት በማይበልጥ ጊዜ ምላሹንም ሆነ እርምቱን በዝግጅቱ ወይም በህትመቱ መውጣት አለበት። ይህን ውሳኔ የመገናኛ ብዙሃኑ በኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ወይም በደብዳቤ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

c) If the editorial team of the media is convinced that additional investigation is required, the periodical or the broadcast program shall entertain the correction or reply not more than 3 weeks after receiving the complaint. The media shall notify the applicant of this decision via electronic communication or a letter.

https://chilot.me


ሠ) መገናኛ ብዙሃኑ ለማስተባበያ የሚቀርበው መልስ ከዘገባው ጋር የተያያዘ፣ ትክክል፣ ተመጣጣኝና ሕጋዊ ይዘት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ መልስ የመስጠት መብት በፍሬ ሀሳብ እውነተኛነት ላይ የተረጋገጠን ዘገባ በሐሰት ለማስተባበል ሊውል አይገባም፡፡

d) Media shall ensure that the reply is related to the report, accurate, proportional and lawful. The right to reply should not be used to negate an accurate reporting ascertainable with facts by providing false responses.

ሠ) ዘገባው የተሰራጨው ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት ከሆነ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ብቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የ፫ ቀን የጊዜ ገደብ ወደ ፷፬ ሰዓት፣ የ፲፬ ቀኑ ገደብ ደግሞ ወደ ፯ ቀን ዝቅ ተደርጎ ይተገበራል፡፡

e) During election periods, only on issues in relation to election, notwithstanding to Sub-Article 3 paragraph (a) and (b) of this Article, the 3 days time limit shall be presumed to be reduced to 24 hours and the 14 days to 7 days to transmit the reply or correction.

ረ) እርማቱ ወይም ምላሹ እንዲወጣ ከተጠየቀ በኋላ ህትመቱ ከተቋረጠ ጥያቄው የቀረበለት መገናኛ ብዙሃን ክፍያዉን በመሸፈን በሌላ ተመሳሳይ መገናኛ ብዙሃን ላይ እርማቱን ወይም ምላሹን እንዲያወጣ ይደረጋል፡፡

f) If the publication of the periodical is terminated after the demand to publish the reply or correction has been made, the media organization shall cover the cost to publish it in a similar media outlet.

ሰ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ሠ) ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው ምላሹ ለመገናኛ ብዙሃኑ የደረሰው ምላሹ የሚወጣበት ህትመት ወይም ፕሮግራም ለመታተም ከመላኩ ወይም በአየር ከመለቀቁ ፷፬ ሰዓታት ቀደም ብሎ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከ፷፬ ሰዓታት ቀደም ብሎ ካልደረሰ በቀጣዩ ህትመት ወይም ፕሮግራም መካተት ይኖርበታል፡፡

g) Sub-Article (3) paragraph (e) of this Article shall only be enforced when the correction or reply is submitted to the media outlet at least 24 hours prior to that edition being sent for printing or program being aired. The correction or reply shall be inserted in the next edition or program when it is not submitted within the 24 hours limit.

https://chilot.me


ሸ) በየጊዜው ለሚወጣ ህትመት፣ ለብሮድካስት አገልግሎትና ለበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን እርማት ወይም መልስ የሚስተናገደው በተመሳሳይ አምድ ወይም ፕሮግራም፣ ገጽ ወይም የአየር ሰዓት መሆን ይኖርበታል፡፡

h) Correction or reply shall be inserted in the same section or program, or page or segment of the periodical, the broadcasting service and the online media where the information that gave rise to the claim was published or aired.

፬/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው የህትመቱ ወይም የፕሮግራሙ አዘጋጅ ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ለማመልከት ይችላል፡፡

4/ Where a media outlet refuses to honour a claimed right of correction or reply, the person affected may appeal to the court to order the media outlet editor or a person responsible to the program to transmit the correction or reply.

፭/ ማመልከቻው የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን በ፲ ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም በምርጫ ወቅት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው በቀረበለት በ፳፬ ሰዓት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

5/ The court shall make its decision within 10 days from application. If the claim is during an election period, the court shall make a decision on the issue within 24 hours from application.

፮/ ኃላፊ የሆነው ሰው በክፉ ልቦና በመነሳሳት መልሱን ለማውጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን ከተረዳ ፍርድ ቤቱ የገንዘብ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

6/ The court may fine the responsible editor for refusing to insert the correction or reply where the editor acted in bad faith.

፯/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፪ሺ፶፬ የተመለከቱትን ከተፈጻሚነት አያስቀሩም፡፡

7/ The provisions of this Article shall not affect the enforcement of Article 2049 of the Civil Code.

፰/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ቅሬታ የፈጠረው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መልስ የማውጣት ጥያቄው ለመገናኛ ብዙሃን የቀረበ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

8/ Provisions under Sub-Article (1) to (6) of this Article shall only be enforced when the demand for reply or correction are made within 3 months from the dissemination of the media outlet which gave rise to the claim.

https://chilot.me


**፶፩. ስለ ዋና አዘጋጅ**

፩/ በየጊዜው ለሚታተሙ ህትመቶች ወይም በይነመረብ መገናኛ ብዙሃን በዋና አዘጋጅነት የሚሾም ሰው ሥልጣን የሚታተሙትን ህትመቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይታተም ማድረግን ያካትታል፡፡ ይህን ሥልጣን የሚገድቡ ማናቸውም አሠራሮች ወይም ስምምነቶች ውድቅና ፈራሽ ናቸው፡፡

፪/ በየጊዜው የሚታተመው ህትመት ወይም በይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ዋና አዘጋጅ በማንኛውም ምክንያት የተሟላ የሕግ ችሎታውን ካጣ የተሟላ የሕግ ችሎታ ያለው ዋና አዘጋጅ መሾም ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሾመው ዋና አዘጋጅ በየጊዜው የሚታተመው ህትመት ውጤቶች ወይም በይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ይዘት ላይ ሙሉ የሕግ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ ታትሞ እንዳይወጣ የማድረግ ሥልጣን አለው፡፡

፬/ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች ወይም ውጤታማ ቁጥጥር ያለው የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ሰዎች ዋና አዘጋጅ ሆነው መሾም አይችሉም፡፡

፭/ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን የዋና አዘጋጁንና የዋና ሥራ አስኪያጁን ሥምና የሚገኙበትን ዝርዝር አድራሻ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ የእነዚህ ሰዎች ሥምና የቢሮ ስልክና የኢሜል አድራሻቸውን ጨምሮ የሚገኙበት ዝርዝር አድራሻ፣ ከበይነመረብ መገናኛ ብዙሃኑ ጋር የሚገናኙ የማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን አድራሻ መገኛ ማስፈንጠሪያ በድረ-ገጹ የአድራሻ መጠቆሚያ ወይም ስለ ድርጅቱ መሠረታዊ መረጃ በሚሰጥበት ክፍል መካተት ይኖርበታል፡፡

**51. Editor-in-Chief**

1/ The editor-in-chief of a periodical or an online media has a mandate to supervise and determine content of the periodical and ensure nothing is printed against his will. Any practice or agreement that restricts this power shall be null and void.

2/ Where the editor-in-chief of a periodical or an online media does not, for any reason, have legal capacity, another editor-in-chief who has full legal capacity shall be appointed.

3/ An editor-in-chief appointed in accordance with Sub-Article (2) of this Article, shall have a full legal responsibility for the content of the publication and has the power to ensure nothing is printed against his will notwithstanding to Sub-Article (1) of this Article.

4/ Owners or shareholders with effective control of a media organization shall not be appointed as editor-in-chief.

5/ Online media shall notify the name and contact details of the editor-in-chief, head of program, whenever available, and general manager to the Authority. The names and contact addresses including office telephone and email address of these persons, links to all social media accounts associated with the online media shall be included in the “Contacts” or “About Us” section of its website.

https://chilot.me


**፶፪. የፕሮግራም እና የዜና ኃላፊ የማሳወቅ ግዴታ**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሚያሠራጨው ፕሮግራም እና ዜና ኃላፊ አድርጎ የሚመድበውን ሰው ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የመገናኛ ብዙሃኑን ኃላፊነት አያስቀረውም፡፡

**52. Obligation to Notify a Person in Charge of Program and News**

1/ A broadcasting service licensee shall notify to the Authority the person assigned to be in charge of programs and news.

2/ The provision of Sub-Article (1) of this Article shall not relieve the licensee of its responsibility.

**፶፫. በህትመትና የብሮድካስት ሥርጭት ላይ የሚገለፁ መረጃዎች**

፩/ ማንኛውም ዓይነት በየጊዜው የሚወጣ ህትመት በእያንዳንዱ እትም ላይ የአሳታሚውን፣ የአታሚውን፣ የዋና አዘጋጁን ስምና አድራሻ፣ የህትመቱን ቅፅ፣ ቁጥር፣ ህትመቱ የሚወጣበትን ጊዜ እና ታትሞ የወጣበትን ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት እና ዋጋ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የፕሮግራም ሥርጭት መጀመሪያና ማብቂያ ላይ፡-

ሀ) የጣቢያውን ሥምና የተላለፈበትን ቀን፣ እና

ለ) የፕሮግራሙን ኃላፊ ወይም አዘጋጅ ሥም መግለጽ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቴሌቪዥን አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የፕሮግራም ሥርጭት የጣቢያውን ምልክት ማካተት አለበት፡፡

**53. Information on Periodicals, Broadcast Transmission and Online Media**

1/ Periodicals, under each publication, shall carry the name and address of the publisher, the printer and the editor in chief and; the volume and number of the periodical periodicity, date of publication and price in a discernible manner.

2/ Any broadcasting service licensee shall, at the beginning and end of each program, state:

a) the name of the station and date of transmission; and

b) the name of the director or producer of the program.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, a television service licensee shall, include the station's logo in each transmission of programs.

https://chilot.me


፬/ የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን በድረ-ገጹ "ስለ እኛ" በሚለው ክፍል ወይም ስለ ድርጅቱ መሠረታዊ መረጃ በሚሰጥበት ተመሳሳይ ሥያሜ ባለው ክፍል የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃኑን ሥም፣ የባለቤቱን ፕሮፋይል፣ የዋና አዘጋጁንና የዋና ሥራ አስኪያጁን ወይም ባለቤት ሥምና የሚገኙበትን ዝርዝር አድራሻ፣ የተመረጠው የቀንና ሰዓት አይነት፣ መረጃው የተሻሻለ ከሆነ መረጃው የተሻሻለበት ቀን ወይም ጊዜ መገለጽ አለበት፡፡

4/ In a section "About Us" or a similarly-named section of the website of the online media providing basic information about the organization, name of online media, owner or owning company profile, names and contact address of editor-in-chief and general manager or owner, the type of date or time chosen, and the date or time of the update of the page where this information is placed.

፭/ ተጠቃሚውን አሳታፊ የሚያደርግ ይዘትን የሚይዘው የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃኑ ድረ-ገጽ ላይ የይዘቱ ጸሐፊ፣ አሳታሚውና ሌሎች በይዘቱ አመንጪነት የተሳተፉ ሰዎች፣ በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ይዘቱ ድረ-ገጹ ላይ የተጫነበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምሕረት እና ሰዓት፣ እንዲሁም ይዘቱ የተሻሻለበት ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምሕረት እና ሰዓት፣ መገለጽ አለበት፡፡

5/ In the website of the online media containing all dynamic and interactive content, name of the author and publisher and other person(s) who participated in the production of the content, date or time, according to Ethiopian calendar, of posting, and date or time, according to Ethiopian calendar, of any updates made to the content must be included.

፮/ የመገናኛ ብዙሃን ይሄንን ግዴታ በማይወጡ ጊዜ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ፲፬ ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን እንዲወጡና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁት ሊያስገድድ ይችላል፡፡

6/ When the media fail to comply with these requirements, the Authority may give them a written warning to take corrective measure within 14 days and demand to be informed of the changes made.

## ፶፬. ያለ ክፍያ ስለሚሰጡ ቅጅዎች

## 54. Gratuitous Copies

፩/ ማንኛውም የሀገር አቀፍ ሥርጭት ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ባለቤት ህትመቱ ታትሞ በወጣ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ መስጠት አለበት፡፡

1/ Periodicals with national distribution shall, within 5 days of print, deposit two gratuitous copies of every volume at the Agency of the National Archives and Libraries.

https://chilot.me


፪/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ሥርጭት በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆነ ታትሞ በወጣ ከ፭ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለክልሉ ቤተ-መዛግብት ወይም ለሚመለከተው ቢሮ መስጠት አለበት፡፡

፫/ የመገናኛ ብዙሃን ይህንን ግዴታ በማይወጡ ጊዜ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ፲፬ ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን እንዲወጡና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁት ሊያስገድድ ይችላል፡፡

2/ Where the circulation of periodical is confined within the bounds of a regional state, two gratuitous copies of every volume shall be deposited within 5 days of print, at the state public library or to the concerned state bureau.

3/ When the media fail to comply with these requirements, the Authority may give them a written notice to take corrective measure within 14 days and demand to be informed of the changes made.

## ፶፭. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች

## 55. Obligations of a Broadcasting Service Licensee

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ትኩረቱን በአንድ ጉዳይ ላይ አድርጎ እንዲዘግብ የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) ለሥነ-ምግባር መመሪያው ተገዥ የመሆን፣

ለ) የተለያዩ የኢትዮጵያ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ብዝሃነት፣ ፍላጎትና ስሜት የሚያንጸባርቁና የሚያስተናግዱ መረጃ ሰጪ፣ አስተማሪና አዝናኝ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣

ሐ) ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግና፣ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱና በሌሎች የሕዝብ ጥቅምና የጋራ አገራዊ እሴቶች እንዲጠናከሩ አስተዋፅኦ የሚያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት የመስጠት፣

1/ Unless it is licensed to report on a specific issue as per Article 31 Sub-Article (2), any broadcasting service licensee shall have the following obligations:

a) abide by the Code of Conduct;

b) broadcast programs that provide information, education and entertainment that reflect and accommodate the plurality, needs and values of the different sections of the Ethiopian society;

c) render a broadcast service that contributes to the country's political, social and economic development and create shared national values on constitutional issues and other matters of public interest;

https://chilot.me


መ) የማኅበረሰቡን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሠረቶች የሚጠብቁ፣ የሚያጠናክሩና የሚያሳድጉ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ሠ) በዕለቱ ፕሮግራም ውስጥ አካባቢያዊ፣ ክልላዊና አገራዊ ዜናዎችን የማቅረብ፤

ረ) ከቀጥታ ሥርጭት ውጭ የማናቸውም ፕሮግራም ይዘት በጣቢያው ከመሰራጨቱ በፊት ሕግን የሚያከብር መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሰ) በፕሮግራም ሥርጭቱ ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ የማድረግ፤

ሸ) በፕሮግራም መርሀ-ግብሩ መሠረት ፕሮግራሞችን የማሰራጨት፤ በመርሀ-ግብሩ መሠረት ማሰራጨት ካልተቻለ አስቀድሞ የማሳወቅ፤

ቀ) በማስታወቂያ አዋጅ ስለማስታወቂያ እና ድጋፍ መግለጫ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የማክበርና ማስታወቂያች በይዘት፣ በድምጸት ወይም በአቀራረብ የሚያሳስቱ ወይም መልካም ሥነ-ምግባርን እንደማይጻረሩ የማረጋገጥ፤

በ) ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች እንዲሁም ለፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ውጤቶች መብት ጥበቃ የወጡ ሕግጋትን የማክበር፤

ተ) በፕሮግራሞች ውስጥ አካባቢያዊ ባህልና ቋንቋዎችን ማበረታታትና ሕብረ-ብሔራዊ ማንነት መጎልበቱንና መጠበቁን የማረጋገጥ፤

d) render a broadcast service that safeguards, strengthens and enriches the cultural, political, social and economic fabric of the society;

e) present local, regional and national news in daily program transmission;

f) ensure the legality of the content of any program before its transmission by the station with the exception of live transmissions;

g) apply appropriate and decent language use in the program transmission;

h) transmit programs in accordance with program schedule; if it cannot be transmitted in accordance with the schedule, notify in advance;

i) respect the Provisions of advertisement and sponsorship provided under the Advertisement Proclamation, and ensure that advertisements, either in terms of content, tone or treatment, are not deceptive or are not repugnant to good taste;

j) respect laws issued to protect copyright and neighbouring right as well as inventions, minor inventions and industrial design;

k) ensure that multi-national identity is developed and maintained in programs while promoting the local culture and languages of the country;

https://chilot.me


ቸ) ዜናና መረጃን በትክክልና ከአድልኦ በጸዳ መልኩ የመሰብሰብና የማቅረብ፤

ነ) ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተያያዙ አወዛጋቢ ወይም አከራካሪ ጉዳዮችን ሽፋን ሲያገኙ በተመሳሳይ ፕሮግራም ወይም በሌላ ቀጣይ ፕሮግራም የተለያዩ አመለካከቶችን ለማስተናገድ ምክንያታዊ ጥረት የማድረግ፤

ኘ) ለአካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ የተዘጋጁ የፕሮግራም ይዘቶችን የማሰራጨት፤

ከ) በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ሕዝባዊ ተሳትፎና የሰላ ክርክር የሚደረግበትን መድረክ የማመቻቸት፤ እና

ኸ) በአጠቃላይ የብሮድካስት አገልግሎቶች ይዘት ዲሞክራሲያዊ፣ ራሱን የቻለ፣ በመረጃ የበለጸገ፣ አዲስ ነገር ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣ ሳይንሳዊ፣ ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ቻይና ታጋሽ የሆነ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር የሚያበረታቱና በሀገር ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን፣ ሀገራዊ ልምዶችንና መዳረሻ ግቦችን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፡፡

፪/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አገልግሎትና ሠራተኞች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማክበራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

ሀ) የእኩልነትን ሕገ-መንግሥታዊ መርህ፤

ለ) የኢትዮጵያ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ፍትሃዊ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፤

l) gather and present news and information accurately and impartially;

m) when controversial or contentious issues of public interest are discussed, make reasonable efforts to entertain different views on the issues, either in the same program or in other programs;

n) broadcast programs with content especially adapted for persons with disabilities;

o) provide a platform for participation and critical public debate in matters of good governance; and

p) ensure that the general content of broadcasting services promote a society that is democratic, self-reliant, well-informed, open-minded, scientific, creative, tolerant and reflective of national priorities, experiences and aspirations.

2/ The licensee of any broadcasting service shall ensure that the services and the personnel comply with-

a) the constitutional principle of equality;

b) the equitable treatment of all segments of the Ethiopian population;

https://chilot.me

ሐ) እንደአግባብነቱ ለተለያዩ ቋንቋዎች ፍትሃዊ ሽፋን መስጠት፤

መ) የሁሉም ኢትዮጵያዊያን መረጃና ሀሳብ የመቀበልና የማሰራጨት መብት፤

ሠ) የተለያዩ ተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች፣ እምነቶችና እይታዎች የማስተናገድ ኃላፊነት፤ እና

ረ) ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተያያዙ ዜናዎችና ፕሮግራሞች ከፍ ባለ ደረጃ ትክክለኛ፣ ፍትሐዊና ከአድልኦ የጸዱ የማድረግ ግዴታ፡፡

፫/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተደራሽነትንና ውድድርን ለማበረታታት በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ባለፈቃዶች ጋር መተባበር ይኖርበታል፡፡

**፶፮. <u>የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>**

፩/ ማንኛውም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) የሀገሪቱን የቋንቋና የብሔር፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ የክልልና የፖለቲካ ብዝሃነት የሚያንጸባርቁ ዜናና ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ለ) የሕዝብን ጥቅም ለሚመለከቱ ዓለም አቀፋዊ፣ ሀገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ሽፋን በመስጠት ከፍተኛ የሙያ ደረጃ የሚጠይቀውን ፍትሃዊነት፣ ገለልተኛነት፣ ሚዛናዊነትና ምክንያታዊነትን በማሟላት ሁሉን አቀፍ ዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

c) the constitutional requirement of equitable treatment of all working languages;

d) the rights of all Ethiopians to receive and impart information and ideas;

e) the mandate to provide for a wide range of audience interests, beliefs and perspectives; and

f) a high standard of accuracy, fairness and impartiality in news and programs that deal with matters of public interest.

3/ The licensee of any broadcasting service shall cooperate with other broadcasting service licensee on technical issues with the aim of promoting accessibility and competition.

**56. <u>Obligations of Public Service Broadcasting Licensee</u>**

1/ Any public service broadcasting licensee shall have the following obligations:

a) provide news and programs that reflect the country's linguistic, ethnic, cultural, religious, gender, regional and political diversity;

b) provide comprehensive news and programs on current affairs in line with the public interest, focusing on matters of international, national, regional and local significance by maintaining fairness, impartiality, rationality and balance required by the professional standard;

https://chilot.me


ሐ) የማኅበረሰብ ልማት፣ ጥቅሞችና የጋራ እሴቶችን የተመለከቱ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦችን አንድነት የሚያበረታቱ ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን ለሕዝብ የማድረስ፤

c) provide news and programs concerning societal development, matters of public interest and shared values, and encourage the unity of the people based on equality;

መ) መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ የሚያግዙ፣ የፍትህ ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚያግዙ እና የሕግ የበላይነት መስፈንን የሚያበረታቱ ዜናዎችንና ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

d) provide news and programs that assist in ensuring good governance, strengthening the justice system, and encourage the realization of rule of law;

ሠ) የሕዝቡን ባህልና ጥበባዊ እሴቶች የማስተዋወቅና የማነልበት፣ ባህላዊ፣ ሀገር በቀልና የዘመኑን የፈጠራ ልዩ ክህሎትና ገለጻ የመደገፍ፤

e) promote and enhance the cultures and artistic values of the public, support for traditional, indigenous and contemporary artistic talent and creative expression;

ረ) በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ድርጅቶችን በፍትሃዊነት የማገልገል፤

f) serve all political parties or organizations operating in accordance with the Constitution and relevant laws of the country fairly;

ሰ) ለሰብአዊ መብትና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መጠናከርና መጎልበት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን የማበረታታት፤

g) provide news and programs that contribute to the promotion of human rights and strengthen democratic systems;

ሸ) ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት የመስጠትና ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችሉ ዜናዎችና ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

h) serve vulnerable groups and provide news and programs that contribute to attracting due attention to affirmative action;

ቀ) ከሌሎች የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ጋር ግንኙነት የመመስረት፣ የሕዝብን ጥቅም በሚመለከቱና በሚያስከብሩ ጉዳዮች ላይ የዜናና የፕሮግራም ልውውጥ የማድረግ፤

i) establish relationship with other public service broadcasting licensees; exchange news and programs related with and advancing public interest;

https://chilot.me


በ) ለአካባቢያዊና ለማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የቴክኒክና የፋይናንስ እገዛና ድጋፍ የመስጠት፤

ተ) ከፍተኛ ጥራት ያለው የብሮድካስት አገልግሎትና መረጃ የሚሰጡ፣ የሚያስተምሩና የሚያዝናኑ ልዩ ይዘቶችን የማቅረብ፤

ቸ) ለአዳዲስ ይዘት አመንጪዎችና ከብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ገለልተኛ የሆኑ አካላት ለሚያመነጩት ፕሮግራም ኮታ ማስቀመጥን ጨምሮ ሀገር በቀል ይዘትን የማበረታታት፤

ኀ) ለጠቅላላው ማኅበረሰብ በሚሆኑ ፕሮግራሞችና ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአናሳ ቡድኖች፣ ለሕፃናት፣ ለወጣትና ለሴቶች የሚቀርቡትን ጨምሮ የተለያዩ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለመጠበቅ በሚዘጋጁ ልዩ ፕሮግራሞች መካከል ሚዛን የሚጠብቁ ልዩ ልዩ የብሮድካስት አገልግሎት ውጤቶችን የማቅረብ፤

ነ) ሥርዓተ-ትምህርቱን የተከተሉ ወይም ኢመደበኛና ጠቅለል ያሉ የትምህርት ርዕሰ ጉዳዮችን እና ሰፊ ሽፋን የሚፈልጉ የትምህርት ፕሮግራሞችን የማካተት፤

ኘ) ብሔራዊ ስፖርቶችን የተመለከቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብና የአናሳ ቡድኖችን ስፖርት የማበረታታት፤

አ) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይቶችና ክርክሮች በቂ ሽፋን የመስጠት፤

ከ) ጠቃሚ ሕዝባዊ ውይይቶችንና በአስፈጻሚው የመንግሥት አካል የሚሰጡ መግለጫዎችንና ንግግሮችን የማሰራጨት፤

j) provide technical and financial support and assistance for local and community broadcasting service licensees;

k) provide high quality broadcasting service and distinctive media contents that inform, educate and entertain;

l) promote local program production, including through minimum quotas for original productions and material produced by independent producers;

m) provide a range of broadcasting service material that strikes a balance between programming of wide appeal and specialized programs that serve the needs of different audiences, including persons with disabilities, minority groups, children, the youth, and women;

n) include significant amounts of educational programming, both curriculum-based and informal and general educational themes;

o) provide programs for national sports and promote minority groups' sports;

p) adequately cover proceedings of the House of Peoples' Representatives;

q) broadcast important public hearings and announcements and national addresses by the executive arm of government;

https://chilot.me


ሸ) በከፍተኛ መጠን ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤ እና፣

ወ) የሥርጭት ሥርዓታቸው በመላው አገሪቱ የሚገኙ ግዛቶችን መሸፈኑን ለማረጋገጥ የመጣር።

፪/ ማንኛውም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከማንኛውም ዓይነት ጣልቃ ገብነት በተለይም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተፈጥሮ ካላቸው ጣልቃ ገብነቶች በተጠበቀ ቦርድ መመራት ይኖርበታል።

፫/ የማንኛውም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ኤዲቶሪያል ነፃነት የተጠበቀ ይሆናል፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል።

፬/ ማንኛውም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተግባራቱን በብቃት ለመፈጸም በሚያስችል ሁኔታ በቂ በጀት ሊኖረው ይገባል።

**፶፮. <u>የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ (፩) ለህዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፍቃድ የተቀመጡት ግዴታዎች በሙሉ በማንኛውም የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በተለይም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተፈጥሮ ካላቸው ማንኛውም ዓይነት ጣልቃ ገብነቶች በተጠበቀና በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ መሠረት በተቋቋመ ቦርድ መመራት ይኖርበታል።

r) provide programs that have significant amounts of domestic contents; and

s) strive to ensure that their transmission system covers the whole territory of the country.

2/ Any public service broadcasting licensee shall be governed by a board which is protected from interference, particularly of a political or economic nature.

3/ Editorial independence of any public service broadcasting licensee shall be guaranteed; and it shall be operationally and administratively independent from any person including government and its institutions.

4/ Any public service broadcasting licensee shall have adequate budgets to discharge its functions in full capacity.

**57. <u>Obligations of Special Public Service Broadcasting Licensee</u>**

1/ All obligations of public service broadcasting stipulated under Article 56 Sub-Article (1) of this proclamation shall be applicable to special public service broadcasting licensees.

2/ A special public service broadcasting licensee shall be led by a board insulated from any political and economic interferences in accordance with the Civil Society Organizations Proclamation.

https://chilot.me


ሸ/ የማንኛውም የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ኤዲቶሪያል ነፃነት የተጠበቀ ይሆናል፣ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ ከመንግሥት እና ሌሎች የፖለቲካ እና የንግድ ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል፡፡

ቀ/ ማንኛውም የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተግባራቱን በብቃት ለመፈጸም እንዲያስችለው የገንዘብ ማሰባሰብ ተግባራትን በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ በተቀመጠው መሰረት ሊያከናውን ይችላል፡፡

3/ The editorial autonomy of any special public service broadcasting licensee shall be respected and it should operate and be administered in a manner that is impartial and neutral from governmental, political and commercial entities.

4/ In order to properly discharge its obligations a special public broadcast service licensee shall undertake its fund-raising activities in accordance with the Civil Society Organizations Proclamation.

**፶፰. <u>የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>**

ትርፍ የማግኘት ዓላማ ይዞ መቋቋሙ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ/ ዲሞክራሲያዊ የግልፅነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን ጨምሮ የማኅበረሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ መረጃዎችንና ፕሮግራሞችን ለሕዝብ የማቅረብ፤

ለ/ ፈቃድ በወጣበት አካባቢ የሚገኙ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የማገልገል፤

ሐ/ ዜናን ማካተትና ወቅታዊና አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ውይይቶችን ያካተቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

መ/ በድምሩ ብዝሃነት ያላቸውን ፕሮግራሞች፣ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ብዝሃነት በሚያንጸባርቅና በሚያስተናግድ መልኩና ብዝሃነት ያላቸውን አገራዊ ቋንቋዎችን በመጠቀም የማቅረብ፤

**58. <u>Obligations of Commercial Broadcasting Service Licensee</u>**

The licensee of any commercial broadcasting service shall, notwithstanding its profit-making objective, have the following obligations:

1/ broadcast news and programs that promote the public interest and in particular good governance issues based on democratic principles of accountability and transparency;

2/ serve all sections of society found within the local area where the license is issued;

3/ include news and provide programs that include discussions on current affairs of local, national, regional and international significance;

4/ provide programs that in the aggregate are of diverse range and reflect and respond to the diversity of society and are in a broad range of local languages;

https://chilot.me


ሠ/ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ በፈቃዱ አካባቢ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ባህልና መዳረሻ ተስፋዎች የሚያበረታቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ሸ/ በከፍተኛ መጠን ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤ እና፣

ቀ/ የኢትዮጵያ ጉዳዮችን የሚያንጸባርቁ ድራማዎችን፣ ዘጋቢ ፊልሞችንና የሕፃናት ፕሮግራሞችን የማካተት፡፡

**፶፱. <u>የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>**

፩/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) የማኅበረሰቡን የሠላም፣ የልማት፣ የማኅበራዊ እና የመልካም አስተዳደር ፍላጎት መሠረት አድርጎ የመሥራት፤

ለ) የማኅበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና ጥበባዊ እሴቶች የማስተዋወቅና የማጎልበት፤

ሐ) በፕሮግራም ዝግጅት የማኅበረሰቡን አባላት የማሣተፍ፤

መ) ሌሎች የብሮድካስት አገልግሎቶች ሊያሠራጩ ያልቻሉትን የማኅበረሰቡን የጋራ ጉዳዮች የሚመለከቱ ፕሮግራሞችን የማሠራጨት፤

ሠ) ከተለያዩ ሕጋዊ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ለማሠራጫ ጣቢያው አገልግሎት የማዋል፤

5/ provides programs that promote the culture and aspirations of the society of the area covered by the service in accordance with the terms and conditions of the license for the service;

6/ provides programs that have significant amounts of domestic content; and

7/ include drama, documentaries and children's programs that reflect Ethiopian themes.

**59. <u>Obligations of Community Broadcasting Licensee</u>**

1/ Any community broadcasting service licensee shall have the following obligations:

a) carry out its activities focused on peace, development, social and good governance needs of the community;

b) promote the language, cultures and artistic values of the community;

c) ensure the participation of the members of the community in the preparation of its programs;

d) transmit programs on issues of common interests of the community that are not getting coverage by other broadcasting services;

e) utilize income legally generated from different sources for the operation of the broadcasting station;

https://chilot.me


ረ) ለማኅበረሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ አስፈላጊ መረጃዎችንና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የማኅበረሰቡን የመረጃ አጠቃቀም ባህልና እውቀት የማዳበር፤

ሰ) የማኅበረሰቡን ፍላጎቶችና ስጋቶች የሚያንጸባርቁና በተለይም ከቋንቋ፣ ከፆታ፣ ከባህልና አሰፋፈር ጋር የተያያዙ ፍላጎቶችን ያካተቱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ሸ) በተለይ ለድሆችና ለተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተለየ ስጋት የፈጠሩ ከማኅበረሰብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የሰብዓዊ መብት፣ የልማት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የትምህርትና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

ቀ) የማኅበረሰቡን ዲሞክራሲያዊ ባህልን የሚያጎለብቱ፣ ባህሉን የሚያበለጽጉና በነዋሪዎቹ መካከል የጋራ ስሜት እንደ አግባብነቱም ሀገራዊ ሥነ-ምግባር የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

በ) የአካባቢውን ማኅበረሰብ አባላት የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉ ጉዳዮችን የማበረታታት፤

ተ) በከፍተኛ መጠን ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤ እና፣

ቸ) ከአካባቢው ማኅበረሰብ የሚመነጩና በአካባቢው ማኅበረሰብ ቋንቋ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞችን የማበረታታት።

f) provide community centered informative and entertaining programs to promote the information utilization culture and knowledge of the community;

g) provide programs that reflect the needs and concerns of the community and provide particularly for the language, gender, cultural and demographic needs of the community;

h) provide programs that highlight grassroots community issues on human rights, development, health care, education and environmental matters of special concern to the poor or marginalized in the community;

i) provide programs that deepen democratic values, enrich the culture of the community and create a sense of shared community, when relevant, national ethics among the people of the community;

j) promote the improvement of the quality of life of members of the community;

k) provides programs that have significant amounts of domestic content; and

l) promote programs with local productions and local languages.

https://chilot.me


፪/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አላማውን ለማሳካት ከእርዳታ፣ ከስጦታ፣ ከድጋፍ፣ ከማስታወቂያና ከአባላት መዋጮ የገቢ ምንጭ ሊያገኝ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የገቢ ምንጩን በተመለከተ ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

2/ Any community broadcasting service in order to meet its objective, may be funded by donations, grants, sponsorships, advertising, membership fees, or by any combination of the aforementioned.

3/ Any community broadcasting service licensee shall be obliged to notify its source of income to the Authority.

**፷. <u>የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

፩/ በባለፈቃዶች መካከል የሚደረግ የፕሮግራም ልውውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የፕሮግራም “ቻናል” ብቻ ፕሮግራሙን የማሠራጨት፤

፪/ በቀጥታ ሥርጭት የሚሠራጩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን ሲያቀርብ የፕሮግራሙን ይዘት በምልክት ቋንቋ የማቅረብ፤ እና፣

፫/ በጽሁፍ የሚያቀርባቸውን አስፈላጊ መረጃዎች በድምጽ አስደግፎ የማቅረብ፡፡

**60. <u>Obligations of Television Broadcasting Service Licensee</u>**

Any television broadcasting service licensee shall have the following obligations:

1/ without prejudice to exchange of program conducted between licensees, transmit its program only through program “channel” indicated on the license;

2/ provide sign language when transmitting current affair on live transmission; and

3/ accompany with audio the necessary information that it presents in writing.

**፷፩. <u>የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የበይነመረብ መገናኛ ብዙሃን የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡

፩/ ይዘት ለማመንጨት፣ ለማሳተምና ለማሰራጨት የሚጠቀሙት ቋንቋ ፀያፍና የብልግና፣ ዕጅን፣ ብሔርንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ አስቀድመው የነበሩም ሆነ ያልነበሩ የጥላቻ ስሜቶች እንዲፈጠሩ አስተዋጽኦ የሚያደርግና ግጭት የሚያነሳሳ እንዳይሆን የማድረግ፤

**61. <u>Obligations of Online Media</u>**

Online media shall have the following obligations:

1/ avoid language usage which are obscene and vulgar, and contribute to previously-exist and non-existing hostilities based on gender, ethnicity, and religion and incite violence in the content production, publishing and dissemination;

https://chilot.me


፪/ በበይነመረብ መገናኛ ብዙሃኑ ከመነጨ ይዘት ጋር የሚያምታታ እንዳይሆን ለማረጋገጥ ከሦስተኛ ወገን ተባባሪዎች፣ ልዩ ፍላጎት ካላቸው ቡድኖችና ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች የሚመነጭ ይዘትን በግልጽ የመለየት፤

2/ clearly indicate contents originating from third party affiliates, special interest groups, and advertisers so as not to create confusion with content produced by the online media;

፫/ የይዘት አመንጪዎችና አሳታሚዎች ይዘቶችና የይዘት ማመንጨትና ማሰራጨት ሂደት ሚዛን የጠበቀና ፍትሐዊ እንዲሁም ብዝሃነት ያላቸው ድምፆችን ያካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥረት የማድረግ፤

3/ make efforts to ensure that contents, and production and dissemination processes of producers and publishers are balanced, fair, and include diverse voices;

፬/ ይዘቶች ለሕፃናትና ለነፍሰጡር ሴቶች ተገቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥረት የማድረግ፤ የተወሰኑ ይዘቶች ተደራሽ ከመሆናቸው በፊት ተጠቃሚዎች እድሜ እንዲሞሉና የይዘቶቹን ባህሪ የተረዱና አደጋውን የተቀበሉ ብቻ እንዲጠቀሙ ምርጫ የመስጠትና እድሜያቸው ከ፲፮ ዓመት በታች እንደሆነ ለገለጹ ሕፃናት ይዘቶቹ ተደራሽ እንዳይሆኑ የመከልከል፤

4/ make efforts to ensure that the contents are appropriate for minors and pregnant women; include an opt-in request before the display explicitly asking users for their date of birth and option that indicates they have understood the nature of the content and accepted the risks of consuming, and prevent access to users who indicated they are 16 years of age or younger in their submission;

፭/ የአልኮል፣ የትምባሆና የተከለከሉ አነቃቂ ንጥረ ነገሮች ተጠቃሚነትን የሚያበረታታ ይዘት ከማተምና ከማሰራጨት የመቆጠብ፤

5/ refrain from publishing and disseminating content that is used to promote the consumption of alcohol, tobacco, and banned recreational substances;

፮/ በተፈጥሮው ወሲብ ቀስቃሽ፣ በግንዘብ የወሲብ ድርጊት እንዲፈጸም የሚያበረታታና ሕፃናትን ለወሲባዊ ጥቃት የሚያዘጋጅና በኤሌክትሮኒክ ኮሚዩኒኬሽ አማካይነት የሚፈጸም ትንኮሳን የያዘ ይዘት ከማተምና ከማሰራጨት የመቆጠብ፤

6/ ensure that the production, publication, and dissemination of content which is pornographic, soliciting sexual acts, child grooming, and encouraging cyber bullying in its nature are prohibited;

፯/ የተጠቃሚዎችን ዳታ የመጠበቅ፤ ለሦስተኛ ወገኖች አሳልፎ ለመስጠት የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲከሰቱም የተጠቃሚዎችን ግልጽ ፈቃድ አስቀድሞ የማግኘት፤

7/ protect the data of users, and obtain explicit consent from users when situations arise to make users' data available to third parties;

https://chilot.me


፲/ ንብረቶቻቸውን በመጠቀም ለሚከናወን ግብይት የአገሪቱን ኤሌክትሮኒክ ግብይት ሕግ አክብሮ የመንቀሳቀስ፣ ከተጠቃሚዎች ጋር በሚገቡት ውል ተፈጻሚ የሚሆኑ ግዴታዎችን በንብረቶቻቸው ላይ በግልፅ በሚታይ መልኩ ማተምና ለተጠቃሚዎች እንደ ማስረጃ እንዲያገለግል ኤሌክትሮኒክ ቅጂ የመስጠት፣ ተፈጻሚ የሚሆኑ ግዴታዎች ላይ ለውጥ ሲኖር በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ለተጠቃሚዎች በማሳወቅ በድጋሚ ፈቃድ የመጠየቅ፣

8/ comply with the electronic transaction law of the country for all transactions to be performed using their properties; publish all terms and conditions applicable in the contract with users visibly on their property and must provide an electronic copy to the users for record keeping; notify users and re-seek their consent within 48 hours of any changes to the terms of usage and applicability of transactions;

፱/ የተሳሳተ መረጃና የኮምፒዩተር ጥቃትን መፍጠር፣ ማተምና ማሰራጨትን ጨምሮ ኢንተርኔትን መሠረት ካደረጉ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች የመታቀብ፣ እና፣

9/ refrain from illegal online activities including the creation, publishing, and dissemination of disinformation and cyber-attacks; and

፲/ የጽሁፍ ይዘቶችን ከታተሙበት ጊዜ ጀምሮ ለ፩ አመት ያህል እንዲሁም ለኦዲዮና ቪዲዮ ደግሞ ለ፮ ወር በማኅደር የማቆየትና በቀላሉ ተፈልገው እንዲገኙ የፈለገህ አግኝ አገልግሎት የማካተት፡፡

10/ archive written content for at least 1 year from the time of publishing and 6 months for all audio and video for the time of transmission, and shall provide a search facility on their properties so that this archive can easily be searchable.

**፷፪. <u>ከሌሎች ምንጮች ይዘት የሚያሰባስቡ ወይም የሚያጠናቅሩና መልሰው የሚያሰራጩ አካላት ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም ከሌሎች ምንጮች ይዘት የሚያሰባስብ ወይም የሚያጠናቅርና መልሶ የሚያሰራጭ አካል እንዲሁም ይዘት የሚያነብ ድረ-ገጽ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

**62. <u>Obligations of Content Aggregators</u>**

Any content aggregator and content reader website shall have the following obligations:

፩/ ከተጠያቂነት የማይከላከለው ቢሆንም የይዘቱን የመጀመሪያ አመንጪ የማመልከት፣

1/ indicate the source of the original content even if it does not protect the content aggregator from liability;

፪/ ይዘቱ ከማስታወቂያና ከሌሎች መንገዶች ገቢ ለማግኘት ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ ከይዘቱ የመጀመሪያ አመንጪ በግልፅ ፈቃድ የመጠየቅ፣ እና፣

2/ notify and seek explicit permission from the originator of the content if the content will be used as part of any revenue generation through advertising and other ways; and

https://chilot.me


፫/ ጽሁፍ በቃላት ቁጥር እንዲሁም ኦዲዮና ቪዲዮ በፕሮግራም እርዝመት ሲለኩ ከይዘቱ እስከ ፲ በመቶ የሚሆነውን ከመጀመሪያ አመንጪው በግልፅ ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልገው ለሌላ ዓላማ የመጠቀም፡፡

3/ repurpose up to 10 percent, either by written word count length or length of program for audio and video, of content from content originators without seeking explicit permission from content originators.

**፷፫. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ይዘት የሚያሰራጩ አካላት ግዴታዎች</u>**

**63. <u>Obligations of Broadcasting Service Content Distributers</u>**

Any broadcasting service content distributer shall have the following obligations:

፩/ እንደ ኬብል፣ ሳተላይትና ዲጂታል መልቲፕሌክስ አንቀሳቃሽ ያሉ የብሮድካስት አገልግሎት ይዘት የሚያሰራጩ አካላት መሠረታዊ አገልግሎት ወይም በባለሥልጣኑ የሚወሰነውን ዝቅተኛውን ጥቅል አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

1/ broadcasting service content distributers such as cable, satellite or digital multiplex operators shall provide the basic service or the minimum package;

፪/ በሚያስተዳድሩት ሥርዓት ውስጥ የሚሰራጩ ሌሎች ይዘቶችን በፍትሐዊነት ለማሰራጨት እንዲችሉ ይዘት ማመንጨት ሥራ ውስጥ መግባት የለባቸውም፡፡

2/ shall not get involved in producing content to ensure fair treatment of other contents via the distribution system;

፫/ በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ፕሮግራሞችን የመያዝና የሀገራዊ ይዘት ኮታን የማክበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ they are required to carry the public broadcasters' channels, other significant domestic channels, and a minimum quota of domestic channels as determined by the Authority;

፬/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ለማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ቻናል መመደብና የገንዘብ እርዳታ ማድረግ አለባቸው፡፡

4/ cable operators are required to make one channel available to the community and provide funding for community broadcasting service licensees in accordance with the Directives of the Authority;

፭/ ስለድርጅቶቹ ባለቤትነት ሁኔታና የገንዘብ ምንጭ እንዲሁም የደንበኞቻቸውን ማንነትና አድራሻ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

5/ they shall notify the Authority regarding the owner of the company and the manner in which operations are financed; and shall provide information regarding its client, and the client's address; and

፮/ ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ የሆኑ አገልግሎቶችን በጥራት ማድረስ አለባቸው፡፡

6/ devise services in such a manner so that the programs will be accessible for vulnerable groups of the society.

https://chilot.me


**፷፬. ሀገራዊ ይዘቶችን የማካተት ግዴታዎች**

፩/ ማንኛውም ሀገር አቀፍ ሥርጭት ያለው የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት እና የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ ሥርጭት ጊዜው ቢያንስ ፹ በመቶውን ለሀገራዊ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ክልላዊ ሥርጭት ያለው የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት እና የልዩ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ፸ በመቶውን ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ አካባቢያዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም አካባቢያዊ ሥርጭት ያለው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ፸ በመቶውን አካባቢውን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው ፷ በመቶውን ፈቃድ የወሰደበት አካባቢን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

፭/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለዜና፣ ለወቅታዊ ጉዳይ፣ ለትምህርታዊ፣ ለመዝናኛና ለሌሎች ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲሁም ልዩ ትኩረት የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ተገቢውን የአየር ሰዓት መመደብ ይኖርበታል፡፡

**64. Obligation to Incorporate Domestic Content**

1/ Any national transmission program by a public service broadcasting licensee or a special public service broadcasting licensee shall allocate at least 80 percent of its weekly transmissions time to national programs.

2/ Any regional transmission program by a public service broadcasting licensee or a special public service broadcasting licensee shall allocate 70 percent of its weekly transmissions time to programs that relate to regional affairs and the rest transmissions time to nationa, local and other programs.

3/ Any local transmission program by community broadcasting service licensee shall allocate 70 percent of its weekly transmissions time to programs that relate to the local affairs and the rest transmissions time to national, regional and other programs.

4/ Any transmission program by commercial broadcasting service licensee shall allocate 60 percent of its weekly transmissions time to programs that relate to the affairs of the license area and the rest transmissions time to national, regional and other programs.

5/ A broadcasting service licensee shall allocate appropriate air time to news, current affairs, educational, entertainment and other different programs as well as programs concerning that part of a community who needs special attention.

https://chilot.me


፮/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከዓመታዊ የሥርጭት ጊዜው ወይም የፕሮግራም በጀት ቢያንስ ፲ በመቶውን ከባለፈቃዱ ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ለሚዘጋጅ ሀገራዊ ይዘት ማዋል ይኖርበታል፡፡

6/ At least 10 percent of the annual broadcasting time or at least 10 percent of the programming budget of a broadcasting service licensee shall be used for domestic contents created by producers who are independent of broadcasters.

፯/ ባለሥልጣኑ ሀገራዊ ይዘቶች ከባለፈቃዶች ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ስለሚዘጋጁበት መንገድ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

7/ The Authority may provide detailed Directives applicable to broadcasting service licensees regarding the commissioning of independently produced domestic contents.

፰/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ሲባል “ሀገራዊ የብሮድካስት ይዘት” ማለት የስፖርታዊ ክንውኖችንና ጥንቅሮችን ሥርጭት እንዲሁም ማስታወቂያ የማያካትት ሆኖ በሚከተሉት የተዘጋጀ ነው፡-

8/ For purposes of this Article ‘‘domestic broadcasting content’’ means a broadcasting program, excluding transmission of sporting events and compilations thereof, advertisements, which is produced by:

ሀ) በብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ፤

(a) a broadcasting service licensee;

ለ) በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ በሆነ ዜጋ፤

(b) by a person who is a citizen of, and permanently resident in, Ethiopia;

ሐ) አብዛኛዎቹ ዳይሬክተሮቹ፣ ባለድርሻዎቹ ወይም አባላቱ በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች የሆኑበት የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት፤

(c) by a juristic person, the majority of the directors, shareholders or members of whom are citizens of, and permanently resident in, Ethiopia;

መ) ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፰ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) የተጠቀሱት ግለሰቦች ቢያንስ ፶ በመቶ የገንዘብ ጥቅም ይዘው ከሌላ አካል ጋር በጥምረት ሲሰሩ፤

(d) in a co-production in which persons referred to under sub-article 8 paragraph (a), (b) or (c) have at least a 50 percent financial interest;

https://chilot.me


ሠ) የብሮድካስት ፕሮግራሙን ለማመንጨት ከተሳተፉት ዋነኛ ሰዎች አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ ቋሚ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች ሆነው ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፰ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) ወይም (መ) በተጠቀሱት ግለሰቦች ሲሰራ፣ ወይም፣

(e) by persons referred to under Sub-Article 8 paragraph (a), (b), (c) or (d), in circumstances where the prescribed number of key personnel who are involved in the production of the television program, are citizens of, and permanently resident in, Ethiopia; or

ረ) የብሮድካስት ፕሮግራሙን ለማመንጨት አብዛኛው ወጪ በኢትዮጵያ የወጣ ሆኖ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፰ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ) ወይም (መ) በተጠቀሱት ግለሰቦች ሲሰራ።

(f) by persons referred to under Sub-Article 8 paragraph (a), (b), (c) or (d), in circumstances where the prescribed percentage of the production costs are incurred in Ethiopia.

፱/ በብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚሰራጭ የሙዚቃ ሥራ እንደ "ሀገራዊ ሙዚቃ" የሚቆጠረው ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ሲያሟላ ነው፡-

9/ A musical work broadcast by a broadcasting service licensee qualifies as ''Domestic music'' if such work complies with at least two of the following criteria, namely:

ሀ) ግጥም ካለውና ግጥሙ በኢትዮጵያ ዜጋ የተፃፈ ከሆነ፣

(a) if the lyrics (if any) were written by an Ethiopian citizen;

ለ) ሙዚቃው በኢትዮጵያ ዜጋ የተዘጋጀ ከሆነ፣

(b) if the music was written by an Ethiopian citizen;

ሐ) ግጥሙ ወይም ሙዚቃው በዋነኛነት በኢትዮጵያ ዜጋ ወይም ዜጎች የተዘጋጀ ከሆነ፣ እና፣

(c) if the music or lyrics was or were principally performed by musicians who are Ethiopian citizens; and

መ) የሙዚቃ ሥራው በጠቅላላ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ፣ ወይም የተቀረፀና የተሰራጨ የቀጥታ ክንውን አካል ከሆነ።

(d) if the musical work consists of a live performance which is recorded wholly in Ethiopia; or performed wholly in Ethiopia and broadcast live in Ethiopia.

https://chilot.me


፲/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፰ እና ፱ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በማዘጋጀት የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ሃገራዊ ይዘት ያላቸውና ከባለፈቃዶች ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ለሚዘጋጁ ፕሮግራሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ድራማዎች ወይም ዘጋቢ ፊልሞች ዝግጅት ከዓመታዊ ገቢያቸው ምን ያህል መመደብ እንዳለባቸው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

10/ Notwithstanding Sub-Article (8) and (9) of this Article, the Authority may, in respect of the broadcasting service licensee, impose and specify such conditions, as prescribed in its Directives, regarding domestic content and independent production, which may include any conditions requiring the broadcasting service licensee to annually expend a specified sum of money, or, alternatively, a specified minimum percentage of its gross revenue, on programs, musical works, drama or documentaries which have domestic content.

**፷፭. <u>አስቸኳይ መንግሥታዊ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት</u>**

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ፡

፩/ የሕዝቡን ሠላምና ደህንነት የሚያናጋ ሁኔታ፣ ወይም

፪/ የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝቡን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ በሽታ፣ በመከሰቱ ምክንያት

የፌዴራል መንግሥት ወይም ማንኛውም የክልል መንግሥት የሚሰጠውን አስቸኳይ መግለጫዎች ያለክፍያ ማሠራጨት አለበት፡፡

**65. <u>Transmission of Governmental Emergency Statements</u>**

Any broadcasting service licensee shall transmit, free of charge, any emergency statement given by the Federal or Regional state government due to the occurrence of:

1/ an incident that endangers the peace and security of the public; or

2/ a natural disaster or an epidemic that threatens public health.

**፷፮. <u>ፕሮግራም ቀርጾ ስለመያዝ</u>**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ማንኛውንም ያሠራጨውን ፕሮግራም ለ፴ ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ አለበት፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ቀደም ሲል የተቀረጸ ፕሮግራም ወይም ፊልም ተካቶ ከሆነ አብሮ መቀመጥና በተፈለገ ጊዜ ሊገኝ መቻሉ መረጋገጥ አለበት፡፡

**66. <u>Keeping Records of Program</u>**

1/ A broadcasting service licensee shall keep the record of any transmitted program for 30 days; where the program contains a previously recorded program or film, such program or film shall be included in the record in such a way that it is accessible when required.

https://chilot.me


፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበ ወይም ለፍርድ ቤት የክስ ሂደት፣ ሙግት፣ ቅሬታ ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ክርክር መነሻ ከሆነ እነዚህ ጉዳዮች አግባብ ባለው ሕግ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚያገኙ ድረስ የፕሮግራም ቅጅውን ባለፈቃዱ ማቆየት አለበት፡፡

፫/ ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የያዘውን ፕሮግራም ቅጅ በራሱ ወጪ ለባለሥልጣኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**፷፯. <u>ውስጣዊ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት</u>**

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብን ቅሬታ ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዶች የራሳቸውን የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ተከትለው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>

## <u>የይዘት ግዴታዎች</u>

**፷፰. <u>አጠቃላይ ግዴታዎች</u>**

፩/ በእርስ በእርስ ቁጥጥር የሚወጡ የሥነ ምግባር መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም ወይም ዜና የሚከተሉትን ማክበር ይኖርበታል፡-

2/ Where a complaint is lodged against a program or when a program is the subject of judicial proceedings, dispute, complaint or other controversy before the expiry of the period specified in Sub-Article (1) of this Article, the record shall be kept by the licensee until final decision is rendered on the case in accordance with the appropriate law.

3/ Where a program is needed for inspection or to investigate a complaint lodged against it, a broadcasting service licensee shall, at its own expense, provide a copy of the program to the Authority.

**67. <u>Internal Complaint Handling Mechanism</u>**

1/ Any broadcasting licensee shall put in place and implement a compliant handling mechanism to address concerns and complaints by its audience.

2/ The Authority shall monitor whether or not licensees are properly implementing their own complaint handling mechanism.

## <u>SUB-SECTION THREE</u>

## <u>CONTENT OBLIGATIONS</u>

**68. <u>General Obligations</u>**

1/ Notwithstanding the Codes of Conduct of self-regulatory bodies of the media, any program or news transmitted through broadcasting service shall respect the following:

https://chilot.me


ሀ) ፕሮግራሞች ወይም ዜናዎችን የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ አጠቃላይ ሕብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዱ አድርጎ ማቅረብ፤ እና፣

a) Program or news should be balanced and impartial in reflecting diverse viewpoints to serve the public at large; and

ለ) የሚሰራጨው ፕሮግራም ወይም ዜና ይዘትና ምንጭ እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አሠራጩ ሪፖርቱ ላይ ተገቢ ጥንቃቄ እንዲያደርግና ስህተት ሲገኝም እንዲያርም ይጠበቅበታል፤ ጥፋቶችን ለማረም የሚያስችል ሥርዓትና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ሊኖረው ይገባል።

b) Broadcasters are expected to make reasonable effort to ensure the content and source of their program or news is accurate and put in place systems and procedures to correct mistakes when it happens.

፪/ በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ፕሮግራም ወይም ዜና፣

2/ Any program or news transmitted through broadcasting service shall not:

ሀ) የሕዝብ ጥቅምን መስፈርት በማያከብር መልኩ የማንኛውንም ሰው የግል ሕይወት የመከበር መብት የሚጥስ፤

a) violate the right to privacy of everyone subject to the requirements of the public interest;

ለ) የሰው ልጆችን ክብር የሚፃረር፤

b) offend human dignity;

ሐ) በቀጥታ ጉዳት የሚያስከትል ወይም ለጤናና ለደህንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የሚያበረታታ፤

c) cause actual harm, or encourage behavior which is harmful to health or safety;

መ) የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም እና ሠላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ የሚቀሰቅስ፤

d) incite crime or disturbance of peace and security; and

ሠ) ማንኛውም ሰው ዘርን፣ ቋንቋን፣ ዜግነትን፣ ብሔርን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ-ፆታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ በሽታንና የአካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅስ፤ መሆን የለበትም።

e) incite hatred or contempt on grounds of race, language, national or ethnic origin, colour, religion, gender, age or mental or physical disability.

https://chilot.me


፫/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጥቃት ወይም ሌላ አሰቃቂ ወይም አስደንጋጭ ሁኔታዎችን የሚዘግቡ መዋዕለ ዜና ወይም ፕሮግራሞችን ሲያሠራጭ በአቀራረባቸው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3/ A broadcasting service licensee shall take reasonable care when transmitting program or news that reports on the usage of liquor, narcotic, assault, or similar horrific or frightening situations.

**፷፱. <u>ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ደህንነት ስለመጠበቅ</u>**

በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች የተቀመጡ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ሞራልና ሥነምግባር ሊጎዳ የሚችል የብሮድካስት አገልግሎት ፕሮግራምን፡-

፩/ ከምሽቱ ፬ ሰዓት እስከ ንጋቱ ፲፩ ሰዓት ካለው ሰዓት ውጪ ማስተላለፍ የለበትም፣ ወይም፣

፪/ ከማሠራጨቱ በፊት የፕሮግራሙን አድማጭ ወይም ተመልካች የዕድሜ ደረጃ አስቀድሞ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች በማሳወቅ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ መረጃ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**69. <u>Protecting the Well–Being of Minors</u>**

Notwithstanding the prohibitions stated under the Criminal Code, any broadcasting service licensee who provide programs that may harm minors, morally and psychologically, shall ensure that such programs:

1/ only be transmitted from 10:00 PM in the evenings up to 5:00 AM in the morning; or

2/ render information to parents or tutors before transmission by notifying in advance the age level of program listener or viewer so that the parent or tutor take relevant caution.

**፸. <u>ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞች</u>**

፩/ ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን የሚያሰራጭ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች ተገቢ ክብር እንደተሰጣቸው ሊያረጋግጥና የሃይማኖት እና የእምነት ነጻነትንና መሠረታዊ ሰብዓዊ መብትን ሊጠብቅ ይገባል፡፡

፪/ ማንኛውም ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራም በሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ሃይማኖት ወይም እምነት ማንኳሰስ፣ ወይም በሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀሰቅስ የለበትም፡፡

**70. <u>Religious Programs</u>**

1/ Any broadcasting service licensee that provides religious programs shall ensure that due respect is given to all religious beliefs, and protect the basic human right to religious freedom.

2/ Any religious program which incites religious hatred or undermine any religion or belief of others, and provokes religious intolerance is prohibited.

https://chilot.me


**ሮ፩. የምርጫ ጊዜ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት**

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ፍትሐዊ የሆነ ሽፋን እንዲያገኙ ያደርጋል።

፪/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በምርጫ ወቅት የሚያቀርባቸው የዜና ዘገባዎች፣ ትንተናዎችና የውይይት መሰናዶዎች ሚዛናዊና የተሟላ ዕይታ እንዲኖራቸው የመራጮችና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ድምፅ በአግባቡ ማካተት ይጠበቅበታል።

፫/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት።

፬/ ባለሥልጣኑ አግባብነት ባለቸው ሕጎች መሠረት ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር እያንዳንዱ ፓርቲ የሚገባውን ነፃ የአየር ጊዜ ግልፅ በሆነና አስቀድሞ በተወሰነ ቀመር መሠረት ይመድባል። ምደባ የሚከናወነው የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ መስፈርቶች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይሆናል፦

ሀ) ፖለቲካ ፓርቲዎች በፌደራል እና በክልል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ባላቸው መቀመጫ ብዛት፤

ለ) የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫው ባቀረቧቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት፤

**71. Transmission of Election Period Statements**

1/ Any broadcasting service licensee shall ensure that political parties or private candidates registered in accordance with relevant laws get equitable coverage during election periods.

2/ Any licensee shall provide a balanced and comprehensive coverage of election campaigns by proportionally including the views of political parties and voters on news, analysis and discussion programs.

3/ Any broadcasting service licensee shall allocate free airtime for political parties or private candidates to publicize their objectives and programs to the public or to transmit statements during the election period.

4/ The Authority in accordance with relevant laws and in collaboration with the National Electoral Board of Ethiopia (NEBE) shall allot specific amounts of free airtime to each party according to a transparent and an equitable pre-determined formula. The allocation of the airtime shall take the following four factors into consideration:

a) The number of seats political parties have in the House of Peoples' Representatives and regional councils;

b) The number of candidates political parties present for the election;

https://chilot.me


ሐ) የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫው ባቀረቧቸው ሴት እጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አካል ጉዳተኛ እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት፤ እና፣

c) The number of female or persons with disabilities candidates of political parties present for the election; and

መ) በምርጫ ለሚሳተፉ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል እንዲከፋፈል የሚመደብ ጊዜ።

d) Equal allotment of airtime for all political parties participating in the election.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፬) ላይ ለተጠቀሱት ለአራቱ መስፈርቶች የሚሰጠው ኮታ መጠንም መርህ ተቀምጦለት ባለሥልጣኑ ከምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር ይወሰናል።

5/ The amount of quota allotted to the four factors referred to under Sub-Article (4) of this Article shall be decided by the Authority, in consultation with the National Electoral Board of Ethiopia based on the above stated formula.

፮/ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል የሚከፋፈለው የአየር ሰዓት መራጮች ድምጻቸውን ለመስጠት የሚያስችላቸውን በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማስቻልን ታሳቢ በማድረግ ይሆናል። ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመደበው ዝቅተኛ አየር ሰዓት በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል።

6/ The amount of airtime allotted to all political parties equally shall be conducted with the basic principle of providing voters with information they need to make their choices. The minimum airtime allocated to political parties shall be clearly determined.

፯/ በማንኛውም ሁኔታ ለልዩ ሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት እና ለንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ነፃ የአየር ጊዜ የመስጠት ግዴታ ከሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ያነሰ መሆን አለበት።

7/ The obligations of commercial broadcasting service and special public broadcasting service providers to allocate free airtime to political parties during election period shall be lower than public service broadcasting under any circumstances.

፰/ ነፃ የአየር ጊዜ የተሰጠው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ ለተሰራጨው ፕሮግራም ወይም መግለጫ ኃላፊ ይሆናል።

8/ The political party or private candidate provided with free airtime shall be responsible for the program or statement transmitted.

፱/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፖለቲካ ማስታወቂያ እንዲያሰራጭ አይገደድም፤ ይህን ለማድረግ ከመረጠ ግን በፓርቲዎች መካከል አድልኦ ከማድረግ፣ አንድ ፓርቲን በተለየ ሁኔታ በማስበለጥ በሌላ ፓርቲ ላይ ቅድመ ግምት ከማሳደር መቆጠብ ይኖርበታል።

9/ A broadcasting service licensee is not required to broadcast a political advertisement. But if the licensee chooses to do so, the broadcaster may not discriminate against any political party or make or give any preference to any political party or subject any political party to any prejudice.

https://chilot.me


፲/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪን የምርጫ ማስታወቂያ እንዲያስተላልፍ አይገደድም። ሆኖም ባለፈቃዱ ማስታወቂያውን ለማስተላለፍ ከመረጠ፣ መልዕክቱ ከፓርቲው ወይንም ከእጩ ተወዳዳሪው ሕጋዊ ወኪል ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።

10/ A broadcasting service licensee shall not be obliged to broadcast a political advertisement from political parties or individual candidates during an election period. However, when it chooses to do so, on its own free will, the message shall be duly approved by an authorized representative.

፲፩/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያዎቻቸውና በነጻ የአየር ጊዜ የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች የምርጫ ሕግና ደንብን ባከበረ መልኩ መከናወናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር ይኖርባቸዋል።

11/ Political parties and individual candidates are required to follow guidelines set by Electoral laws and Codes of Conduct and are responsible and subject to liability related to political advertisements and messages aired using free of charge airtime during the election period.

፲፪/ ለምርጫ ውድድር ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ በተመሳሳይ ሰዓት ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀው ክፍያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

12/ The fee required for election campaign advertisement may not exceed the fee required for equivalent commercial advertisements.

፲፫/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያዎቻቸውና በነጻ የአየር ጊዜ የሚያስተላልፏቸው ዝግጅቶች የብሮድካስት ባለፈቃዱን የቴክኒክ ጥራት መስፈርትና የመቀበያ ፎርማት ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

13/ A party, or individual candidate's election broadcast and political advertisement shall conform to a technical quality and compatibility acceptable to the broadcast licensee.

## ክፍል አምስት
## አስተዳደራዊ እርምጃዎች

## PART FIVE
## ADMINISTRATIVE MEASURES

### ፸፪. መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ በግልፅ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚያስተጓጉል አሠራር፣ አስተዳደራዊ ተግባርና እርምጃ ተከልክሏል፡፡

### 72. Basic Principles

1/ Unless expressly authorised by law, procedures, administrative actions and measures that adversely affect media freedom are prohibited.

https://chilot.me


፪/ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ሊወሰዱ፣ የአስተዳደራዊ የፍትሕ ሥነ-ሥርዓት ሊከተሉና የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱን የመሰማት መብት ሊያከብሩ ይገባል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ሲወሰድ የጥፋቱ ክብደት እና የመገናኛ ብዙሃኑ ተደጋጋሚ ጥፋቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት።

**፸፫. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና ይህን አዋጅ ተከትለው የሚወጡ ደንብ ወይም መመሪያዎች የተላለፈ መገናኛ ብዙሃን ላይ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) እስከ ብር ፪፻፺ሺ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት፤

ሐ) ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፤

መ) ጥሰት የፈጸመውን የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ፤

፪/ የባለሥልጣኑ ቦርድ በየሶስት አመቱ ግምገማ በማድረግ የእርስ በእርስ ቁጥጥር ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አደረጃጀቶች አጠቃላይ አሠራርና የሥነ-ምግባር ደንብ አፈጻጸም ይዞታ ውጤታማነትና ጥንካሬ አሳማኝ ደረጃ መድረሱን ካረጋገጠ፣ የሥነ ምግባር ደንብን ጨምሮ በዚህ አዋጅ

2/ All administrative measures on sanctions shall be taken fairly and with respect to due process rights, including the right of the broadcasting service licensee to be heard.

3/ Any administrative measure taken in accordance with this Proclamation, shall take into account the gravity of the noncompliance and the past records of recidivism of the media.

**73. <u>Administrative Measures</u>**

1/ The Authority may step by step take, as may be appropriate, the following administrative measures, where a broadcasting service provider contravenes the provisions of this Proclamation and Regulations or Directives issued in accordance with this Proclamation:

a) issue a written warning;

b) impose administrative fine up to Birr 200,000 (Two Hundred Thousand Birr);

c) suspend or terminate the program that violated the law;

d) suspend or revoke the license of the licensee that violets the law.

2/ As an alternative to the provisions of this Proclamation, the Authority may allow the self-regulation structures of the media to enforce their Code of Conduct before appealing to the Board on certain issues after conducting an evaluation every three years to check

https://chilot.me


በተለያዩ ድንጋጌዎች ውስጥ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የእርስ በርስ ቁጥጥር አደረጃጀቶች በአማራጭነት እንዲወስኑ በማድረግ የባለሥልጣኑ ቦርድ ውሳኔዎቹን በይግባኝ መመልከት ሥልጣን እንዲኖረው ሊወስን ይችላል፡፡

the effectiveness and strength of the operations of the media self-regulation bodies and their implementation of Code of Conduct.

**፸፬. <u>የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች</u>**

፩/ የሚከተሉትን ጥፋቶች የፈጸመ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡-

ሀ) የባለቤትነት መስፈርት ድንጋጌዎችን ከጣሰ፤

ለ) ዋና አዘጋጅ የመሾም ወይም የፕሮግራም ኃላፊን የማሳወቅ ግዴታ ካልተወጣ፤

ሐ) በህትመትና የብሮድካስት ሥርጭት ላይ የሚገለፁ መረጃዎችን ካላወጣ፤

መ) ያለ ክፍያ ቅጅዎች የመስጠትግዴታ ካልተወጣ፤

ሠ) ከአንቀጽ ፶፫ እስከ ፷ የተደነገጉትን የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ከጣሰ፤

ረ) የሀገራዊ ይዘት ግዴታዎችን ካልተወጣ፤

ሰ) የይዘት ግዴታዎችን ካላሟላ፤

ሸ) በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ሌሎች ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ደህንነት ስለመጠበቅ የተደነገጉትን ግዴታዎች የተላለፈ፤

**74. <u>Offences that Give Rise to a Written Warning</u>**

1/ Any media that commits the following offenses shall receive a written warning:

a) violating the provisions that deal with ownership criteria;

b) noncompliance with the obligation to notify appointment of a director or program manager;

c) noncompliance with the obligation to provide the necessary information in print and broadcasting transmissions;

d) failing to provide the gratuitous copies;

e) failing to comply with the Provisions of Article 53 and 60 of this proclamation

f) failing to comply with obligatons related with national content;

g) failing to fulfil content-related obligations;

h) notwithstanding other penalties provided under this Proclamation and other relevant laws violating provisions dealing with the duties to protect the well being of minors;

https://chilot.me


ቀ) በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ሌሎች ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን በሚመለከት የተደነገጉትን ግዴታዎች የተላለፈ፤

በ) በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡ ሌሎች ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው የምርጫ ጊዜ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት የተደነገጉትን ግዴታዎች ካልተወጣ፤

ተ) አስቸኳይ መንግሥታዊ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት የተደነገጉትን ግዴታዎች ካልተወጣ፤

ቸ) ውስጣዊ የቅሬታ አፈታት ሥርዓትን በሚመለከት የተደነገጉትን ግዴታዎች ካልተወጣ፤ ወይም፣

ኘ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ቀላል ጥፋቶችን ከፈፀመ፤

፪/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያዎች ማስጠንቀቂያው የተሰጠበትን ምክንያት፣ ባለሥልጣኑ እንዲወሰድ የወሰነው የማስተካከያ እርምጃ እና ማስተካከያውን እንዲወሰድ የሚጠበቅበትን የጊዜ ገደብ በግልጽ በማስቀመጥ ለባለፈቃዱ መድረስ አለባቸው።

**፸፭. <u>የገንዘብ ቅጣትን ስለመጣል</u>**

፩/ የሚከተሉትን ጥፋቶች የፈጸመ ማንኛውም ሰው ላይ ባለሥልጣኑ እንደአግባብነቱ የሚከተለውን የገንዘብ ቅጣት ይጥልበታል፤

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭፣፴ ወይም አንቀጽ ፵፬ የተደነገገውን ከተላለፈ እስከ ብር ፻፶ሺ (መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

i) notwithstanding other penalties provided under this Proclamation and other relevant laws violating provision dealing with religious programs;

j) notwithstanding other penalties provided under this Proclamation and other relevant laws violating provision dealing with duties related to transmission of election period statements;

k) violating provisions dealing with transmission of governmental emergency statements;

l) violating provision dealing with internal complaint handling mechanism; or

m) committing other offences found on similar levels.

2/ A written warning shall be sent to the licensee clearly stating the reasons of the Authority, the measure that should be taken, as decided by the Authority, and the time frame in which the licensee should take the corrective measure.

**75. <u>Fine</u>**

1/ Any person that commits the following offenses shall be punished with the fines stated below, as the Authority deems appropriate:

a) violating Article 25, 30 or Article 44 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 150,000 (One Hundered Fifty Thousand Birr).

https://chilot.me


ለ) በባለሥልጣኑ ድክመት ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ ወይም ፳፯ የተደነገገውን ከተላለፉ እስከ ብር ፶ሺ(ሃምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

b) violating Article 26 and 27 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 50,000 (Fifty Thousand Birr). If the registration is not conducted as a result of the Authority's failure, this provision is not applicable.

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ የተደነገገውን ከተላለፉ እስከ ብር ፲፭ሺ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

c) violating Article 53 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 15,000(Fifteen Thousand Birr).

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፭ የተደነገገውን ከተላለፉ እስከ ብር ፲፭ሺ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

d) violating Article 45 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 15,000(Fifteen Thousand Birr).

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ እና ፷፱ የተደነገገውን የተላለፉ ማንኛውም በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም የብሮድካስት ባለፈቃድ እስከ ብር ፻ሺ(መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

e) any periodical or broadcasting licensee violating Article 68 and 69 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 100,000 (One Hundered Thousand Birr).

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶ መሠረት የተላከለትን መልስ ወይም ማስተካከያ ያላወጣ የመገናኛ ብዙሃን ዋና አዘጋጅ ወይም የፕሮግራም አዘጋጅ እስከ ብር ፲፭(አስራ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

f) any editor or program producer who has failed to publish or broadcast a reply or correction sent to him pursuant to Article 50 of this Proclamation shall be punishable with a fine up to Birr 15,000 (Fifteen Thousand Birr).

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፩ የተደነገገውን የተላለፉ ማንኛውም ባለፈቃድ እስከ ብር ፶ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

g) any licensee violating Article 71 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 50,000 (Fifty Thousand Birr).

https://chilot.me


ሸ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ወይም ፳፬ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ባለፈቃድ እስከ ብር ፪፻፺ሺ(ሁለት መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

ቀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ባለፈቃድ ከብር ፶ሺ(ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

በ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የገንዘብ ቅጣት የሚያስጥል ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው እስከ ብር ፶ሺ(ሃምሳ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የገንዘብ ቅጣት የሚጣልበት ማንኛውም ሰው የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት እንደሆነና ጥሷል የተባለውን ጉዳይ እንዲያውቅ ማድረግና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ መደረግ አለበት።

፫/ ባለሥልጣኑ የገንዘብ ቅጣት መጠን ሲወስን የመገናኛ ብዙሃኑን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪዎችን የማክበር እና ቀላል የሆኑ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚታለፉ ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት።

፬/ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት። በአጠቃላይ የሚጣለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ከአጠቃላይ ካፒታሉ አንጻር ሲሰላ የመገናኛ ብዙሃኑን ህልውና ከባድ አደጋ ላይ የሚጥል መሆን የለበትም።

h) any licensee violating Article 23 and 24 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 200,000 (Two Hundered Thousand Birr).

i) any licensee violating Article 40 of this Proclamation shall be punishable with a fine not exceeding Birr 50,000 (Fifty Thousand Birr).

j) Other offences found on a similar level shall be punishable with a fine not exceeding Birr 50,000(Fifty Thousand Birr).

2/ Any person punished with the fine stated under Sub-Article (1) of this Article should be informed that they are threatened with a fine, and given an opportunity to comment, both on the alleged breach itself and on the intention to levy a fine.

3/ The amount of the fine should take into account the seriousness of the breach, the licensee's record of breaches, any financial benefit the licensee might have gained as a result of the broadcast and the overall financial state of the broadcasting service licensee.

4/ Fines should be proportionate to the offence. In general, the Authority should not seek to levy fines of such magnitude that it seriously endangers the broadcaster's viability.

https://chilot.me


**፹፮. ፕሮግራም ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ**

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ ሰ፣ ሸ፣ ቀ ወይም መሰል የሥነ ምግባር ግዴታዎችን ባለማክበር የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ማስተካከያ ያላደረገ እንደሆነ ባለሥልጣኑ እንደጥፋቱ ክብደት ፕሮግራሙ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የፕሮግራም እገዳ ወይም ስረዛ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

**፹፯. ፈቃድን ስለማገድ**

፩/ የብሮድካስት ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጡ ደንብ እና መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን በተደጋጋሚ የሚፈጽና የጥሰቱም ክብደት እየጨመረ መምጣት ማሻሻያ እንደማያደርግ የሚያሳይ ከሆነ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከ፩ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ እገዳ በጽሁፍ ሆኖ እገዳው የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና ጊዜ ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡ ባለፈቃዱ ማሻሻያ የማያደርግ ከሆነ ፈቃዱ ሊሰረዝ እንደሚችል ግልፅ ሊደረግለት ይገባል፡፡

**76. Suspension or Termination of a Program**

1/ Depending on the gravity of the offence, the Authority may suspend or terminate a program where the licensee has failed to comply with (g), (h) and (i) of Article 74 Sub-Article (1) of this Proclamation or other similar offences and fails to take corrective measure in accordance with a written warning he received.

2/ The Authority shall give to the broadcasting service licensee an opportunity to comment on the decision before the program is suspended or terminated.

**77. Suspension of License**

1/ The Authority may suspend a license for a period not exceeding 1 month where the licensee has failed to comply materially with any of the provisions of this Proclamation or Regulations and Directives issued hereunder, keeps committing more serious offenses and does not take corrective measure;

2/ The suspension given to the licensee pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be in writing and shall specify the grounds of suspension and the effective date. It should be made clear to the licensee that a failure to improve will result in the licensee being revoked.

https://chilot.me


፫/ ባለፈቃዱ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችል አሳማኝ እቅድ እና ተግባር መፈፀሙን ካረጋገጠ ባለሥልጣኑ እገዳው ተፈፃሚ እንዲሆን ከተጠቀሰው ጊዜ ቀድሞ እገዳውን ሊያነሳ ይችላል፡፡

**፸፰. <u>የፈቃድ እገዳን የሚያስከትሉ ተግባራት</u>**

ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የመገናኛ ብዙሃንን ፈቃድ ሊያግድ ይችላል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም ፸፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶበት ተገቢውን ማስተካከያ ያላደረገ እንደሆነ፤

፪/ ያለበቂ ምክንያት ሥርጭቱን ወይም አገልግሎቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ የተመለከተውን የክፍያ ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ ፤ ወይም

፬/ ፍርድ ቤት የእገዳ ውሳኔ ሲሰጥ፡

**፸፱. <u>ፈቃድን ስለመሠረዝ</u>**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጡ ደንብ እና መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን ወጥ በሆነ ሁኔታ ባለማክበር እንዲሁም የባለሥልጣኑን ትዕዛዞች ባለመፈጸም ከባድ ጥፋት ከፈጸመ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ይሰርዛል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ ስረዛ ስረዛው የተደረገበት ምክንያት፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና ጊዜ ተገልጾ ለባለፈቃዱ በጽሁፍ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

3/ If the licensee provides an evidence of a reasonable plan or action that can correct the failure, the Authority may lift the suspension before the end the suspension period imposed.

**78. <u>Grounds for the Suspension of License</u>**

A broadcasting service license may be suspended by the Authority on any one of the following grounds:

1/ where a licensee does not take corrective measure after an administrative measure was taken in accordance with Sub-Article (1) of Article 74 and Sub-Article (1) of Article 75.

2/ where the transmission has been interrupted without sufficient cause for over a month;

3/ where the licensee fails to discharge its payment obligations provided under Article 46 of this Proclamation; or

4/ where a court orders suspension of the license.

**79. <u>Revocation of License</u>**

1/ The Authority shall revoke license when a broadcaster consistently shows disregard for the provisions of this proclamation and the subordinate Regulation and Directive and commits serious offence by ignoring instructions from the Authority.

2/ The revocation of a license pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be given in writing and shall specify the grounds of revocation and the effective date.

https://chilot.me


## ፹. የፈቃድ መሰረዝን የሚያስከትሉ ተግባራት

፩/ የብሮድካስት ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፯ እና ፸፰ መሰረት እገዳ ተጥሎበት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ እገዳውን ለማንሳት የሚያስችል የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ወይም ጥፋቱን በተደጋጋሚ የፈጸመ፤

ለ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ በ፩ ዓመት ጊዜ ውስጥ መደበኛ ሥርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ) ባለፈቃዱ በራሱ ፍላጎት ሥራውን ሲያቆም፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተጥሰው ሲገኙ፤ ወይም፤

ረ) ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የባለቤትነት መስፈርት ድንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ እንደሆነ፤ ይህንንም ለማሻሻል የማይችልና የማይፈልግ መሆኑ ሲረጋገጥ፡፡

፪/ የብሮድካስት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መደበኛ ሥርጭቱን ለመጀመር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው ስለመሆኑ አመልክቶ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ሥርጭቱን ለመጀመር የሚያስችል ከ፩ አመት የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 80. Grounds for the Revocation of License

1/ A broadcasting service license may be revoked by the Authority on any one of the following grounds:

a) where a licensee that has been suspended in accordance with Article 77 and 78 of this Proclamation does not take corrective measure within the suspension period or keeps committing the same offence;

b) where it is proved that the licensee has failed to commence transmission within 1 year from the date of obtaining the license;

c) when it is proved that the licensee has obtained the license by deception;

d) where the licensee, in his own will, stops the service;

e) where the provisions of Sub-Article (2) of Article 68 of this Proclamation are violated; or

f) when the licensee is in breach of the ownership requirements and is not able or willing to comply with.

2/ Where the licensee lodges application and the Authority proves the existence of force majeure which hindered a broadcasting licensee from commencing regular transmission within the period referred to in paragraph (b) of Sub-Article (1) of this Article, it may allow additional time not exceeding 1 year, for commencement of the transmission.

https://chilot.me


**፹፩. የአስተዳደራዊ እርምጃዎች ውሳኔ አሰጣጥ**

፩/ የፈቃድ አለማደስ፣ የፈቃድ ማገድ ወይም የፍቃድ መሰረዝ የሚያስከትሉ ውሳኔዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

፪/ ቦርዱ የፈቃድ አለማደስ፣ የፈቃድ ማገድ ወይም የፈቃድ መሠረዝ የሚያስከትል ቅጣት የሚጸርግ ክስ ሲቀርብለት ባለፈቃዱ በጉዳዩ ላይ ያለውን ምላሽ በፅሑፍ እና በአካል እንዲያቀርብና ጉዳዩ ላይ ሕዝባዊ አስተያየት እንዲሰጥ የማድረግ እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

፫/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ ከባድ የገንዘብ ቅጣት ወይም አንድን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሠረዝ በባለሥልጣኑ ሊወሰን ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በተወሰኑት ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ፲፬ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፤ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፭ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቦርዱም ሆነ ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ መስጠት አለባቸው፡፡

**፹፪. ስለ አቤቱታና ይግባኝ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፬) መሰረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ውሳኔው በደረሰው በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

**81. Decision-Making on Administrative Measures**

1/ The Board shall have the power to make decisions resulting on refusal to license renewal, and suspension and revocation of licenses.

2/ Where the Board intends to refuse renewal, suspend, revoke license, it shall give the licensee the opportunity to present its views in person; submit to the Authority within the time specified by the Authority, a written statement of objections to the refusal suspension of the license; and request for holding a public hearing in connection with the issue.

3/ Decisions on giving written warning, imposing serious fine, taking measures or suspendingor terminating a program can be taken by the Authority.

4/ Any person who is aggrieved by the order given by the Authority as specified under Sub-Article (3) of this Article, may submit his grievance to the Board within 14 working days from the date of receipt of the decision; and the Board shall give its decision within 30 working days from the date of receipt of the grievance.

5/ According to this Article, the Board or the Authority shall give its decisions related to administrative measures within 30 working days.

**82. Petition and Appeal**

1/ Any party who is aggrieved by the decision given by the Board pursuant to Sub-Article (1) or (4) of Article 81 of this Proclamation may submit his petition to the Federal High Court within 30 working days from the date of receipt of the decision.

https://chilot.me


፪/ ውሳኔውን የሰጠው ቦርድ አመልካቹ አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን በፅሁፍ ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለበት፡፡

፫/ በቦርዱ ውሳኔ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉዳዮችን በመመርመር በአቤቱታው ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

፬/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታው በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

፭/ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ፴ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤትም አመልካቹ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ የፍርዱን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለበት፡፡

፮/ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙ በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት
## ሕጋዊ እርምጃዎች

### ፹፫. መሠረታዊ መርሆዎች

፩/ መገናኛ ብዙሃን ሕግን አክብረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

፪/ ሕጋዊ እርምጃዎች በሕግ መሰረት የሚከናወኑና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በማያጠብ መልኩ የሚተገበሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

2/ The Board shall give a copy of its decision to the applicant within 7 working days from the date of request by the applicant in writing .

3/ The Federal High Court has a power to review a question of fact and law on petition on the decision of the Authority.

4/ The Federal High Court shall give its decision within 30 days of receiving the appeal.

5/ Any party aggrieved by a decision of a court may, within 30 days, lodge an appeal before the appellate court. The court shall send a copy of its decision to the applicant within 24 hours from the date of the request.

6/ The appellate court shall give its decision within 30 days of receiving the appeal.

## PART SIX
## LEGAL LIABILITIES

### 83. Basic Principles

1/ Media shall operate respecting the law.

2/ Legal liabilities shall be imposed in accordance with the law and shall not constitute undue infringements on the right to freedom of expression.

https://chilot.me


**፹፬. የስም ማጥፋት ተጠያቂነት**

፩/ የሥም ማጥፋት ተግባር በመገናኛ ብዙሀን ሲፈጸም ከፍትሐብሔር ሀላፊነት በስተቀር በወንጀል አያስጠይቅም፡፡

፪/ የሥም ማጥፋትን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙሃን ላይ የሚጣለው የህሊና ጉዳት ካሣ ከብር ፫፻ሺ(ሦስት መቶ ሺህ ብር) ሊበልጥ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የህሊና ጉዳት ካሣ ሲወሰን የመገናኛ ብዙሃንን የትርፍ ሁኔታ፣ የደረሰው የጉዳት መጠን እና የሚወሰነው ካሳ በመገናኛ ብዙሃኑ ህልውና ላይ ያለው ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

፬/ ምንም ዓይነት የሕዝብ ጥቅም በሌለበት በግለሰቦች ላይ ከሚፈጸመው በስተቀር፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች በሥም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትሉ አይችሉም፡-

ሀ) የመጉዳት ሀሳብ ከሌለና የንግግሩ ይዘት እውነተኛ የሆነ እንደሆነ፤

ለ) የንግግሩን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ተቀባይነት ያላቸውን አካሄዶችና መንገዶች ሁሉ ተጠቅሞ ያገኘው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ በቅንነት በማመን ያደረገው ንግግር ከሆነ፤ ወይም፣

ሐ) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተደረገ ንግግር ከሆነ፡፡

፭/ የሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች በስም ማጥፋት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትሉ አይችሉም፡-

**84. Liability for Defamation**

1/ When an act of defamation is committed through media,it shall result in civil liability, not criminal liability.

2/ A moral compensation for defamation by the media shall not exceed Birr 300,000 (Three Hundered Thousand Birr)

3/ In determining the amount of compensation and penalty pursuant to Sub-Article (2) of this Article, profit conditions, the seriousness of the damage and the effect the compensation would have on the viability of the media shall be taken into account.

4/ With the exception of an attack on individuals without any public interest, the following conditions shall not result in civil liability for defamation:

a) when the content of the statement is true, and there is no intent to harm;

b) when statements were made with genuine belief that the statements are true after following acceptable mechanisms and means to verify the accuracy of facts; and

c) when the statement is made in the interest of the public.

5/ The following special conditions shall not result in civil liability for defamation:

https://chilot.me


ሀ) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት፣ ወይም በክልል ምክር ቤቶችና ሥራ አስፈፃሚ አካላት የተደረገ ንግግርን አስመልክቶ የሚደረግ ንግግር ከሆነ፣

ለ) ማንኛውም የፌደራልም ሆነ የክልል መንግሥታት ተሿሚዎች፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ በምክር ቤትም ይሁን በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው የተደረገ ንግግርን ወይም ውሳኔን አስመልክቶ የሚደረግ ንግግር ከሆነ፣

ሐ) በፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ በዳኞች፣ ጠበቆች፣ ተከላካይ ጠበቆች፣ ዓቃቢያነ ሕግ፣ ነገረ-ፈጅ፣ ወይም ምስክሮች የሚያደርጉት ንግግር፣ ወይም፣

መ) የሕግ ግዴታ ያለበት ሰው የሚያደርገው ንግግር።

፮/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፭) የተዘረዘሩት ልዩ ሁኔታዎች ምንም ዓይነት የሕዝብ ጥቅም በሌለበት የተጠቀሱት ግለሰቦችን ግለ ሰብዕና ለማንቋሸሽ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይገባም።

## ፹፭. <u>የእገዳ እርምጃዎችን ስለመውሰድና እግድ ስለመጣል</u>

፩/ እንደነገሩ ሁኔታ የፌደራል ወይም የክልል ዓቃቤ ሕግ በብሔራዊ ደህንነት ላይ ከሥርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ሕገ ወጥ ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የህትመት ውጤቱ ወይም የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲያዝ ማመልከት ይችላል።

a) statement made by the Federal Democratic Republic of Ethiopia President, Prime Minister, members of the House of Peoples' Representatives, members of the Council of Ministers, or members of Regional Councils and Executive organ;

b) statement made on any speech or decision by Federal or Regional government appointees, Peoples' Representatives, at Federal or Regional parliament or in their official capacity;

c) statement made by judges, attorneys, defence counsel, prosecutors, legal counsel, or witnesses in a court proceeding; or,

d) statement made by a person who has a legal obligation.

6/ The special conditions listed under Sub-Article (5) of this Article shall not be used to attack the personality of individuals mentioned without any public interest.

## 85. <u>Impounding and Injunction</u>

1/ Where the Federal or Regional public prosecutor, as the case may be, has sufficient reason to believe that a periodical or a broadcasting service which is about to be disseminated or transmitted contains illegal matter which would, if disseminated, lead to a clear and imminent grave danger to the national security which could not otherwise be averted through a subsequent imposition of sanctions, may apply to Federal High Court to get a grant of an order to impound the periodical or an injunction order forbidding transmission of a broadcasting service.

https://chilot.me


፪/ ዓቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትዕዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ውሳኔ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ አንድን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ከሥርጭት እንዲታገድ ውሳኔ በሰጠ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ እግዱ በ፵፰ ሰዓት ለፍርድ ቤት ካልቀረበ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የእግድ ማስታወቂያ የደረሰው ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕጉ የእገዳ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ፷፬ ሰዓት ውስጥ የእገዳ እርምጃው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭/ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት እንዲታገድ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተሰጠው ትዕዛዝ ሲቀርብለት፡-

ሀ) በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሕገ-ወጥና ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው የጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉን ትዕዛዝ በማፅደቅ ዓቃቤ ሕጉ የማገድ እርምጃ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ባለው በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ የወንጀል ክሱን እንዲመሰርት ማመልከቻ እንዲያቀርብ ማዘዝ አለበት፡፡ ዓቃቤ ሕግ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ካልፈጸመ ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት እንዲያዝ ወይም ሥርጭቱ እንዲቋረጥ የሰጠውን ትእዛዝ ያነሳል፡፡

2/ In cases of extreme emergency, where it is not possible for a public prosecutor to obtain a court order in time to prevent the harm, the Attorney General may order the periodical to be impounded or forbid the transmission of a broadcasting service.

3/ The Attorney General shall notify the Federal High Court of the order to impound the periodical or an injunction order forbidding transmission of a broadcasting service within 48 hours.The impounding or injuction is considered no longer enforce should the Attorney General fails to inform the court within 48 hours.

4/ The court stated under Sub-Article (3) of this Article shall determine within 24 hours whether or not the Attorney General's order shall be upheld.

5/ The Federal High Court to which the order to impound a periodical or an injunction order forbidding transmission of a broadcasting service issued by the Attorney General, is submitted may.

a) if it deems that periodical or the broadcasting service contains unlawful matter that is likely to cause serious danger, uphold the Attorney General's measure and order that criminal proceedings be instituted within 15 days from the date on which the court pronounced its decision. If the Attorney General fails to take such action, the court shall revoke the order to seize the periodical or the broadcasting service and bar its dissemination or transmission; or

https://chilot.me


ለ) በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሕግን የማይተላለፍና ከፍተኛ ጉዳትን የማያስከትል ሆኖ ካገኘው በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተሰጠውን የእገዳ ትዕዛዝ ውድቅ በማድረግ የታገደው ህትመት እንዲለቀቅ ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ካልታገደ በስተቀር ትዕዛዙ በተሰጠ በ፵፰ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል።

b) if it deems that the content of a periodical or a broadcasting service is lawful and not likely to cause any damage, revoke the impoundment order issued by the Attorney General and may order the release of the publication or transmission of the barred broadcasting service. Unless otherwise the stay of execution is issued by an appellate court the order shall be executed after the lapse of 48 hours.

፮/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ላይ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ ፍርድ ቤቱ ህትመቱ እንዲያዝና እንደአስፈላጊነቱ ቀጣይ እትሞች ከማውጣት እንዲታገድ ወይም የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ለመሰረዝ ይችላል።

6/ Once criminal proceedings have been instituted for offences committed through a periodical or a broadcasting service or an application is made to the court for a periodical to be impounded or forbid the transmission of a broadcasting service, the court shall have the power to order the publication to be impounded and its further dissemination be barred or forbid the transmission of a broadcasting service, or revoke an order, that has been issued under Sub-Article (4).

፯/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ሥርጭት ላይ የሚሰጥ የእገዳ ትዕዛዝ ለትዕዛዙ መነሻ የሆነውን አንቀጽ ወይም አንቀጾች፣ የህትመቱን ቅፅ፣ ጽሁፉ የወጣበትን እትም መግለጽ አለበት። እገዳውም ለሥርጭት በተዘጋጁ ህትመቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል።

7/ An order for the impoundment of a periodical shall contain a statement indicating the offending passage or passages in the publication which occasioned the order and shall specify the volume, part, issue, or installment in which these passages occur. An order for the impoundment of a periodical shall relate only to copies intended for dissemination.

https://chilot.me


፰/ ዓቃቤ ሕግ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን አግባብ በሌለው መንገድ የተጠቀመበት እንደሆነ በሕግ ይጠየቃል፡፡ አላግባብ መጠቀማቸው የተረጋገጠ የመንግሥት አካላት የሆኑ ግለሰቦች ላይም አስተዳደራዊና የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡

8/ The prosecutor shall be legally liable for a malicious exercise of his powers under this Article. Administrative sanctions and fine may be imposed on the individuals within the government institutions for a malicious exercise .

**፹፮. <u>ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዙ ክሶች ስለሚቀርቡበትና ስለሚሰሙበት ሁኔታ</u>**

**86. <u>Manner of Instituting and Hearing Media Related Cases</u>**

፩/ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የወንጀል ድርጊት በመፈፀም የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ወይም አካል በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ለተጨማሪ ምርመራ በእስር እንዲቆይ ሳይደረግ ክሱ በቀጥታ በዓቃቤ ሕግ አማካኝነት ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

1/ Any person charged with committing an offence through the media by the public prosecutor shall be brought promptly before a court, without being remanded for further investigation pursuant to the Provisions of Criminal Procedure Code.

፪/ ክሱን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻው በቀረበለት በ፲፭ ቀናት ውስጥ ክሱ እንዲሰማ ማድረግ አለበት፡፡

2/ The court having jurisdiction over the case shall commence the hearing of the case within 15 days of the filing of the charge.

፫/ ፍርድ ቤቱ ክሱ ከመሰማቱ ቢያንስ ከ፭ ቀናት በፊት የክሱን ማመልከቻ ግልባጭ ወይም ቅጂ እንዲሁም የቀረቡ ማስረጃዎች ካለ ለተከሳሹ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

3/ The court shall cause the accused person to obtain a copy of the charge, together with a copy of any evidence, at least 5 days before the commencement of the trial.

፬/ ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱ መሰማት ከጀመረበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢበዛ በ፩ ወር ጊዜ ውስጥ ፍርድ መስጠት ይኖርበታል፡፡

4/ The court shall pronounce its judgment within 1 month from the commencement of the trial.

፭/ ተከሳሹ በአድራሻው ባለመገኘቱ የተነሳ መጥሪያውን ለማድረስ ያልተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በ፯ ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን የሚገልፅ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲወጣ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

5/ Where it has not been possible to deliver a summons personally to the accused person because he was not found at his address, the court shall require a notice to be posted announcing the summons and notifying the accused that the hearing shall proceed in his absence should he fail to appear within 7 days.

https://chilot.me


**፹፯. ስለ ይርጋ**

፩/ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በየጊዜው በሚወጣ ህትመት አማካይነት የሚፈጸም የወንጀል ጥፋት ህትመቱ ከተሰራጨበት ወይም ከተላለፈበት ቀን አንስቶ እስከ ፩ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክሱ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

፪/ በብሮድካስት አማካይነት ለሚፈፀም ጥፋት ጥፋቱ የተፈፀመበት ፕሮግራም ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው ፮ ወር ጊዜ ውስጥ ምርመራ ካልተጀመረ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

፫/ በበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን አማካይነት ለሚፈፀም ጥፋት ጥፋቱ የተፈፀመበት ፕሮግራም ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው ፫ ወር ጊዜ ውስጥ ምርመራ ካልተጀመረ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፹፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሠረት የተሰጡ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዶች እንደፀኑ ይቆያሉ፤ ባለፈቃዱም አደረጃጀቱን በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲያሻሽል ይደረጋል፡፡

፪/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት በድጋሚ መመዝገብ ሳያስፈልገው ሥራውን ይቀጥላል፣ ሆኖም ባለስልጣኑ የሚፈልገው መረጃ በሚኖርበት ጊዜ ይህንኑ ማቅረብ ሀላፊነት አለበት፡፡

**87. Statute of Limitation**

1/ Notwithstanding the Provision of Article 28 Sub-Article (1) of the Constitution, no criminal proceeding for an offence committed through a periodical may be instituted after the lapse of 1 year from the date when the offending item was published.

2/ No criminal proceeding for an offence committed through a broadcasting service may be instituted if criminal investigation is not started with 6 months from the date when the offending program was broadcast.

3/ No criminal proceeding for an offence committed through an online media may be instituted if no investigation is started with 3 months from the last date on which the offending program was available online.

## PART SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**88. Transitory Provision**

1/ The broadcasting service licenses granted in accordance with the law before the coming into force of this Proclamation shall remain in force; and the licensee shall improve its organization in accordance with this proclamation.

2/ Periodicals in operation prior to the coming into force of this Proclamation shall continue in operation. But whenever the authority seeks information, it shall present it.

https://chilot.me


**፹፱. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

፩/ በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፡፡

፪/ ማስታወቂያን በተመለከተ በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፱/፪ሺ፬ ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሰረት ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፡፡

**89. Transfer of Right and Obligation**

1/ The rights and obligations of the Ethiopian Broadcasting Authority established under the Broadcasting Service Proclamation No. 533/2007 are hereby transferred to the Media Authority.

2/ The regulatory powers and duties vested in Ethiopian Broadcasting Authority as stipulated under the Advertisement Proclamation No. 759/2012 deals about advertisement are hereby transferred to the Authority.

**፺. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ በግልፅ በተሰጡት ጉዳዮች ላይ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

፫/ ፍትሐዊነትንና ግልፅነትን ለማረጋገጥም ባለሥልጣኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች አሳትሞ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በረቂቅ መመሪያ ላይ የባለድርሻ አካላት እና ሕዝባዊ አስተያየት መድረክ ያዘጋጃል፡፡ ሁሉም መመሪያዎች ሲወጡ ስለመውጣታቸው ባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

**90. Power to Enact Regulation and Directive**

1/ The House of Peoples' Representatives shall enact Regulation to implement this Proclamation.

2/ The Board shall issue Directives on clearly stipulated issues under this Proclamation and the Regulation enacted in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ In order to ensure fairness and transparency, the Authority shall publish all of its Directives and make them accessible to the public.

4/ The Authority shall organize stakeholders' consultation and conduct public hearings in respect of a draft directive. All directives prescribed ought to be subject to a public notice.

https://chilot.me


**፺፩. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

፩/ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር ፭፻፺/፪ሺ ላይ የመገናኛ ብዙሀንን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፫/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዕዛዝ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፺፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**91. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ Provisions concerning mass media on Mass Media and Access to Information Proclamation No. 590/2008 are here by repealed with this proclamation.

2/ Broadcasting Service Proclamation No. 533/2007 is hereby repealed.

3/ No law, Regulation, Directive, order or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect in respect of matters covered hereunder.

**92. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 5th Day of April, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**
**PRESIDNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me